

ወይዘሮ አስቴር ወርቅነህ እሸቱ ከባላማባራስ እማኙ ይመር ጋር፣ወይዘሮ ኤሊሣቤት ወርቅነህ እሸቱ፣ከልጅ ኃይሌ ተድላ ዘለቀ ጋር አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በተክሊል ተጋቡ።

ጋብቻ በዘመናዊ መንገድ እንዲካሄድ ያላቸው አስተሳሰብ፣ለሴቶች ልጆች ነጻነት ያጎናጸፈና ጋብቻ በዘመድ አዝማድ ውሳኔ ሳይሆን በፍቅርና በመግባባት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ተገቢ ግንዛቤ የሚሰጥ ምክር ነው። በዚህም መሰረት በወላጆቻቸው እና በቤተ ዘመዶች፣በፍቅርና በደስታ ተመርቀው ሙሽሮቹ በየአውቶሞቢላቸው ተሳፍረው ወደየቤታቸው ሄዱ።

ሁለቱን ሴቶች ልጆቻቸውን በአንድ ቀን ሠርግ በአንድነት ድረው እና ለዊልፍሬድ ቴሰገር የጉዞ ፈቃድ ከሰጡ በኋላ ወደ አዲስ አበባ የመጡበትን ጉዳይ እንደጨረሱ፣በንጉሠ ነገሥቱ ተጠርተው ሐኪም ወርቅነህ ቀደም ሲል ጠይቀው የነበረው የጨው ንግድ ተፈቀደላቸው። ለዚህ ንግድ ተፈላጊ የሆነውን ሁሉ አዘጋጅተው ወደ አሰበ ተፈሪ ተመለሱ።

በጥር ወር መጨረሻ ሐኪም ወርቅነህ ወደ ሹመት አገራቸው አሰበ ተፈሪ እንደገቡ የጨርጨር አውራጃ ወምበር (ዳኛ) አቶ መሸሻ እያስቸገሯቸው መሆኑን በመግለጥ፣ከእሱ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ አልነበሩም።



ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችን በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር መነጋገር የተፈቀደላቸው መሆኑ እየታወቀ፣የሐረርጌ ዋና አስተዳዳሪ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ሐኪም ወርቅነህን እንደታዛዥ ያይዋቸው ጀመር። ከደጃዝማች ገብረማርያም ጋር ያለውን አለመግባባት እልባት ለማስያዝ እና ጉዳዩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቋጨት በማሰብ መጋቢት ፲ ቀን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ሄዱ። በዚህ ጉዳይ ላይ አዛዥ ወርቅነህ ጠንካራ አቋም ስለነበራቸው ደጃዝማች ገብረማርያም ከሐረርጌ ዋና አስተዳዳሪነት እንዲሻሩ ጠይቀው ሚያዚያ ፪ ቀን ወደ አሰበ ተፈሪ ተመለሱ።

ሚያዚያ ፳፤ አንድ አሳዛኝ ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥቱ ደረሳቸው። ይኸም፣እሳቸውና አቶ ደሬሳ የተበደሩትን ገንዘብ ካልከፈሉ፣ዱብዳ ያላቸው የማዕድን ማምረቻ ይወረሳል የሚል ነበር። ደብዳቤው እንደ ደረሳቸው ወደ አዲስ አበባ ለአቶ ደሬሳ በልክ ደውለው ስለዚህ ጉዳይ ትንሽ ተነጋገሩ። አቶ ደሬሳ (በኋላ ብላታ) ሲናገሩ "ደብዳቤው ለኔም ደርሶኛል፣ስለዚህ እኔ ወደ እርስዎ ዘንድ መጥቼ በጉዳዩ እንወያይበት" የሚል ሃሳብ አቀረቡ። ሐኪም ወርቅነህ እና አቶ ደሬሳ በዚህ ሃሳብ ስለተስማሙ፣ከአንድ ሳምንት በኋላ አቶ ደሬሳ አሰበ ተፈሪ ገብተው ከሐኪም ወርቅነህ ጋር ተገናኙ። ሁለቱ ሸርከኞች ስለ ብድር ክፍያው ጉዳይ ከተነጋገሩ በኋላ አቶ ደሬሳ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ሐኪም ወርቅነህ ንብረቶች ሸጠው ዕዳቸውን ለመክፈል ወሰኑ። ለሚስታቸው ለወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ደብዳቤ ጽፈው ይህን ሐሳብ ገለጡላቸው። ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ለትጻፈላቸው ደብዳቤ አጥጋቢ መልስ ባለመስጠታቸው አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ቅር ተሰኙ። በዚህ መሐል ሐኪም ወርቅነህ የደጃዝማች ገብረማርያምን ከሐረር ግዛት መነሳት ቸር ወሬ ሰሙ። ቸር ወሬ ያልኩበት ምክንያት፣ቀደም ሲል እንደገለጥኩት (በሁለቱ አስተዳዳሪዎች መሐከል አለመግባባት ተፈጥሮ ስለነበረ ነው። በእሳቸው ምትክ ልዑል መኮንን የሐረርጌ አውራጃ ዋና አስተዳዳሪ ሊሆኑ ነው እየተባለ በአሰበ ተፈሪ እና በየአውራጃዎቹ ተወራ። እንደተባለውም፣ልዑል መኮንን የሐረርጌ አስተዳዳሪ ሆነው ከመሄዳቸው በፊት፣ጃንሆይ እና እቴጌ በጨርጨር በኩል ሲያልፉ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ መዔሶ ባቡር ጣቢያ ላይ ተቀበሏቸው። ዕለቱኑ ንጉሠ ነገሥቱ እና እቴጌ ሐረር ገብተው አደሩ። በማግስቱ፣ንጉሣዊ ቤተሰቦች መኳንንትና ወይዛዝርት በተገኙበት፣ልዑል መኮንን ኋይለ ሥላሴ የሐረርጌ ዋና አስተዳዳሪና እንደራሴ ሆነው በይፋ ተሾሙ። የሹመት ሥነ ሥርዓቱ ካለቀ በኋላ፣ጃንሆይ ወደ አዲስ አበባ ከመመለሳቸው በፊት ወደ አሰበ ተፈሪ ሄደው፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ያሠሩትን አዲስ የጉምሩክ ሕንፃና ዘመናዊ ሱቆች ጎበኙ። አዲሱ የሐረርጌ አገር አስተዳደሪ፣ልዑል መኮንን ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ መዔሶ ባቡር ጣቢያ ተገኝተው ሸኟቸው። ሐኪም ወርቅነህም ከሦስት ቀን በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ሄዱ። ዋናው የተጠሩበት ምክንያት ዶክተር ጆን ሜሊ የሚባሉ እንግሊዛዊ ሐኪም፣ የሕክምና ማስተማሪያ የሚሆን ትልቅ ሆስፒታል አዲስ አበባ ውስጥ የማቋቋም ሃሳብ ስለነበራቸው፣ከሐኪም ወርቅነህ ጋር እንዲነጋገሩ ጃንሆይ ስለፈለጉ ነው።



ወይዘሮ አስቴር ወርቅነህ እሸቱ ከባላማባራስ እማኙ ይመር ጋር፣ወይዘሮ ኤሊሣቤት ወርቅነህ እሸቱ፣ከልጅ ኃይሌ ተድላ ዘለቀ ጋር አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በተክሊል ተጋቡ።



ሐኪም ወርቅነህ ከበላታ ደራሳ ጋር በስልክ ሲነጋገሩ

ሁለቱ ሐኪሞች ስለ ትምህርት ቤቱ ጉዳይ ሲነጋገሩ፣ዶክተር ሜሊ ሊገነቡ ያሰቡት ትምህርት ቤት ለዘመኑ በጣም ግዙፍ በመሆኑ ከአቅም በላይ ስለሚሆን ሃሳቡ ከፍጻሜ የሚደርስ ለመሆኑ ሐኪም ወርቅነህ ጥርጣሬ አደረባቸው። የጥርጣሬያቸው መነሻ፣ዶክተር ሜሊ ለሕክምና ሙያ ትምህርት ቤት ለመክፈት ያሰቡት ሕንፃ ግዙፍነት ነበር። እንደ ሐኪም ወርቅነህ አባባል፣ሕንፃውን ለመሥራት የሚያስፈልገው የግንባታ ዕቃ አቅርቦት ማነስ እና ይህን በመሰለ የሕክምና ትምህርት ቤት ለመማር የሚችሉ ወጣቶች ቁጥር እጥረት መኖሩ ሌሎቹ ምክንያቶች ናቸው። ይህን ችግር ለጃንሆይ እና ለዶክተር ሜሊ አስረዱ። ዶክተር ሜሊም ጉዳዩን ጠለቅ አድርጎ ከአሰበበት በኋላ፣ለሌላ ጊዜ ተለዋጭ ሐሳብ ይዤ እመጣለሁ በማለት ከጃንሆይ ተሰናብቶ ወደ አገሩ ተመልሶ ሄደ።



በዚያው ሳምንት እሑድ ጠራሽ እስኩ ወሰን ከደሴ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ስለ ነበረ፣ሐኪም ወርቅነህ ከእሳቸው ጋር ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ፣ወደ አሰበ ተፈሪ ተመለሱ። ሐኪም ወርቅነህ አሰበ ተፈሪ የገቡ ዕለት፣የሐረር አዋሎች (Harrar Awals) በእንግሊዝ መንግሥት የተሰጣቸውን የጥገኝነት ፓስፖርታቸውን መልሰው፣በጨርጨር አውራጃ አስተዳደር ስር በሚገኘው ኩርፋ ውስጥ ለመኖር መጠየቃቸውን ሰሙ። አዋሎቹ የሚገኙት ኩርቱ ከሚባል ቦታ በመሆኑ፣ሐኪም ወርቅነህ ነሐሴ ፯ ቀን ወደዚያ ሄዱ። ሰዎቹን ተቀብለው ከአነጋገሯቸው በኋላ ግሪፊያ መሬት እና ገንዘብ ሰጧቸው። ኩርቱ በነበሩበት ጊዜ የራምሴ ማክዶናልድ (Ramsey MacDonald) የግል ፀሐፊ ለሆኑት ሚስተር ኔቪል በትለር (Misterr Neville Butler) እንደ ደብዳቤ ጻፉ። የደብዳቤው ይዘት "የእንግሊዝ ቅኝ በሆነችው ሶማሌ የዚይላ ወደብ ተመልሶልን ኢትዮጵያ በነፃ ወደብነት እንድትጠቀምበት እንዲፈቀድ ቀደም ሲል ለጻፍነው ደብዳቤ መልሱን እየጠበቅን ነው" ይላል። መልሱ ግን ያው የተለመደው ዝምታ ሆነ። ይህ ጉዳይ ሳያልቅ፣አቶ ሐኪም ወርቅነህ የኢሉባቦር አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ከንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈ ደብዳቤ ደረሳቸው። በዚያን ዘመን የኢሉባቦር አስተዳዳሪ ፊታውራሪ ማሞ ነበሩ። አቶ ሐኪም ወርቅነህ ከሹመቱ በስተጀርባ ያለውን ሁኔታ ስለሚያውቁ ሥራውን ለመቀበል አመነቱ።

በዚህ መሐል አቶ ሐኪም ወርቅነህ ራሳቸው ለሰዎች ያበደሩትን ገንዘብ ከባለዕዳዎቹ መሰብሰብ አስቸገራቸው። በአንጻሩ ደግሞ ለዩብዶ ማዕድን ማስፋፊያ ከንጉሠ ነገሥቱ የተበደሩትን ገንዘብ መክፈል ነበረባቸው። ሐኪም ወርቅነህ ወዲያ ወዲህ ብለው ከብድር ገንዘቡ ላይ የተወሰነውን ለመክፈል ቻሉ። ቀሪውን ገንዘብ ሌላ ጊዜ እንዲከፍሉ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ፈቀዱላቸው ለጊዜውም ቢሆን የዕዳው ውጥረት ተቀነሰላቸው። እንደሚታወቀው ፈረንጆች በአፍሪካ ቀንድ የቅኝ ግዛት ፍለጋ በመጡበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ግዛት ቆርሰው በመያዝ፣የፈረንሳይ፣የእንግሊዝ፣የጣሊያን ሶማሊላንድ እያሉ በመሰየም መሬቱን ተቀራመቱ። ጣሊያኖች ሞቃዲሾ፣እንግሊዞች በርበራ፣ፈረንሳዮች ጅቡቲ ውስጥ፣የሶማሌ ላንድ የቅኝ ግዛት መምሪያ ቢሮ አቋቁመው ጦር አሰፈሩ። ኢትዮጵያ በበኩሏ ጅጅጋን ከተማ፣ከጅቡቲ ፪፻ ኪሎሜትር ያህል ገባ ባለ ቦታ ደግሞ የጠረፍ መቆጣጠሪያ ወልወል የሚባል መንደር መሰረተች። የሶማሌ ሕዝብ ከብት አርቢ በመሆኑ፣ኑሮቸው የዘላን ነው። አገሩ በረሃማ ሰፊ በመሆኑ፣ግጦሽና ውሀ ፍለጋ ከቦታ ቦታ መዘዋወር ግድ ነው። በዚህ ምክንያት ለከብት መኖ ፍለጋ ሲዘዋወሩ፣የአንዱ አገር ሶማሌ፣ከሌላው ክልል ከሚመጣው ሶማሌ ጋር ግጭት ይፈጠር ነበር። ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ለማድረግ ታስቦ፣በቅኝ ገዥዎች በተያዘውና በኢትዮጵያ ስር የሚገኘውን የሶማሌ አስተዳደር ወሰን ለማካለል መሐንዲሶችና የሕዝቡን ደህንነት የሚጠብቅ ዘብ አብሮ ተላከ። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ወልወል ሲደርሱ ጣሊያኖች ጠብ በማንሳታቸው ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጎበ፣ባላምባራስ አበበ ደስታ እና ሌሎች በርካታ ሰዎች ተገደሉ።



ሐኪም ወርቅነህ ከብላታ ደሬሳ ጋር በስልክ ሲነጋገሩ

ከዚያም ጣሊያኖቹ ይብስ ብለው "ለምቻችንን ኢትዮጵያ ያለ አግባብ ገድላብናለች። ለዚህም ፪ መቶ ሺሕ ብር ካሣ ከፍላን ይቅርታም ልትጠይቀን ይገባል" በማለት አጉራ ጠናኝ አሉ። ኢትዮጵያ በበኩሏ ጣሊያኖች የፈጸሙትን ግፍ የሚመረምሩ ሰዎች እንዲልክ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቤቱታ አቀረበች። እንዳሰበችውም ከዓለም ማኅበር መርማሪ ኮሚቴ ተልኮ ነገሩን ሲያጣሩ፣የኢትዮጵያ አቤቱታ እውነትን የያዘ ጥያቄ መሆኑን አረጋገጡ። ጣሊያኖች ወልወል ላይ ለፈጸሙት እኩይ ተግባር ምንም ፍርድ ሳይሰጥ፣ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ የሚል ሃሳብ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ምክር ቤት ቀረበ። ኢጣሊያም፣ እርቁን በግን አለብኝነት ሳትቀበል ቀረችና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ላይ በርካታ የጦር መሣሪያ አከማቸች።

ለዚህም እንደ ምክንያት ያቀረበችው "ኢትዮጵያ የሱማሌና የኤርትራ ቅኝ ግዛቶቼን ለመውጋት አሳብ ስላላት፣ወረራ ልትፈጽምብኝ ስለሆነ፣ግዛታችንን መከላከል ስላለብን ነው" የሚል የሐሰት ቃል ነበር። ቀጥሎም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ክልል መሣሪያ ማጓጓዝ ጀመረች። የተከዜን ወንዝ ተሻግራ ወደ መቀሌ አመራች። የጣሊያን ጦርነት አሜሪካንነት ያሰጋት ኢትዮጵያ፣ነፃነቷን ለማስጠበቅ መሣሪያ ለመግዛት ስትጠይቅ አብዛኛዎቹ የአውሮፓ መንግሥታት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀሩ።

እንግሊዝና ፈረንሳይ ደግሞ በእነሱ ግዛት በኩል የጦር መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ማዕቀብ ጣሉ። እንዲሁም ቼኮስሎቫኪያ፣ቤልጂየምና ዴንማርክ ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር መሣሪያ ለመሸጥ የተስማሙበትን ውል አፈረሱ። ይብስ ብለው ደግሞ፣እንግሊዞች በሚቆጣጠሩት ስዌዝ ካናል (ቦርፅ) በኩል፣ጣሊያኖች ወታደሮች እና መሣሪያ፣ወደ ምፅዋ እና ሞቃዲሹ ያለ ማቋረጥ እንዲያጓጉዙ ፈቀዱላቸው። ኢትዮጵያ መሣሪያ ገዝታ ነጻነቷን ለማስከበር ከጠላቶቿ ጋር እንዳትዋጋ አብዛኛው የአውሮፓ መንግሥታት እንቅፋት ሆኑባት። በኢትዮጵያ ላይ ስለተፈፀመው ደባ፣ከፍ ብዬ የገለጥሁትን ዊልፍሬድ ቴሲገር "የሕይወቴ ምርጫ" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ እንደዚህ ብሎ ጽፏል።

> Britain and France now banned the passage of arms to Abyssinia through their territories; Belgium, Czechoslovakia and Denmark cancelled orders for arms from the Abyssinian Government. The British controlled Suez Canal, through which the Italian troops and weapons were constantly passing on their way to Massawa and Mogadishu.

ጣሊያን፣አይሮፕላን፣ታንክ፣ቦምብ፣የመርዝ ጋዝ ጢስ፣መድፍ፣መትረየስ እና ጠመንጃ ሌት ተቀን የምታመርትበት የመሣሪያ ፋብሪካዎች አላት።
ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ የማታመርተው ኢትዮጵያ ግን፣መሣሪያ ገዝታ ወደ አገሯ እንዳታስገባ የማገድና የመጓጓዝ ማዕቀብ ተጥሎባታል። የነበራት መሣሪያ ጎራዴ፣ጋሻ፣ ጦርና አሮጌ ጠመንጃ ብቻ ነበር።



ሌላው እንኳን ቢቀር በዓለም ውስጥ ሰላም ለማስፈን የተቋቋመው የዓለም ማኅበር፣ጣሊያኖች ያጓጉዙ የነበረውን የጦር ኃይል በስዌዝ ካናል በኩል እንዳያሳልፉ ለእንግሊዝ መንግሥት መንገር ሲገባው ምንም ሳያደርግ ቀረ።
ጣሊያን አገራችንን ለመውረር መነሳቷ እርግጥ መሆኑ ሲረጋገጥ "ለአንድ አስቸኳይ ጉዳይ ይፈለጋሉና ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ" በማለት ጃንሆይ ስልክ ደውለው ለሐኪም ወርቅነህ ነገሯቸው።

## በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያ አምባሳደር

አፄ ኃይለ ሥላሴን እና አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን፣እርስ በእርስ የሚያቀራርባቸው የሥራ ግንኙነት፣እንደ ማግኔጥ (magnet) ከፍተኛ የመሳሳብ ኃይል አለው። ሁለቱም ለአገራቸው በጎ ያስባሉ። ሁለቱም፣ሕዝቡ በቶሎ ወደ ሥልጣኔ እንዲገሰግስ ጽኑ ፍላጎት አላቸው። ይህ እንዲሰምር፣ከፍተኛ ዕውቀት፣ብዙ የሥራ ልምድ፣የበሰለ አስተያየት እና ቅንነት ያላቸው ሐኪም ወርቅነህ፣ለጃንሆይ ራዕይ መሳካት በጣም ጠቃሚ ሰው ሆነዋል። ጃንሆይ በየጊዜው አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን በርካታ ሥራ ሲያዟቸው፣ኃላፊነቱን እየተቀበሉ በአርኪ ሁኔታ እየሠሩ መልካም ውጤት አሳይተዋል። በየጊዜው ችግር ሲፈጠር፣በቀይታ ይነጋገራሉ። አንዳንድ ጊዜ የሃሳብ ግጭት ቢፈጠር እንኳን፣ሁለቱም እርስ በርስ ተከራክረው ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ። ከዚህ አኳያ ሲታይ፣ወደ አዲስ አበባ በቶሎ እንዲመጡ የጠሯቸው ሌላ ከባድ ጉዳይ ቢኖር መሆኑን መገመት አያዳግትም።
አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጥሪው በደረሳቸው በሁለተኛው ቀን፣ከአሰበ ተፈሪ ተነስተው አዲስ አበባ ገቡ። ከዚያም ቤተ መንግሥት ሲደርሱ፣እጋፋሪዎቹ ከደጅ ተቀብለው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አሉበት ክፍል አስገቧቸው። አዛዥ ወርቅነህ ገብተው ከጃንሆይ ፊት፣ከጠረጴዛው ትንሽ ራቅ ብለው ቆሙ። ጃንሆይ በእጅጉ ተክዘው እና በቀኝ እጃቸው የያዙትን እርሳስ ጠረጴዛቸው ላይ እየቆረቆሩ ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ድንገት ቀና ሲሉ፣ሐኪም ወርቅነህን ስለ አይዋቸው፣ከመቀመጫቸው ተነስተው እንኳን ደህና መጡ አሉና ከጠረጴዛቸው ፊት ለፊት ወዳለው ወንበር እየጠቆሙ ይቀመጡ አሏቸው። ሁለቱ ሲነጋገሩ ሐኪም ወርቅነህ በዕድሜያቸው፣ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ ንጉሠ ነገሥት በመሆናቸው፣ተገቢውን የአክብሮት ቃል በመጠቀም እርስዎ-ሌና አንቱ ይባባሉ እንደነበረ እዚህ መግለጡ ተገቢ ይሆናል። ንጉሠ ነገሥቱ ሆምጨጭ ብሎ የነበረውን ፊታቸው ፈካ አድርገው ስለ ሐኪም ወርቅነህ ጉዞ ለጥቂት ደቂቃ አነጋገሯቸው። በዚህ መሐል ቀደም ሲል የኢሉባቦር ገዢ አድርገው ሊሾሟቸው አስበው እንደ ነበረ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ትዝ አላቸውና አሁን የተጠሩት ለዚህ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው። ነገሩ ግን እሳቸው እንደ ጠረጠሩት አልሆነም።
ጃንሆይ ስለ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጉዞና አሰበ ተፈሪ ሁኔታ ጠይቀዋቸው ተገቢውን መልስ ካገኙ በኋላ፣አሁን ለምን እንደጠሯቸው ከመንገራቸው በፊት የሚኒስትርነት (የአምባሰደርነት) ልብስ ተሰጣቸው። በዚህን ጊዜ ነበር ሐኪም ወርቅነህ የተጠሩት እሳቸው እንደጠረጠሩት ለአገረ ገዥነት ሳይሆን በጣም ለየት ያለ ሥራ መሆኑን የተረዱት።

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በአስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ያደረጋቸው ከባድ የአገር ጉዳይ በመሆኑ፣የንጉሥ ክብደት ምን ያህል እንደሆነ ለማስረዳት አስበው ንጉሠ ነገሥቱ የሚከተለውን ነገሯቸው።


> ጣሊያኖች በውጋዴን በኩል ድምበራችንን አልፈው፣በጠረፍ ጠባቂዎቻችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸውን እርስዎም ያውቃሉ። አሁን ደግሞ በሰሜን በኩል፣የአገራችንን ድምበር ጥሰው ወደ መቀሌ እየገሰገሱ ነው ተብሏል። ስለዚህ ይህን በደል፣ለዓለም ሕዝብ እንዲያሳውቁ ወደ ለንደን እንዲሄዱ እንፈልጋለን። ለዚህም በእንግሊዝ አገር፣የኢትዮጵያ ሚኒስትር እና ባለ ሙሉ ሥልጣን አድርገን ሾመንዎታል።

ይህን ከተናገሩ በኋላ "ምን ይመስልዎታል?" ብለው አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን ጠየቋቸው። አነጋገራቸው የትዕዛዝ ሳይሆን የመመካከር ዓይነት ነበር። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የሚመልሱት ነገር ግራ ስለ ገባቸው ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብለው ቆዩ። በጉዳዩ እጅግ ካሰቡበት በኋላ "ግርማዊ ሆይ፣እኔ የሕክምና ባለሙያ እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም። ይህን የመሰለ ኃላፊነት መቀበል እጅግ ይከብደኛል፣ይከብደኛልም እና ሌላ ሰው ቢመደብ የሚሻል ይመስለኛል" የሚል መልስ ሰጡ። ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው፣እሳቸውን አግባብተው ሹመቱን እንዲቀበሉ ለማድረግ ዝግ ባለ ድምፅ የሚከተለውን ተናገሩ።

> በዚህ ቦታ መሥራት ያለብዎ እርስዎ ነዎት። ከእንግሊዞች ጋር አብረው ኖረዋል፣ቋንቋቸውን አቀላጥፈው ይናገራሉ፣ከዚህም ሌላ ደግሞ ወግ እና ሥርዓታቸውን እና ጠባያቸውን አበጥረው ያውቃሉ።
>
> እንደሰማሁት ከሆነ ከወርቅታ ታላላቅ የእንግሊዝ ሹማምንቶች ጋር ጥሩ ወዳጅነት አለዎ። በዚህ ተቀጠሮ ለዓት፣የኢትዮጵያን በደል ለዓለም ሕዝብና ለታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ሊያስረዳ የሚችል ሰው ከእርስዎ ሌላ ከወዴት እናገኛለን? ስለዚህ፣ለዚህ አንገብጋቢ የአገር ጉዳይ በሙሉ ወደ ሥራዎ መሄድ አለብዎ በማለት፣ትዕዛዝ ሳይሆን ጥያቄውን አስረግጠው ነገሯቸው።

በዚያን ዘመን ከምዕራብ አውሮፓ ሰዎች ጋር እኩል ቀጥ መነጋገር እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የኢትዮጵያን አቋምና ፍላጎት ለማስረዳት የሚችሉ፣ውጭ አገር አድገውና ተምረው፣አገራቸውን ለማገልገል ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጡት፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ንጉሠ ነገሥቱ ለአለበት ተልዕኮ ብቁ ናቸው የሚል እምነት በንጉሠ ነገሥቱ አእምሮ ውስጥ ተቀርጾ ነበር። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያ አምባሳደር አድርገው ለመሾም የወሰኑትም ለዚህ ነው። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ከተቀመጡበት ተነስተው "እሺ የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ" በማለት እጅ ነስተው ሹመቱን የተቀበሉት፣የንጉሠ ነገሥቱ አነጋገርና በወቅቱ የተከሰተው የጦርነት አደጋ በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ አስጊ ሁኔታ ስለሚያስከትል ነው። ያ ወር፣ከወይዘሮ ቀጸላ ቱሉ ጋር በስምምነት ተለያይተው (ተፋትተው) የነበሩበት ጊዜ ነበር።





አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በአምባሳደር ማዕረግ ልብስ

ቢሆንም አዲስ አበባ አራዳ ከሚገኙ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ገና አልገቡም ነበር። አሁን ግን ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ስለመጡ፣መሐል አራዳ ከሚገኘው፣ቴዎድሮስ እና ሳሙኤል (ቻርሊ) ወርቅነህ በዚያን ጊዜ ይኖሩበት ከነበረው ቤታቸው ውስጥ ለመኖር ወሰኑ።



አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በአምባሳደር ማዕረግ ልብስ

ከቤተ መንግሥት እንደ ተመለሱ፣ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተለዋወጡትን ሃሳብና እንግሊዝ አገር ምኒስትር ሆነው እንዲሄዱ በንጉሠ ነገሥቱ መሾማቸውን ለልጆቻቸው ከነገሩ በኋላ ወደ አሰበ ተፈሪ ሄደው የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቻቸውን ለመሰናበት እንደሚፈልጉ ገለጹላቸው። እሳቸው ወደ አሰበ ተፈሪ ሄደው እስኪመለሱ ድረስ፣ለመንገድ አስፈላጊ የሆኑትን አንዳንድ ነገሮች ቤተሰቡ አዘጋጅቶ እንዲጠብቋቸው መመሪያ ሰጡ። ይህን ካደረጉ በኋላ ወደ አሰበ ተፈሪ ሄዱ። አሰበ ተፈሪ እንደ ደረሱ፣የሥራ አጋሮቻቸውን ሰብስበው እሳቸው ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄዱ መሆናቸውን ነገሯቸው። በሁለንተናው መንገድ የቅርብ ወዳጆቻቸው እና ረዳቶቻቸው የነበሩ ሁሉ ከእሳቸው በመለየታቸው እጅግ አዘኑ። በሐኪም ወርቅነህ ፈንታ የተተካ ሰው ባለመኖሩ፣ሌላ ሰው እስኪሾም ድረስ ምክትላቸው እና አማቻቸው የሆኑትን አቶ ሰይፈ ሚካኤልን ለጊዜው ወከሏቸው። ከዚያም የሥራ ባልደረቦቻቸውንና ተማሪዎቻቸውን ተሰናብተው፣ለአውራጃው ዕድገት ደፋ፣ቀና ብለው ያቀኑትን የጨርጨር አወራጃ ለቅቀው በታላቅ ኀዘን እና ቅሬታ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ለሰው ልጅ ቅን አሳቢ ሰው በመሆናቸው፣ለአገራቸው ይበጃል፣ይጠቅማል የሚሉትን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ ብለው አያውቁም። የቅርብ ረዳቶቻቸው አቶ ሰይፈ ሚካኤል፣አቶ አማኑኤል አብርሃም፣አቶ ዘውዴ ገብረ ሕይወት እና የሌሎቹም የሥራ ባልደረቦቻቸው ቅን ድጋፍ እና እርዳታም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ነበረው። ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን በእንደራሴነት ሲመሩ፣አቶ አማኑኤል አብርሃም እዚያ ይማሩ ነበር። ትምህርታቸውን እንደ ጨረሱ፣ሥራ ለማግኘት ብዙ ከተንከራተቱ በኋላ፣ወደ አሰበ ተፈሪ ለመምጣት የቻሉት በሐኪም ወርቅነህ ፈቃድ ነው። አቶ አማኑኤል አሰበ ተፈሪ እንደ ደረሱ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ቤት እየኖሩ፣በልዩ ፀሐፊነት፣በዲሬክተርነትና በአስተማሪነት ሠርተዋል። ወጣቱ አማኑኤል ከእሳቸው ጋር በሠሩበት ጊዜ በአሳዩት ሥራ ወዳድነት፣ጨዋነት እና የመማር ፍላጎት በቅርብ ያውቋቸው ስለ ነበረ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ ሎንዶን ይዘዋቸው ለመሄድ ወሰኑ።

ወዲያው "ለሥራ ወደ እንግሊዝ አገር መሄዴ ስለሆነ፣እንደ ተማሪዬ ሆነህ በጽሕፈት ሥራ እንድተረዳኝ፣ያለ ደሞዝ ልወስድህ አስቢያለሁ እና የምትፈልግ እንደሆን አስታውቀኝ በማለት ሚያዚያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የተጻፈ ደብዳቤ ለአቶ አማኑኤል ላኩ። አቶ አማኑኤል አብርሃም በበኩላቸው፣ይህን የመሰለ የመማር ዕድል ስላገኙ በጣም ተደስተው "ዕውቀቴ እንዲሰፋልኝ እና ለኋላ ሥራዬ እንዲረዳኝ ስላሰቡልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። የዕለት ምግቤንና ልብሴን ካገኘሁ ምንም ደመወዝ አልፈልግ ጌታዬ ወደሚሄዱበት ተከትዬ ለመሄድና በትንሿ አቅሜ ክቡርነትዎን ለመርዳት ዝግጁ መሆኔን አረጋግጥልዎታለሁ" በማለት መልሱን ለአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በደብዳቤ ላኩላቸው። አቶ አማኑኤል የሕይወቴ ትዝታ በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ይህን ደብዳቤ ለአለቃቸው የጻፉበትን ምክንያት ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል፡፡፡



> አሰበ ተፈሪ ትምህርት ቤት አስተማሪም፣አስተዳዳሪም በመሆን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ከሠራሁ በኋላ፣በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በሚያዚያ ወር በፍጹም ያላሰብሁት ሌላ መልካም ዕድል አጋጠመኝ። እሱም፣በኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት ባለሥልጣን ሁለት ጊዜ ተነፍጌ የነበረውን፣ወደ ውጪ አገር ሄጀ ተጨማሪ ዕውቀትን የመገብየት ዕድል ማግኘቴ ነበር። በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የአገሪቱ የዲፕሎማሲ ሥራ ገና በዘመናዊ መንገድ ያልተቋቋመ ስለነበረ፣ በሥራው የሠለጠኑ ሠራተኞች አልነበሩም። ለዚህ ሥራ ይደረግ የነበረ ውጭም እጅግ መጠነኛ ነበር። ስለዚህ፣ወደ ውጭ አገር የሚላክ ባለሙሉ ሥልጣን ምኒስትር ወይም ቆንሲል፣በጸሐፊነት እንዲረዳው የመሰለውን ሰው መርጦ ይዞ እንዲሄድ ይፈቀድለት ነበር። ይህን የሚያውቁ አንዳንድ ወጣቶች፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ይዘዋቸው እንዲሄዱ ለጠየቋቸው ሰዎች እኔ የመረጥሁት ሌላ ልጅ አለ፣ብለው መለሷቸው።

ለሐኪም ወርቅነህ ሥራ መሳካት ደግሞ እንደ አቶ ሰይፈ ሚካኤል፣አቶ ዘውዴ ገብረ ሕይወት እና አቶ አማኑኤል አብርሃምን የመሰሉ ቅን ረዳቶች ነበሯቸው። ረዳት ከነበሩት ከሦስቱ አንዱን ብቻ በግድ መምረጥ ነበረባቸው። እሳቸው የመረጡት አማቻቸው፣አቶ ሰይፈ ሚካኤልን ወይም ትጉ ሠራተኛ የሚባሉትን አቶ ዘውዴ ገብረ ሕይወትን አልነበረም። ወደ እንግሊዝ አገር ከእሳቸው ጋር እንዲሄድ የመረጡት አቶ አማኑኤል አብርሃምን ሆነ። ለምን? ቢባል፣መልሱ ሦስት ምክንያቶች ነበራቸው የሚል ይሆናል።

<u>አንደኛው ምክንያት፡-</u> አቶ አማኑኤል አብርሃም፣ከእሳቸው ጋር ብዙ ጊዜ በመሥራታቸው እና በቂ ልምድ ያገኙ በመሆናቸው

<u>ሁለተኛው ምክንያት፡-</u> ያለደሞዝ በተማሪነት ለመሥራት በመስማማታቸው

<u>ሦስተኛው ምክንያት፡-</u> ወጣትና ትዳር ያልያዙ በመሆናቸው፣ዕውቀት ለማግኘትና ልምድ ለማካበት ከፍተኛ ጉጉት በማሳየታቸው

ይህንንም አቶ አማኑኤል በማጠቃለል እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> በአዛዥ ወርቅነህ መሪነትና አስተማሪነት ከሦስት ዓመት በላይ እንደዚህ ከሠራሁ በኋላ፣በትምህርት ቤት ሥራ ብቻ ሳይሆን በጽሕፈት ሥራም ብዙ ልምድ አገኘሁ። እሳቸው በአጻጻፍ ረገድ ጠንቃቃ ስለ ነበሩ፣እኔም ይህን የአሠራር ጠባይ እንድቀስም ያሰቡበት ይመስለኛል። ወደ ብሪታንያ የመሄዳችን አሳብ ከመነሳቱም አስቀድሞ የሚሰጡኝን ትምህርት በደስታ የምቀበል እና በጥንቃቄ የምከተል መሆኔን እንደተመለከቱ ይሰማኛል። ወደ ሌላ ስፍራ ሲሄዱ እንዳልለያቸው ያሰቡበት አንዱ ምክንያት መሆኑንም እምናለሁ።

በመቀጠልም፣አቶ አማኑኤል ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጋር ተገናኝተው ለረጅም ጊዜ አብረው በመሥራታቸው ያገኙትን ጥቅም እንደሚከተለው ጽፈውታል።

ክቡር አዛዥ ወርቅነህ እሸቴ (ዶክተር ቻርልስ ማርቲን) ያስተማሩኝን እና ያደረጉልኝ በጎ ነገር ሁሉ፣በምስጋና እንዳስባቸው እንዳደረገኝ፣አገርንና ወገንን የማገልገል ዕድል ባገኘሁትም ረጅም ዘመን ሁሉ፣እንደ ፋና ሆኖ ሥራዬን እንድመራ የረዳኝ መሆኑን ይህን ጽሁፍ ለሚመለከቱ ሁሉ መግለጥ እወዳለሁ። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ትውልዱ ከዚህ አውራጃ ነው ከዚያ ነው ሳይሉ፣ለብዙ ኢትዮጵያውያን ይሰጡት የነበረው ድጋፍ እና እርዳታ፣ያሳዩ የነበረው የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት አርዓያም፣እስከ ዘመኔ መጨረሻ በልቤ ውስጥ ይኖራል።

ይህን የመሰለ ሀቀኝነት የሞላው ምስክርነት ስለ ሐኪም ወርቅነህ የሰጡ ሰው ወደፊትም አብረዋቸው እንዲሠሩ ቢመርጧቸው ምን ያስደንቃል? አቶ አማኑኤል አብርሃም አዲስ ያገኙትን ውጭ አገር የመሄድ ዕድል ለመጠቀም የሚያስችለውን ፓስፖርት ለማውጣት ወደ አዲስ አበባ ሄደው፣ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ቤት አረፉ። በጥቂት ቀናት ውስጥ ፓስፖርታቸውን እጃቸው ካስገቡ በኋላ የሥራ ባልደረቦቻቸውን ለመሰናበት እና በእጃቸው ያለውን የትምህርት ቤቱን ንብረት ለማስረከብ ወደ አሰበ ተፈሪ ተመለሱ። እዚያ እንደ ደረሱ የትምህርት ቤቱን ወጪ እና ገቢ የሚያሳዩትን መዝገቦች አስፈተሹ። መዝገቡ ተፈትሾ፣ምንም የገንዘብ ጉደለት ወይም የአሠራር ስህተት ስላልተገኘ አቶ አብርሃም ከተጠያቂነት ነፃ የወጡ ለመሆናቸው ማረጋገጫ በመዝገብ ላይ ተጽፎ፣ከምክትል አስተዳዳሪው ከአቶ ሰይፈ ሚካኤል እና ከሌሎቹም የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ተሰነባበቱ።

እንዲሁም በስፍራው ከነበሩት ተማሪዎችም ጋር ሲሰነባበቱ መላቀሳቸውን አቶ አብርሃም ጽፈውታል። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ አራት ትናንሽ ልጆቻቸውን፣የእህታቸውን ልጅ ቦጋለን፣የልጆቹን ሞግዚትና አንዲት ወጥቤት አስከትለው ከአዲስ አበባ ተነስተው ድሬዳዋ ገብተው ነበር። አቶ አብርሃም በበኩላቸው ከአሰበ ተፈሪ ተነስተው ወደ መዔሶ ሄደው ባቡር ተሳፈሩ። ምሽቱ ላይ ድሬዳዋ ገብተው ሐኪም ወርቅነህ ወደ አረፉበት ባሎላኮስ ሆቴል ሄዱ። ሐኪም ወርቅነህን አግኝተው እጅ ከነሱ በኋላ መኝታ ቢጠይቁ፣አልጋ እንደሌለ እና ክፍሎቹ በሙሉ መያዛቸው ተነገራቸው። ረጅሙ ጉዞ አድክሟቸው ስለነበር ሌላ አማራጭ ሲያጡ ሁለት ወንበሮች አጋጥመው እዚያ ተኝተው አደሩ። በማግስቱ ሰኔ ፲፯ ቀን ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ተኩል ላይ የሐኪም ወርቅነህ ቤተሰብና አቶ አማኑኤል አብርሃም ከድሬዳዋ ተነስተው ጉዟቸውን ጀመሩ እና ከሰዓት በኋላ ፲፩ ሰዓት ላይ ጅቡቲ ገብተው አደሩ።

ሰኔ ፲፯ ቀን በአምስት ሰዓት ዳርታኛን (D'artagnan) በሚባል መርከብ ተሳፍረው ሰኔ ፳፪ ቀን ጧት ፲፱፻፳፮ ዓ.ም. ፖርትሳይድ ደረሱ። መርከቡ ጉዞውን የሚቀጥለው ከሰዓት በኋላ በአሥር ሰዓት ስለ ነበረ አቶ አማኑኤል ወደ ኢትዮጵያ ቆንሲል ቢሮ ሂደው ከአቶ ይልማ ወልደ ገብርኤል ጋር ሲገናኙ ከአዲስ አበባ ያመጡላቸውን ደብዳቤ ሰጧቸው። አቶ አማኑኤል ቆንሲሉን ይዘዋቸው መጡና ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጋር አገናኟቸው። መርከቡ ከፖርት ሰይድ ወደብ እስኪነሳ ድረስ ስለ አገር ጉዳይ እና ስለ ሌሎችም ሁኔታዎች በሰፊው ተጫወቱ።

ከዚያ የሁሉም ዕቃ ወደ ባቡር ተጫውሮ ጉዟቸውን ቀጠሉና ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ፓሪስ ገብተው ሆቴል ደላጋር ዱ ኖር (Hotel de L'agar du Nord) አረፉ። መንገዳቸውን የሚቀጥሉበት ሰዓት ስለ ደረሰ ከአቶ ይልማ ወልደ ገብርኤል ጋር ተሰነባብተው መርከቡ ላይ ተሳፈሩ። መርከቡ አራት ቀን ከተጓዘ በኋላ ሰኔ ፳፯ ቀን ማርሴይ ገባ። እዚያ የአንድ ቀን አዳር አድርገው ሰኔ ፳፰ ቀን ወደ ፓሪስ ሄደው ከምኒስትር ተክለ ሐዋርያት ጋር ተገናኙ። ሐኪም ወርቅነህ እንግሊዝ አገር የሌጋሲዮን ኃላፊ እና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሆነው በምኒስትርነት ማዕረግ የሚሄዱ መሆናቸውንና ስለ ጊዜው ሁኔታ ከተጫወቱ በኋላ፣ዕቃዎቻቸው በባቡር ላይ ተጭኖ፣ወደ ካሌ (Calais) ወደብ ጉዞ ተጀመረ። ካሌ ሲደርሱ፣ዕቃቸው ባቡር ውስጥ እንዳለ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህና ጓዛቸው በመርከብ ተሳፍረው ሌሊቱን በመጓዝ፣የእንግሊዝ ቻኔልን (English Channel) አቋርጠው ዶቨር (Dover) ከሚባለው ወደብ ደረሱ። ከዚያ ዕቃቸው በተጫነበት ባቡር ተሳፍረው ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ.ም. ሎንዶን ገቡ። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እንግሊዝ አገር ተሾመው እስከ መጡበት ቀን ድረስ፣ሚኒስትር ተክለ ሐዋርያት መቀመጫቸው ፓሪስ ሆኖ፣በእንግሊዝ አገር ምኒስትር እና ጄኔቭ በሚገኘው የመንግሥታት ማኅበር የኢትዮጵያ እንደራሴም ነበሩ።

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ሎንዶን በገቡ ጥቂት ቀናት ውስጥ፣ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ (Foreign Office) ሄደው ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለሥልጣን ጋር ተነጋግረው የሹመት ደብዳቤውን ለንጉሡ ለመስጠት ቀጠሮ አስያዙ። እዚያም የውጭ ጉዳይ ቢሮ ዋና በሐፊ፣ሰር ሳሙኤል ሆር (Sir Samuel Hoare) እና ለኢትዮጵያና ግብፅ ጉዳይ ኃላፊ ከሆነው ሹም፣ከሚስተር አር. ኪው. ካምቤል (Mr. R.Q. Campbell) ጋር ከተገናኙ በኋላ፣ለመደራደር አገናኝ መቀየን ሆኖ ከሚሠራ፣ከሌላ ሰው ጋር አስተዋወቋቸው። ከዚያ በኋላ ይፋ የሆነ የዲፕሎማቲክ ሥራቸውን ጀመሩ። ከሥራቸው አንዱ ኢትዮጵያ ራሷን ከጠላት ለመከላከል የሚያስችል መሣሪያ ለመግዛት ማፈላለግ ነበር።
ለምኒስትር ሐኪም ወርቅነህ ለየት ያለ ታላቅ አክብሮት የሰጧቸው ሚኒስተር ሃንከክ ከጥቂት ቀን በኋላ እቤታቸው የራት ግብዣ አደረጉላቸው። በእራት ግብዣው ላይ ሚሲዮኔር ከሆኑት ሚስስ ፍራንሲስ ፊሸር (Mrs. Francis Fisher) ጋርም አስተዋወቋቸው። ሚስስ ፊሸር ቀደም ሲል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩ እና ለአገሪቷም ብዙ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ እመቤት ናቸው። እሳቸው ቀደም ሲል ጀምሮ ከኢትዮጵያ ሚሲዮን ለመሾም ጉጉት ነበራቸው ይባላል። ኢትዮጵያ ችግር እንደ ሲጋጠማት ሲሰሙ እንኳን ለኢትዮጵያ ያላቸው መልካም አስተያየት አልተለወጠም። እኚህ ወይዘሮ ስለ ኢትዮጵያ አንድ መጽሐፍ አዘጋጅተው ስለ ነበረ ለአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ አንድ ቅጂ ሰጧቸው። ይህን ያደረጉበት ምክንያት ምኒስትሩ ስለ መጽሐፉ አስተያየት እንዲጽፉላቸው ነው። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ መጽሐፉን አንብበው ስለ ወደዱት ይመስላል፣ጥሩ መግቢያ ጻፉላቸው። በኢትዮጵያ ምኒስትር ለመጽሐፉ መግቢያ እንዲሆን የተሰጠው ምስክርነት፣ደራሲዋ ልዕልት ለመሆናቸው ዕውቅና የሰጠ እና መጽሐፉንም እውነተኛ ታሪክ አስመሰለው። በዚህም ምክንያት ለመጽሐፉ መሸጥ ትልቅ እገዛ አደረገ።

የመጽሐፉ ይዘት ትክክል ዘገባ የሌለው መሆኑን አንዳንድ ሰዎች ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ነግረዋቸው ነበር እና ምኒስትሩ ለዚህ ትክክለኛ ላልሆነ መጽሐፍ ድጋፍ ስለ ሰጡ፣ጃንሆይን በእጅጉ ቅር አሰኙ። ይሁን እንጂ የመጽሐፉ መሸጥ አልተቋረጠም። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ እንግሊዝ ቤተ መንግሥት ገና አልሄዱም ነበር። ስለዚህ ቀደም ሲል የሌጋሲዮኑ ጸሐፊ የነበሩት አቶ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን፣ወደ እንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሄደው፣ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የሹመት ደብዳቤውን እንዲያቀርቡ ከባለ ሥልጣኖቹ ጋር ቀጠሮ አስያዙላቸው። በዚህ መሐከል በርካታ የቀድሞ ወዳጆቻቸው እየመጡ ሐኪም ወርቅነህን ማነጋገር ጀመሩ። የምኒስትር ሐኪም ወርቅነህ ወዳጅ ከነበሩት እና አሁን ሊያይዋቸው ከመጡት መሐከል አንዱ ሚስተር ቫዮሌት ክሬሲ—ማርክስ (Mr. Violet Cressy--Marcks) ናቸው። እሳቸውም ልክ እንደ ሚስተር ሃንኮክ እቤታቸው ጋብዘዋቸው፣ስለ ኢትዮጵያ የወቅቱ ሁኔታ ሲጨዋወቱ፣በሚችሉት መንገድ ሁሉ ለመርዳት ጽኑ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ነገሯቸው። በዚያው ሰሞን የምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የቀድሞ ወዳጅ የሚስተር ዛፊሮ ሚስት የእንጀራ ልጃቸውን በመወከል፣እጅ ለመንሳት መጡ። ሚስተር ዛፊሮ፣አዲስ አበባ ውስጥ የእንግሊዝ ሌጋሲዮን የምሥራቅ አገሮች ፀሐፊ ሁኖ የሚሠራ እና ንጉሠ ነገሥቱ አውሮፓን ሲጎበኙ አብሮ የነበረ ሰው ነው። ሐኪም ወርቅነህ አዲስ አበባ በሚገኘው የእንግሊዝ ሌጋሲዮን ሐኪም ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ሐኪም ወርቅነህን ያውቋቸዋል።

ዛፊሮ ከኢትዮጵያዊት ሚስቱ አንድ ልጅ ሲወልድ ተስፋዬ (ሬጂናልድ) የሚል ስም አውጥሎታል። ሬጂናልድ በልጅነቱ ወደ እንግሊዝ አገር መጥቶ ከፍተኛ ትምህርት የተማረው፣ፒትስበሮ (Pitsborough) በሚገኘው ኪንግስ ኮሌጅና ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ነው። ሬጂናልድ ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ይማር በነበረበት ጊዜ የሮድስ ሽልማት (Rhodes Scholarship) አግኝቶ ለአንድ ዓመት ወደ አሜሪካን አገር ሂዶ ተምሯል። በዚያው ሰሞን ወደ ኢትዮጵያ ሌጋሲዮን እየመጡ የገንዘብ እና የሞራል ድጋፍ ለመስጠት ቃል ይገቡ የነበሩት ሰዎች ቁጥር ብዙ ነበር። በዚህ መሐል፣የሚስስ ሆላንድ ወንድም፣ሚስተር ፍሬድሪክ ዎልድማየር (Mr. Frederik Waldemier) የቺኮ ጦርነት (Chico War) ሲያልቅ መሣሪያ እንደሚረክስ ተናገሩ። መሣሪያው ተገኝቶ ለመግዛት ሲዘጋጁ፣ጠመንጃ እና ጥይት ከአገር የማስወጫ ፈቃድ ማግኘት አስቸጋሪ ሆነባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ሌጋሲዮኑ የሚመጣው ሰው በየቀኑ እየተበራከተ ሄደ። በየቀኑ የሚመጣው እንግዳና የጋዜጠኞች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ሌጋሲዮኑ ያለበት ሕንፃ፣ለምኒስትሩ መኖሪያና በቢሮነትም ጭምር የሚያገለግል ስለ ነበረ ከምንጊዜውም የበለጠ የቦታ ጥበት ተከሰተ። የቤቱ መጥበብ ሚኒስትር ሐኪም ወርቅነህን በእጅጉ አሳሰባቸው። በዚህ ምክንያት ተለቅ ያለ እና ብዙ ክፍሎች ያሉት ቤት ማፈላለግ ጀመሩ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሃይድ ፓርክ (Hyde Park) ፊት ለፊት ፕሪንስስ ጌት (Princess Gate) መንገድ ላይ የሚገኘውን ሕንፃ ስለ ወደዱት፣ከሁለት ቀን በኋላ ገዙት።



ይህ ጥሩ ሕንፃ የተገዛበት ፯ ሺሕ ፓውንድ፣ከዛሬው ዋጋ ጋር ስናስተያየው ለላቅ (ቀልድ) እንጂ እውነት አይመስልም። በማግስቱ የቤት ግዢውን ውል አፀኑት። በፕሪንስስ መንገድ ቁጥር ፫ ላይ የሚገኘው ይህ ቤት ከመንገድ ዳር የሚገኝ፣ምገስ ያለው ሕንፃ ሲሆን፣የምድር ቤቱን ጨምሮ፣ሕንፃው ባለ ስድስት ፎቅ ነው። በስተጀርባው፣በአካባቢው ካሉት አሥር ሕንፃዎች ጋር የሚጋራው የተንጣለለ የአትክልት ቦታ አለ። በዚህም ለሌጋሲዮኑ ሥራ እና ለሚኒስተር ሐኪም ወርቀነህ ቤተሰቦች፣እንዲሁም ለጸሐፊያቸው አቶ አማኑኤል ጭምር የሚበቁ የመኖሪያ ክፍሎች አሉ።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. የሌጋሲዮኑ ቢሮ ወደዚህ ቤት ተዛወረ። ከላይ እንደተገለጠው ግቢው የተንጣለለ የአትክልት ቦታ ስለነበረው፣የሐኪም ወርቅነህ ልጆች እየተሯሯጡ የሚቦርቁበት፣ሲያስፈልጋቸውም ግራሞፎኑን ከበረንዳው ላይ አድርገው ሙዚቃ የማዳመጥ እድል አጋጠማቸው። አንዳንድ ጊዜም ትናንሾቹ ልጆች ከሕንፃው ደረጃ ስር ተቀምጠው ይጫወቱ ነበር። አልፎ ተርፎም ወደ ሌጋሲዮኑ የሚመጡት እንግዶች ሻይ የሚጋበዙት እዚህ መናፈሻ ከሚመስለው የአትክልት ስፍራ ነበር። ለግንዛቤ እንዲረዳ በወቅቱ የተነሱትን የቤቱንና የግቢውን ሁኔታ የሚያሳይ ፎተግራፍ በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ። መሣሪያ ለመሸጥ፣ወይም ከኢትዮጵያ ጎን ሆነው ለመዋጋት ሐሳብ ለማቅረብ በርካታ ሰዎች ወደዚህ ቢሮ ይመጡ ጀመር። መሣሪያ ለመሸጥ ከሚመጡት መሐል ከአየርላንድ የመጡት አሻሻጮች ቁጥር የበዛ ነበር። ደላሎቹ እርስ በእርሳቸው እየተፎካከሩ የመሣሪያዎቹን ዓይነትና ብዛት እና ዋጋ እስከ ማቅረብ ደርሰው ነበር።

ምኒስትር ወርቅነህ ደላሎቹን በየተራ ጠርተው ሲያነጋግሯቸው፣ለጊዜው በእጃቸው ገንዘብ የሌላቸው መሆኑንና በተጨማሪም መሣሪያውን የመግዛት ምኞት ቢኖራቸውም፣ ፈቃድ የማግኘቱ ችግር የጎላ መሆኑንም ይነግሯቸው ጀመር። ደላሎቹ የክቡር ምንስትሩን ችግር ከአዳመጡ በኋላ እያዘኑ ወደየመጡበት እየተመለሱ ይሄዱ ነበር። የመሣሪያ ግዢን እና ሌሎችም ወቅታዊ ጉዳዮች በተመለከተ ስትራንድ የሚባለው መጽሔት (Strand Magazine) ጋዜጠኛ ከሆኑት ሚስተር ኤቴርቶን (Mr. Etherton) ጋር ሰፋ ያለ ቃለ ምልልስ አደረጉ። በዚህ ብቻ ሳያቆሙ፣ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ሄደው፣ለሁለተኛ ጊዜ ከሚስተር ካምቤል ጋር ስለ ወቅቱ ሁኔታ ተነጋገሩ። እንደ በፊቱ ሁሉ፣በእንግሊዞች በኩል ያለው አቋም ተስፋ ሰጪ አልነበረም። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ስለ መሣሪያ ግዢና ወደ ኢትዮጵያ የማስገባት ጉዳይ ለመነጋገር ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ቢመላለሱም ምንም የተጨበጠ መልስ ሳያገኙ ቀሩ። በሁኔታው አዝነው ወደ ቢሯቸው እንደተመለሱ፣የቀድሞ እጮኛቸው የቴዎድሮስ ወርቅነህ እናት፣ሚስስ ኤዲት (Mrs. Edith) በፊት ሚስ ፋብሪክስ መጥታ ስለ ልጃቸው ሁኔታ ተወያዩ። ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ሚስተር ቻርቶክ (Mr. Chartok) የሚባል አሜሪካዊ መሣሪያ ነጋዴ መጥቶ፣ያቤሉ ያለውን የወርቅ እና የፕላቲነም ማዕድን ኩባንያ በዋስትና ይዤ የአንድ ሚሊዮን ዶላር መሣሪያ ልሸጥልዎት አላቸው።

ነገሩ እንጂ በሆነም የስመፍው ማግኘት በትው የታወቀ ባለመሆኑ፣ ካሰቡት ሳይተባበሩት ቀሩ። ሚስተር ቻርችልም ወደ ሲጋሊያኑ የመግባት ጉዳይ ሳይሳካለት በመቅረቱ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ እንደሚመጣ ተናግሮ ጉዞ አያለው ሄደ። ቸርችል ከቢሮቸው ሲወጣ፣ እንግሊዝ ቤት ተቀምጠው ተራቸውን ይጠብቁ ከነበሩት ከክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር (Christian Science Monitor) ጋዜጣ እና እንዲሁም ከቅርብ ምሥራቅ ሕንድ አሳታሚዎች (The Near East and India Publication) ጋር ቃለ ምልልስ አደረጉ። እነሱ ከቢሮ እንደወጡ ደግሞ፣ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ፈቃድ ሊጠይቅ የመጣው ዶክተር ቶሬንስ (Dr. Torrence) ገብቶ አነጋገራቸው። እሳቸውም አስፈላጊውን የይለፍ ፈቃድ ሰጡት። በተጨማሪ ጊዜያቸው ከአሜሪካ፣ ከካሪቢያን እና ከሌሎችም አገሮች የመጡ በርካታ ሰዎች፣ አሁን በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ችግር በመስማታቸው፣ ማዘናቸውን እና ወገናዊነታቸውን (solidarity) ለመግለፅ የመጡትን ሲያነጋግሩ ከረሙ።

የኢትዮጵያ ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ በሆነበት ወቅት፣ ሲኖር ከረዮ ወደ ቢሮቸው መጥቶ በለ ፕሮፌሰር ስታንሊይ ጀቮንስ (Professor Stanley Jevons) ጉዳይ አንድ ሃሳብ (proposal) አቀረበ። ሚኒስትር ወርቅነህም "ዛሬ ከሰዓት በኋላ በውጭ ጉዳይ ቢሮ ውስጥ ከሰር ላንስሎት ኦሊፋንት ጋር (Sir Lancelot Oliphant) ተመር ለሳልና ወለሌ ጊዜ እንነጋገር" በማለት አሰናበቱት። እሱን ካሰናበቱት በኋላ ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ሄደው ከሰር ኦሊፋንት ጋር ለኢትዮጵያ በሚያስፈልገው የመሣሪያ ጉዳይ ለሁለተኛ ጊዜ ሲነጋገሩ ለአንድ ሳምንት ታግዶ የሚል መልስ አገኙ። ሆኖም ይህ ተስፋ ሰጪ አባባል ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን ሐኪም ወርቅነህ የተረዱት ከወራት በኋላ ነው። በሊያት ሰሞን ሲዶኞቸው የሌሎች ብዙም ከለፈ ወደ እሳቸው ዘንድ መጥተው ነበር። እንግሊዞችን በመወትወም የቴምድርስ እናት እመቤት ኢቴል ፋውልስ፣ሚስ ጆርጅ ወር ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ መጡ። የልጇን ወንድሞች ቢያዩ የነበረ ለመምታ ከሰጡቸው በኋላ ሁሉንም ወደ ቤቷ ወስዳ እራት ጋበዘቻቸው።

ሐምሌ ፳፫ ቀን ከዮጎዝላቪያ አምባሳደር ጋር በመሆን፣ የሚሊያንን መንግሥት የሚወክሉ ጽሑፍ፣ ጄኔቭ ለሚገኘው የዓለም መንግሥታት ማኅበር ቢጋራ ለማቅረብ ሲያዘጋጁ ዋሉ። ከሰዓት በኋላ የአሜሪካ ዜና ማሰራጫ ተወካይ ሁለቱንም ሚኒስትሮች አነጋገረ። በዕለቱ የተዘጋጀውን ጽሑፍ በሁለቱ አገሮች ስም ወደ ጄኔቭ ለመላክ ስለ ወሰኑ፣ ለአሜሪካ ዜና ማሰራጫ ወኪል ቅጂውን ሰጡት።

ሐምሌ ፳፭ ቀን የእንግሊዝ ፓርላማ ሃውስ ኦፍ ኮመንስ አባላት (Members of the House of Commons) ለሚኒስትር ሐኪም ወርቅነህ ክብር፣ የእራት ግብዣ አደረጉ። የግብዣው አዘጋጅ ኮሚቴ ኃላፊ፣ የተከበሩ ሚስተር ራልስ ዴቪስ (Mr. Ralys Davis) የእንኳን ደህና መጡ ንግግር አደረጉ። ሚኒስትር ሐኪም ወርቅነህ በበኩላቸው፣ ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሰላምና ችግር በሚገባ ተናገሩ።




እሳቸው ከተናገሩት ጥቂቱ "ለመሣሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ የእንግሊዝ መንግሥት እንዲያበድረን እንዲሁም፣ አዲስ አበባ የሚገኘውን ሌጋሲዮናችሁን ከእኛ ወታደሮች ጋር ሆነው የሚጠብቁ እንግሊዛዊ ሰዎች እንዲመደቡ" የሚል ነው።




የሐንስ እና ዳዊት ወርቅነህ አትክልት ስፍራ የግራሞፎን ሙዚቃ ሲሰሙ

ይህን ቃል ከተናገሩ በኋላ፣ ለተደረገላቸው መልካም አቀባበል እና የእራት ግብዣ ልባዊ ምስጋና አቀረቡ። ሐምሌ ፳፮ ቀን በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት በዓል ምክንያት፣ ከእንግሊዝ ንጉሥ የእንኳን አደረሰዎ መልዕክት ስለ መጣ፣ ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ በቴሌግራም ላኩት። ሐምሌ ፳፮ ቀን በአዲስ አበባ ሐኪም ቤት ከፍቶ የነበረው ዶክተር ላምቢ መጥቶ ለዶክተር ቶሬንስ ወደ ኢትዮጵያ የመግቢያ ፈቃድ (ቪዛ) እንዲሰጡት ጠየቀ።

እሳቸውም ዶክተር ቶሬንስ ቀደም ሲል መጥቶ ስለነበረ ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ የመግቢያ ፈቃድ የሰጡት መሆናቸውን ነገሩት። ቀደም ሲል በበኪንግሃም ቤተ መንግሥት የተያዘላቸው የቀጠሮ ቀን ስለ ደረሰ፣ ሚኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣ የክብር ልብሳቸውን ለብሰው፣ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ለንጉሥ ጆርጅ አምስተኛ የሹመት እና የበፊቱ ምኒስትር ከሥልጣን መነሳታቸውን የሚገልጠውን ደብዳቤ አስረከቡ።



ዮሐንስ እና ዳዊት ወርቅነህ አትክልት ስፍራ የግራሞፎን ሙዚቃ ሲሰሙ



ዮሐንስ፣ዳዊትና ሊያ ከሌጋሲዮኑ ቤት ደረጃ ላይ

በተጓዳኝ የንጉሥ ሰለሞን እና የንግሥት ሳባን ኒሻን ከነሀብሉ (Cordon) በአፄ ኃይለ ሥላሴ ስም ለንጉሥ ጆርጅ አምስተኛ ሸለሙ:: የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ኃላፊ እና ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒስትር መሆናቸው አሁን በዚሁ ይፋ ወጣ:: በዚህ ምክንያት፣ቀደም ሲል ከሰር ላንሴሎት ኦሊፋንት (Sir Lancelot Oliphant) ጋር ሲነጋገሩ ለአንድ ሳምንት ተብሎ ተይዞ የነበረው ቀጠሮ፣በወራቶች ቢዘገይም፣ስለ ወቅቱ ጉዳይ ለመነጋገር ነው በማለት ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ጠሯቸው:: የዕለቱ አጀንዳ የመሣሪያ ግዢ ጉዳይ ነበር ተብሎ በቅድሚያ ስለ ተነገራቸው፣ተስፋ ሰንቀው ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ሄዱ:: ሰር ላንሰሎተ ተገቢውን የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ካደረጉላቸው በኋላ፣ሁለቱ ሰዎች ለመነጋገር ተቀመጡ::




ከሁለቱ ሰዎች ጋር ወይይት ሲጀምሩ፣ሰር ላንሰሎት ፊት ላይ ጭንቀት ይታይ ነበር:: የእሳቸው ጭንቀት፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ቸር ወሬ ለመስማት የነበራቸውን ተስፋ አጨለመው:: የፈሩትም አልቀረ፣ሰር ላንሰሎት ያሊፋንት ፊታቸውን ከአሻሹ በኋላ "ክቡር ምኒስትር፣ዛሬ እንዴት ብዬ እንደማስረዳዎ ግራ ገብቶኛል፣ግን በጥሞና ያዳምጡኝ:: ታላቋ ብሪታንያ ለእርስዎና ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ ፍቅርና አክብሮት አላት:: ግን በአሁኑ የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ፣ከፍላጎታችን ውጪ የሆነ ውሳኔ ማሳለፍ ግድ ሁኖብናል:: በዚህም የእኛ ምክር ቤት (House of Commons) ለኢትዮጵያ እና ለጣሊያን መንግሥታት መሣሪያ የመሸጥ ማዕቀብ ለማድረግ ተገድዷል:: ይሁን እንጂ፣ኢትዮጵያ በእንግሊዝ ግዛቶች ሁሉ መሣሪያ ማጓጓዝ እንድትችል ተፈቅዷል" አሉ:: የሰር ላንሰሎት ያሊፋንት አነጋገር «እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው» የሚባለው ተረት ዓይነት ነበር:: ለዚህ አባባሌ ምክንያት የሆነኝ፣በዚያን ወቅት ጉልበቱ ከፈረጠመ፣ኃይለኛነቱን ከአሳወቀው የናዚ መሪ አዶልፍ ሂትለር ጋር የሙሶሊኒ መንግሥት ተባብሮ እንግሊዝን እንዳይወጋት ስለሰጉ መሆኑ ነው:: ይህን የተረዱት ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ለሰር ላንሰሎት ነገሩት::

"በእንግሊዝ ግዛቶች በኩል መሣሪያ እንዲተላለፍ ከተፈቀደ፣መግዛትስ ለምን ሳይፈቀድ ቀረ? ትልቁ ጥያቄ ይኸ ነው:: ጣሊያን የመሣሪያ ፋብሪካ አላት:: የጦር መሣሪያዎችን በገፍ ታመርታለች:: ሆኖም፣ለእኛ የተፈቀደው የመሣሪያ ማጓጓዝም ለጣሊያንም ይፈቀዳል ማለት ነው:: እኛ ደግሞ መሣሪያ እንዳንገዛ ማዕቀብ ተጥሎብናል:: ታዲያ መሣሪያ ከየት ተገኝቶ ነው በእንግሊዝ ግዛቶች ማሳለፍ ትችላላችሁ የምትሉን? መሣሪያ ከሌለን ደግሞ እንዴት ነጻነታችንን ለማስከበር ከወራሪዎቹ ጋር መዋጋት እንችላለን?" ብለው ላቀረቡት ጥያቄ፣ሰር ላንሰሎት ያሊፋንት ምንም መልስ ሳይሰጡ ቀሩ:: በዚሁ ቀን፣የቅርብ ምሥራቅ እና የሕንድ የህትመት ድርጅት (The Near East afid Indian Press Officer) ኃላፊ የሆኑት ሚስተር ሃንኮክ ለሁለተኛ ጊዜ መጥተው፣ከምኒስትር ወርቅነህ ጋር ቃለ ምልስ ተካሄደ::

በማግስቱ ደግሞ፣ዘኒው ስቴትስ ማን (The New Statesman) የሚባለው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆኑትን ሚስተር ኪንግስሌይ ማርቲን (Mr. Kingsley Martin) የሚባሉትን የኢትዮጵያ ወዳጅ ተቀብለው አነጋገሩ:: ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እንግሊዝ አገር ከገቡበት ቀን ጀምሮ፣በዲፕሎማቲክ ግንኙነት፣ለመሣሪያ ገንዘብ ብድር ፍለጋ እና የጦር ትጥቅ መሣሪያ ግዢ ማዕቀብ እንዲነሳ በመከራከር፣ከዚያም በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ወዳጆች የገንዘብ እና የሃሳብ ድጋፍ ለማግኘት፣ያለ እረፍት ይሯሯጡ ነበር:: ሐምሌ ሸኟ ቀን፣ወደ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ድንገት ተጠርተው ሄዱ:: እዚያ ደርሰው ከሰር ጆርጅ ማውንትሴይ (Sir George Mountsey) ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ለውይይት ተቀመጡ::

በመጀመሪያ፣ሰር ማውንትሴይ የተናገሩት፣ለጦር መሣሪያ መግዣ ኢትዮጵያ የጠየቀችው የገንዘብ ብድር" አለመፈቀዱን ነበር::



ዮሐንስ፣ ዳዊትና ሊያ ከሌጋሲዮኑ ቤት ደረጃ ላይ

ሁለተኛ ያሉት ደግሞ "አዲስ አበባ የሚገኘውን የእንግሊዝ ሌጋሲዮንን ከእኛ ወታደሮች ጋር ሆኖ ይጠብቅ ያላችሁትም አልተፈቀደም። ምክንያቱም፣የእኛ የጦር ሠራዊት ከእናንተ ወታደሮች ጋር መደባለቁን ሕጋችን አይፈቅድምና ነው" አሉ። በመቀጠልም "ለዚህ ጉዳይ በእኛ የውጭ ጉዳይ ቢሮ በኩል መፍትሄ ተቀይሷል። መፍትሄውም ፲፬ኛው የፑንጃብ ሽለቃ ሠራዊት ክፍል፣ ነሐሴ ፲፮ ቀን ወደ አዲስ አበባ ተልኮ ሌጋሲዮኑን እንዲጠብቅ መታዘዙ ነው" የሚል ቃል አከለበት። ምኒስትር ወርቅነህ ይህን የመሰለውን ሐሳብና ውሳኔ ከሰሙ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ቢሯቸው በታላቅ ቅሬታ ተመለሱ። የኢትዮጵያ ችግር እንዲህ እየተወሳሰበ በአለበት ወቅት፣የቀይ መስቀል ማሕበር ማቋቋም ኢትዮጵያ ውስጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣ከሉርድ ሉጋርድ (Lord Lugard)፣ከዶክተር ሜሊና (Doktor Melly) ከሚስተር ቤንቲንክ (Mr. Bentink) ጋር ተነጋግረው ስምምነት ላይ ደረሱ። ከሁለት ቀን በኋላ፣ ከካንተርቤሪ ሊቀ ጳጳስ (Archbishop of Canterbury) ጋር ምሳ ሲበሉ፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር እንዲቋቋም፣በሚቻላቸው ሁሉ ማኅበሩን እንደሚረዱ ተናገሩ። መናገር ብቻ ሳይሆን አይሮፕላን ጭምር ያለው የቀይ መስቀል ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ተዘጋጁ። ወዲያውኑ እንደ ኢትዮጵያ በቂ አይሮፕላን ማረፊያ ለሌላት አገር አመቺ ናቸው የተባሉ ሁለት አይሮፕላኖች፣ድንኳኖች እና መድኃኒቶች ተገዙ። እንግሊዛውያን አይሮፕላን አብራሪዎች፣ሐኪሞች እና መድኃኒት፣ድንኳኖች እንዲሁም ከስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበር የመጡ አራት ሐኪሞች እና አንድ አይሮፕላን አብራሪ ጭምር ወደ ኮረም ተላኩ።

ሐምሌ ፳፱ ቀን፣የእንግሊዝ ነገሥታት ዘመድ የሆኑት ካውንት ፓላቪንቺኒ (Count Pallavincini) ከሚኒስትር ወርቅነህ ጋር ተገናኝተው፣ጀርመን አገር በሚገኘው በክሩፕ (Krupp) ኩባንያ በኩል የጦር መሣሪያ ለመግዛት እንዲቻል ፈቃደኛ መሆናቸውን ተናገሩ። ሚስተር ክሩፕ፣ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመጀመሩ በፊት በስሙ በሚጠራው ኩባንያ፣ግዙፍ የሆነ የመሣሪያ ፋብሪካ አቋቁሞ የሂትለርን የናዚ መንግሥት ገናና እና ኃይለኛ እንድትሆን የረዳ የጦር መሣሪያ አምራች የሆነው የግል ኩባንያ ባለቤት እና ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው።

ሚኒስትር ወርቅነህ አሁን የተሰጣቸውን ተስፋ ተመርኩዘው ከጥቂት ቀናት በኋላ ልጃቸው ዮሴፍ፣ከክሩፕ ኩባንያ ዲሬክተር ጋር እንዲነጋገር፣ከካውንት ፓላቪንቺኒ ጋር ወደ ጀርመን ላኩት። ካውንት ፓላቪንቺኒ እና ዮሴፍ ጀርመን አገር ከመሄዳቸው በፊት፣ከጀርመን አምባሳደር ዶክተር ሊዮፖልድ (Dr. Leopold Von Hoesch) ጋር ስለ ፕሮፓጋንዳ ጉዳይ ለንደን ውስጥ ተነጋግረው ነበር። ለዚህም ነው፣ልጃቸው ዮሴፍ ያለ አንድ ስጋት ወደ ጀርመን ሊሄድ የቻለው። ዮሴፍ ስለ መሣሪያ ግዥ እና ወደ ኢትዮጵያ የማጓጓዝ ጉዳይ ከክሩፕ ጋር ተነጋግሮ ተስፋ ሰጪ ስለሆነ ስምምነት ላይ ደረሱ።



ወደ ጀርመን የሄዱበትን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ዮሴፍና ካውንት ፓላቪንቺ ወደ ለንደን ተመለሱ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የኢትዮጵያ የልብ ወዳጅ የሆኑት ካውንት ፓላቪንቺኒ ወደ ሌጋሲዮኑ መጥተው "እርስዎ ወደ አዲስ አበባ የሚልኩትን ሃሞላ የእንግሊዝ መንግሥት በየጊዜው እየጠለፈብዎት ነው" ብለው ለምኒስትር ወርቅነህ ነገሯቸው። እሳቸው (ምኒስትሩ) ይህን መረጃ እንዳገኙ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ተዘጋጁ። ቀጥሎም ጣሊያን እና ኢትዮጵያን ለማስታረቅ በእሳቸው (ፓልቪንቺኒ) እና በጣሊያን ንጉሥ በኩል ሙሶሊኒን እንዲያግባቡት ደብዳቤ ተዘጋጀ። ይህ ደብዳቤ ለንጉሡ የሚላክበትን መንገድ እንዲያመቻች ለኮሎኔል ራየን (Ryan) ሰጡት። እሱ ደግሞ በበኩሉ ደብዳቤውን ለአየርላንድ ፕሬዚደንት ሚስተር ደ ቫሌራን (Mr. De Valera) በቫቲካኑ ጳጳስ በኩል እንዲያደርሳቸው ያድርጉልን ብሎ ሰጣቸው። ደብዳቤው ለጣሊያኑ ንጉሥ መድረሱ ቢረጋገጥም ከዚያ በኋላ የት እንደ ደረሰ ለማወቅ አልተቻለም። በአንፃሩ መሣሪያ ስለመግዛት ጉዳይ ዮሴፍ ወርቅነህ ጀርመን አገር ድረስ ሄዶ፣ከክሩፕ ኩባንያ ጋር ያደረገው ድርድር በገንዘብ እጦት ምክንያት ሳይሳካ መቅረቱ እውን ሆነ። ሐምሌ ፴ ቀን ከሚሲስ ፖል ሮብሰን (Mrs. Paul Robeson) ጋር እና ከሚሲስ ማርቆስ ጋርቬይ (Mrs. Marcus Garvey) ጋር ተገናኙ። ሚሲስ ጋርቬይ ሲመጡ፣የኢትዮጵያ ወዳጆች ማኅበር ሠራተኛ የሆነው ዶክተር ሂጊንስ (Doctor Higgins) አብሮ ነበር። በዚያኑ ዕለት፣ዶክተር ጀቨንስ (Dr. Jevons) የሚባል ሰው መጥቶ "እኔ ገንዘብ በማሰባሰብ ለመርዳት ፈቃደኛ ነኝ። ነገር ግን እኔ ለማሰባው ገንዘብ በቅድሚያ ኮሚሲዮን መከፈል አለብኝ" አለ። ማንም ሊረዳው (ሊገነዘበው) እንደሚችለው፣በዚያን ጊዜ የጦር መሣሪያ ለመግዛት ከነበሩት ችግሮች አንዱ የገንዘብ እጦት ነበር። ምኒስትር ወርቅነህ የሰጡት መልስ "ለእንተ የደላላ ክፍያ በቅድሚያ መክፈል ይቅር እና መሣሪያውን ለመግዛ እንኳን በእጃችን ምንም ገንዘብ የለም" የሚል ነበር፡ ስለዚህ የደላላው ዶክተር ጀቮንስ የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ሆነ።

ነሐሴ ፪ ቀን፣በኢትዮጵያ የቀድሞ የሃንጋሪ አምባሳደር የነበረው ሚስተር ሽዊርመር (Mister Schiwirmer) ወደ ሌጋሲዮኑ መጥተው ከሚኒስትሩ ጋር ተገናኙ። እኚህ ሰው ለኢትዮጵያ ልዩ ፍቅር ያላቸው ሰው ስለሆኑ፣ወደ ለንደን መጥተው ሚኒስትሩን ከአወያዩዋቸው በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲሄዱ ኢትዮጵያን ለመርዳት የተቻላቸውን ያህል እንደሚጥሩ ቃል ገቡላቸው።

ነሐሴ ፲፮ ቀን፣የለንደን ዩናይትድ ፕሬስ (London United Press) ጋዜጠኛ ወደ ሌጋሲዮኑ መጥቶ፣ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ መግለጫ ቢሰጡን ፩ ሺሕ ጊኒ (ፓውንድ) ለመክፈል ዝግጁ ነን አሉ። ሆኖም በዚያ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ መሄድ አስቸጋሪ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ነሐሴ ፳ ቀን ደግሞ፣የስፔኑ ራይሞን ኮንክሪ (Mr. Raymond Conquery) ወደ ሌጋሲዮኑ መጥቶ ለሚኒስትር ወርቅነህ ቃለ መጠይቅ አቀረበላቸው። በመቀጠል ወደ ሮም ሄዶ ለሙሶሊኒም ቃለ መጠይቅ እንደሚያቀርብ ነገራቸው። ከአንድ ወር በኋላ የሁለቱም ቃለ ምልልስ በጋዜጣ ወጥቷል።

በዚያኑ ሰሞን ደግሞ፣በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክልል፣ሚስተር ሪኬትስ (Ricketts) የሚባል አሜሪካዊ፣ነዳጅ (ዘይት) ለማውጣት ፈቃድ ተሰጠው ተብሎ የጋዜጦቹ የሰሞኑ ዜና ሆነ። ለዚህ ጉዳይ ጋዜጠኞች መጥተው ሚኒስትር ወርቅነህን ጠየቋቸው። እሳቸው ለሪኬትስ ስለተሰጠው ፈቃድ ምንም የሚያውቁት ነገር ስላልነበረ፣ምኒስትር ወርቅነህ መግለጫ የሚጠይቅ ደብዳቤ ወደ አዲስ አበባ ጻፉ። ከአዲስ አበባ ምንም መልስ ሳይገኝ ቀረ።

ነሐሴ ፳፰ ቀን፣በሎርድ ሶምፌል (Lord Somphill) ሰብሳቢነት፣በሃይድ ፓርክ ሆቴል ፻፶ እንግዶች በተገኙበት ዝግጅት ላይ፣ሐኪም ወርቅነህ ተገኝተው ነበር። እሳቸው በዚህ ስብሰባ ላይ ያደረጉት ንግግር፣በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፈ፣የሰውን አትኩሮት የሳበና የአዳማጩን ልብ የሚማርክ ንግግር ነበር። ተሰብሳቢዎቹ በጭብጨባ እና ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር በሚል መፈክር ንግግራቸውን ማድነቃቸውን አሳዩ። በመቀጠልም ትንንሽ ልጆቻቸው የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር አሰሙ። ከዚህ የተከበረ እና የተደነቀ ስብሰባ በኋላ፣የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሚስተር ካምቤል ተቃውሟቸውን ለመንገር ሚኒስትር ወርቅነህን ገለል ወዳለ ቦታ ወስደው "በስብሰባ ላይ ዲፕሎማቶች ይፋ የፖለቲካ ንግግር ማድረግ ክልክል መሆኑን አያውቁምን? ለአሁኑ ሁኗል፣ከእንግዲህ ወዲያ ግን፣ይህን የመሰለ ንግግር እንዳያደርጉ" በማለት ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው።

የሚኒስትር ወርቅነህ ንግግር ይፋ በወጣ ጊዜ ዜናውን የሰማው ሚስተር ቼርቶክ እና የሥራ ጓደኛው ሚስተር ራፓፖርት (Mr. Rappaport) ከዚህ በፊት ጀምረው በነበረው የፕላቲነም ማዕድን ጉዳይ በድጋሚ ለመነጋገር ፈልገው ወደ ሌጋሲዮኑ መጡ። በዚህ ጉዳይ ላይ ስለተነሳው ብድር ከመነጋገራቸው በፊት፣፪፻ ሺሕ ፓውንድ ስተርሊንግ በባንክ ውስጥ አስገቡና አሳዩኝ በማለት ምኒስትሩ አፋጠጧቸው። ቼርቶክ እና ራፓፖርት በበኩላቸው፣የጦር መሣሪያ ለመግዛ የሚውል አንድ ሚሊዮን ፓውንድ ስተርሊንግ ለማበደር እንስማማለን። እንዲሁም የፕላቲነም ማዕድኑን በአንድ ሚሊዮን ብር ድርሻ እንገዛዎታለን። ከዚህ በተጨማሪም ማዕዱኑ ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ፣፴፭% ለእርስዎ እንሰጣለን በማለት ምኒስትር ወርቅነህን ለማግባባት ሞከሩ። ነገሩ ዕውነት ባይመስልም የውል ረቂቅ ተጽፎ ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ተላከ። ደብዳቤው ለጃንሆይ መድረሱ ባይታወቅም፣ወቅቱ አገርን ከጠላት ወረራ ለመታደግ ሩጫ የበዛበት ጊዜ ስለ ነበረ መልስ ለማግኘት ችግር መኖሩ ግልጽ ነው።

ቼርቶክ ከሚኒስትሩ ጋር ስለ መሣሪያ ግዢ ጉዳይ መነጋገራቸውን ከሰሙት ጋዜጠኞች መሐከል፣የሞርኒንግ ፖስት (Morning Post) ጋዜጠኛ ሚስተር ኤች.ኤ. ግዊን (Mr. H.A. Gwynne) አንዱ ነው። ይህ ሰው፣የሉዳኑ አቡን ግዊን ወንድም ሲሆን፣ሌላው ወንድሙ ደግሞ በእንግሊዝ ሱማሌና በኢትዮጵያ መሐል የሚገኘው ጠረፍ ኮሚሽነር ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎች ወደ ሚኒስትር ወርቅነህ ዘንድ የመጡት ስለ ቼርቶክ እና ራፓፖርት ማንነት ለማጣራት ነው።



እነሱ በኋላ እንዳገኙት መረጃ፣እነዚህ ሁለት ሰዎች በማጭበርበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ተራ ወንበዴዎች መሆናቸውን ነው። ስለ ማጭበርበር ጉዳይ ከተነሳ፣ኢትዮጵያ ለጊዜው ያጋጠማትን ችግር ለመቋቋም በገፁህ ልቡና የተነሱ እንዳሉ ሁሉ የግል ጥቅም ፈላጊዎች በአፍሪካ አሜሪካን ህብረተሰብ መሐከል ሠርገው የገቡ አጭበርባሪዎች እንደነበሩ ማወቅ ተገቢ ነው። ቀደም ሲል ከገለጥናቸው ግለሰቦች በተጨማሪ ሌሎችም ጥቅም አሳዳጆች መኖራቸው ታውቋል። እንደነዚህ ያሉትን አጭበርባሪዎችን ለማጋለጥና በጨዋነት ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ የሚሹትን ለመርዳት ሲባል በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ላይ የሐርለም ጥቁር አሜሪካኖች የምኒልክ ክበብ የሚባል አቋቁመው ነበር። ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ሰዎች የጀመሩት የምኒልክ ክበብ ተጠናክሮ "ለኢትዮጵያ ዕርዳታ አስተባባሪዎች" (United Aid for Ethiopia) ወደሚል ደረጃ ከፍ አለ። የዚህ ተቋም ዋና ዓላማው፣እንግሊዝ አገር በሚገኘው ቢሮ ዕውቅና ያለው ሆኖ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በቅርብ ለመሥራት የተዘጋጀ አስተባባሪ ኮሚቴ ነበር። ሐሳባቸው የኢትዮጵያን መንግሥት ዕውቅና ይዘው ውጤታማ የሆነ ዕርዳታ ለማሰባሰብና በማጭበርበር ላይ የተሰማሩትን ሌሎች ድርጅቶች ጨርሶ ለማስቆም ባይቻል እንኳን እንቅስቃሴያቸውን በመጠኑም ቢሆን ለመግታት ታስቦ ነው። ይህን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ለተቅዋሙ መሪ ሆነው የተመረጡት የዝነኛው ፕሬስቢተሪያን ቄስ ሎይድ ኢሜስ (Reverend Lloyd Imes)፣የኒው ዮርክ አምስተርዳም ዜና አሳታሚ ሚስተር ፊሊፕ ሳቮይ (Mr. Philip Savoy) የተቋሙ ዋና ጸሐፊም ናቸው። እነዚህ ታዋቂ አፍሮ አሜሪካኖች ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው ከኢትዮጵያ የሌጋሲዮኑ ሚኒስትር ወርቅነህ ጋር ተገናኙ። በአሜሪካ ዋና ቃንሲል ሆኖ ከተመደበው ጆን ሾው (John Shaw) ጋር አሳስፈላጊ ያልሆነ ግጭት እንዳይኖር በሚስብ ሦስቱ ሰዎች ወደ እንግሊዝ አገር የሄዱት ያለ ትልቅ ትዕይንት (without great fanfare) ነው*። ብራዘር/ ብሮድኸረስት (Broadurst) መጥተው ሚኒስትሩን አነጋገሯቸው ነበር። ቃለ ምልልሱን የሰሙ በርካታ ሰዎች በስልክ እየደወሉ በአካልም እየመጡ ከኢትዮጵያ ጎን እንቆማለን የሚል የማጽናኛ ንግግር አደረጉ። አንዳንዶቹም አቅማቸው የቻለውን ያህል የገንዘብ አስተዋፅዖ አድርገዋል። መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ደግሞ፣ሚስስ ጋርቬይ መጥተው በአሜሪካን አገር ገቢ ማስገኘት ቅስቀሳ ለማድረግ ስለ አሰቡ፣ለሥራ ማንቀሳቀሻ የሚሆን ገንዘብ ምኒስትሩ እንዲሰጧቸው ጠየቁ። እሳቸውም "እኛን ለእናንተ የምንሰጠው ለእኛ ሥራ ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ የለንም" የሚል መልስ ሰጧቸው። የኢትዮጵያ ደጋፊ የሆኑት ሰዎች እና ሐኪም ወርቅነህ ያተኮሩት መሣሪያ ፍለጋ ላይ ብቻ አልነበረም። ዘመናዊ የጦር መሣሪያና አይሮፕላን ከተገዛ በኋላ፣መሣሪያዎቹን በአግባቡ ሊሠሩባቸው የሚችሉ ሰዎችም አፈላልጎ መቅጠርም ነበረባቸው። ምክንያቱም አዲስ የሚገዙትን አዳዲስ መሣሪያዎች ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሰዎች እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ጊዜ ይፈጃልና ነው። በዚህ ምክንያት ከአገሩ ሰዎች ጎን ለመሰለፍ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ፈቃደኞች የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን የሚፈልጉ መሆናቸውን፣ሐኪም ወርቅነህ ከበቂ ማብራሪያ ጋር በጋዜጣ አወጡ።


ጋዜጣውን እንደሰሙ ከኢትዮጵያ ጎን ሆነው ለመዋጋት የሚፈልጉ ከልዩ ልዩ አገሮች በርካታ ያሉ ሰዎች መጡ:: አብዛኛዎቹ የመጡት ለግንም ሲሆን እንዳንዶቹ ደግሞ ግፍን የሚጠሉ፣ሰብአዊ ርኅራኄ የነበራቸው ናቸው:: ከእነዚህም አንዱ አለክሳንደር ዶል ባዩ የሚባል የከዩባ ተወላጅ ነው:: ጋዜጣውን አንብቦ እና ጥሪውን ተቀብሉ የመጣው ይህ የኩባ ቢጋ ወደ አገራችን ገብቶ ከኢትዮጵያውያ ጎን ሁኖ ተዋግቷል:: ይህ ሰው ቀይ አንበሳ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ "አንድ ነጭ በጥቁሮች ሰቆቃ ምድር" የሚል ታሪክ ጽፎ አሳትሟል:: ይህ መጽሐፍ በዶክተር ተስፋዬ መኮንን ባይለሚ ተተርጉሞ ታትሞ ወጥቷል:: በመጽሐፉ ውስጥ ስለ አምባሳደር ወርቅነህ የሚናገረውን በቀንፅል እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

> እኔ ሉንደን ነበርኩኝ:: ወደ ኩባ መመለስ የሚያስችለኝ ገንዘብ ከተማ ነበር:: ሃሳቤን ለመስወጥ ያነሳሳኝን በእርግጠኝነት መናገር አልችልም:: አንድ ቀን ማታ 'ኢሉስትሬትድ ለንደን ኒውስ' "Illustrated London News" ጋዜጣ፣ የኢትዮጵያን አምባሳደር ደብሊው ማርቲን ምስል የያዘ "በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን የውጭ ሀገር የጦር መኮንኖች ከኢትዮጵያ ወገን ተሰልፈው ለመዋጋት የሚፈልጉ መጥተው እንዲመዘገቡ ጥሪ ተላለፈ" የሚል መልዕክት ያዘለ ዜና ይዞ መውጣቱን አየሁ:: እኔ የምፈልገው ይሄ ነበር ዕድል ሆነ!
>
> የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን የሚገኘው በፒ ኢልም ፓርክ ጋርደን ነበር:: በታክሲ ወደዚያ አመራሁ:: ባለ ስድስት ፎቅ ቀንጆ ቤት ነበር:: እንደደረስኩም አንድ እንግሊዛዊ ጠባቂ እስከ እንግዳ መቀበያው ይዞኝ ገባ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሌጋሲዮኑ ፀሐፊ ወደ እኔ መጣ:: ለአቢሲኒያ ሄጄ ለመዋጋት እንደምፈልግ ከገለፅሁለት ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብሎኝ በረጅሙ ተንፍሶ "ለምን ያንተ ያልሆነ ምድር መታገል ትመኛለህ?" አለኝ:: በቀላሉ ገድል ለመሥራት ከልጅነቴ ጀምሮ ወደ አፍሪካ ምድር መሄድ እፈልግ ነበር:: ይሄ አጋጣሚ ትክክለኛና ጥሩ ነው ብዬ አምናለሁ" ስል መለስኩ:: የሌጋሲዮኑ ጸሐፊ ፊቱን ከስተር አድርጎ በዝምታ ጥሎኝ ወደ መግቢያ ተመለሰ:: ከመግቢያው በር ሲደርስ መለስ ብሎ በዝግታ ወደ እኔ መጣ:: "ክቡር አምባሳደር ቢሯቸው ናቸው:: አሁኑኑ ሄጄ እነግራቸዋለሁ:: ለጥቂት ሰከንዶች እባክዎ ይታገሱኝ" አለ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ ተመልሶ ወደ ላይኛው ፎቅ ቢሮ እንድወጣ ነገረኝ:: በጣም ትልቅ መስኮቶቹ ሰፊ ስለሆኑ የሚያስገቡት ብርሃን ቤቱን (ክፍሉን) በግልፅ የሚያሳይ ሳሎን ውስጥ ገባሁ:: ክቡር አምባሳደር ደብሊው ማርቲን ወንበራቸው ላይ በጥግ በኩል ቆጭ ብለዋል:: የቤት ውስጥ እሳት ማንደጃው በላይ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ካባ ደርበው ከንግሥት መነን ጎን የተነሱት ትልቅ ፎቶግራፍ ተሰቅሏል:: እንግሊዝኛቸው ጥርት ያለ እንከን የማይወጣለት፣ሁለመናቸው እና አቀራረባቸው እንደ አንድ የተማረ ሰውና ብልህ ጨዋ ሰው ነው:: ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ብልህ ሰው ነበሩ:: ለማርቲን ክቡር እንዳልኩው ከወሰጋ አካባቢ በሚገኝ ወርቅ ማዕድን ማውጫ፣ፈታድ ስጥተው፣ከእንግሊዞች ጋር ያላቸውን ቅርብ ግንኙነት ከግምት በማስገባት ሲሠራቸው የተቀላጠፈ እና ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል በማለት በእንግሊዝ አገር ባለ ሙሉ ሥልጣን አምባሳደር አድርገው ሾሟቸው::






በታላቋ ቢሪታኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር
አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እሸቱ
1927 ዓ.ም



በታላቋ ቢሪታኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር
አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ
1927 ዓ.ም



ዮሐንስ እና ዳዊት ወርቅነህ አትክልት ስፍራ የግራሞፎን ሙዚቃ ሲሰሙ

አምባሳደር ማርቲን በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተከበሩ እና ድምፃቸው በሁሉም ዘንድ ተደማጭነት የነበራቸው ሰው ነበሩ። አምባሳደሩ ከመቀመጫቸው ተነስተው ወደ እኔ መጡ። ምንም እንኳን ጠና ያሉ ቢሆኑም ቀጥ ብለው ያለ ምንም ድጋፍ በእርግጠኛነት ይራመዳሉ። የሰላምታ እጃቸውን ከዘረጉልኝ በኋላ ዜግነቴ ምን እንደሆነ ጠየቁኝ። ኩባዊ ነኝ አልኳቸው። ከእኛ በኩል ሆነህ ለመታገል ስትል ብቻ ነው ከአገርህ ድረስ የመጣኸው?"

"አይደለም" ስል መለስኩኝ። ዕውነተኛነቴን ለመግለፅ፣ከስፔን ገና መምጣቴ ነው። ወደ ኩባ ለመመለስ ነበር ዕቅዴ። ለውጭ አገር መኮንኖች በአቢሲኒያ ላይ የተቃጣውን ወረራ ለመዋጋት የቀረበውን ጥሪ አንብቤ ነው የመጣሁት። ይኸው ነው በቃ።

"አንተ የእኔን ምድር ታፈቅራታለህ?"

በእርግጠኛነት አላፈቅራትም። ግን በኃይልና በጉልበት አንድ አገር ይዞ የሚያደርሰውን ግፍ በፍፁም እጠላለሁ። የእኔ አገር በጣም ትንሽ ነች። ለሀገር ምድር ሙሉ ነፃነትና ክብር ለሚደረግ ውጊያ መዋጋት እጅግ በጣም ደስ ይለኛል።

አምባሳደር ማርቲን በለጠኋቸው መልስ የረኩ ይመስላሉ። በውስጤ ያለውን ዘልቀው ለመመልከት በዝምታ አተኩረው የተመለከቱኝ ምን ጊዜም ቢሆን ይታወሰኛል። "ብዙ የውጭ አገር መኮንኖች ከእኛ ሠራዊት ጋር ሆኖ ለመዋጋት ያቀረቡት የምዝገባ ጥያቄ በእጄ አለ (ይገኛል)፣አንተም ይህንን ፎርም ሙላ። አጥንተነው መልሱን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንሰጥሃለን" አሉ። ራሴን በመነቅነቅ የእሉታዊ መልስ ሰጠሁኝ። ከተቀበሉኝ አሁኑኑ ለመንዝ እና አገልግሎቴን መስጠት ለመጀመር ዝግጁ ነኝ። በተጻራሪው ከሆነ ወደ አሜሪካ እመለሳለሁ። የተከበሩት አምባሳደር ለጥቂት ጊዜ ካሰላሰሉ በኋላ፣
«ጥሩ፣በምን ውስጥ ነው ለማገልገል የምትፈልገው? በእግረኛነት ነው ወይስ በአየር አገልግሎት?" » ብለው ጠየቁኝ። እኔም "በአየር አገልግሎት ውስጥ" ብዬ መለስኩላቸው። እሳቸውም ወደ መቀመጫቸው ተመልሰው ለሚገን መዝገበው ለሚቀጥለው ቀን ቀጠሩኝ። "ነገ ከቀትር በኋላ በ፱ ሰዓት ተመለስ። ወደ ክሮይደን አውሮፕላን ማረፊያ ሄደን ፈተናህን እዚያ እንድታደርግ ይደረጋል።"
በተከበሩት አምባሳደር ሁለት ልጆቻቸው በመታጀብ በሚቀጥለው ቀን በተቀጠርኩበት ሰዓት ክሮይደን አየር ሜዳ ደረስን። ከሉንደን ከተማ ፱ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ፈተናዬን የምሠራበት ቢች ክራፈት የስፖርት ሆርኔት ሞተር የተገጠመላት ባለ ፪፻ የፈረስ ጉልበት ትንሽ አውሮፕላን ነበረች።

ወደ አውሮፕላኗ የማብረሪያ ክፍል ገብቼ ሞተሯን ካስነሳሁ በኋላ መሬቱን በመልቀቅ በአየር ላይ መንሳፈፍ ጀመርኩኝ። ለ፴ ደቂቃ ያህል የተለያዩ ለወታደራዊ በረራ አስፈላጊ የሆኑትን እንቅስቃሴዎች እና የበረራ ስልቶች ካሳየሁ በኋላ ያለ ምንም ችግር ተመልሼ አረፍኩ። እንደ ወረድኩም ክቡር አምባሳደር ማርቲን በድርጊቱ በጣም የረኩ ይመስላሉ።





ዮሴፍና ብንያም ወርቅነህ እሸቱ በአይሮፕላን በራሪ ልብስ

"ኮንትራት ውሉን ለመፈራረም ነገ ጧት ወደ ሌጋሲዮናችን እንድትመጣ" አሉኝ። በማግስቱ "የተከበርከው ዴል ባዬ በሻምበልነት ማዕረግ ለኢትዮጵያ ሠራዊትነት ተቀብለንሃል። ግን ሕጋዊ የሆኑትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርብሃል። በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥትህ በአቢሲኒያ በኩል ሆነህ ለመታገል እንቅፋት ሊፈጥርብህ አይችልምን?" ሲሉ ጠየቁኝ። "ክቡር አይችልም። አንድ የፖለቲካ ስደተኛ ነኝ" ብዬ መለስኩኝ። "ክርስቲያን ነህ?" "አዎን" "ለንጉሥ ኃይለ ሥላሴ እና ለወራሾቻቸው የአገልግሎት ጊዜህ እስከ አለቀ ጊዜ ድረስ በታማኝነት ለማገልገል ቃል ትገባለህ?" ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ። የተከበሩ አምባሳደርም ተነሱ። ጠረጴዛቸው ላይ በተዘረጋው የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ በተቀመጠ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እጄን እንዳስቀምጥ አደረጉኝ።



የሴፍና ብንያም ወርቅነህ እሸቱ በአይሮፕላን በራሪ ልብስ

ቃለ መሃላውንም ፈፀምኩ:: በንጉሡ ሠራዊት በኩል እንዳገለግል የሚያስገድደኝ የ፫ ዓመት ውል ፈረምኩኝ:: በፀረ ጣሊያን ወረራ ለሚወሰደው ዘመቻ ሁሉ የሚፀና» የሚል ሐረግ ይገኝበታል:: በመቀጠልም "በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ መጀመር አለብህ::

ለሥራ የሚያስፈልጉህን ወታደራዊ ትጥቆች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በሙሉ በዚህ ሌጋሲዮን ሂሳብ ከዚሁ ከሎንዶን ከዊልኪንሰን ቤት መግዛት ይኖርብሃል:: አሁን ከእኔ ጋር ገቢታ እንድትቀርብ በማክበር እጠይቅሀለሁ" አሉኝ:: ይህ አቀባበል በእርግጥ እንዲበገረመኝ አመሰክራለሁ:: የተከበሩት ኢትዮጵያዊ ክብዙ ሺህ የውጭ ሀገር ሰዎች መሐል እኔን ለመምረጥ ምን እንዳነሳሳቸው ለመጠየቅ አልፈለግሁም:: በሚቀጥሉት ቀናት፣ ከዊልኪንሰን ቤት በሌጋሲዮኑ ሂሳብ፣አንድ ባለ ፩ ሚሊ ሜትር ማንቼስተር ስኮር የጦር መሣሪያ ከነጥይቶቹ፣ የጦር ሜዳ መነፅር፣ የአቅጣጫ መጠቆሚያ (ኮምፓስ) እና ቴሌስኮፕ ገዛሁ:: በጣሊያኖችም ሆነ በእንግሊዞች የተሠሩ የአቢሲኒያ ካርታዎች በሎንዶን ሊገኙ የሚችሉትን ሁሉ አሰባሰብኩኝ:: በተጨማሪም እንደ የኢትዮጵያ ሹምበል ልብስ (ዩኒፎርም)፣ሸሚዙ ካኪ፣ሱሪው ግራጫ ገበርዲን እና ክብ ቆብ እንዲሰሩልኝ አዘዝኩኝ:: በሎንዶን ከሚገኙ ከምርጥ ሆቴሎች አንዱ በሆነው በሳቮይ ሆቴል ለአንድ ሳምንት ቆይታ አደረግሁ:: የተከበሩት አምባሳደር ልጆች፣የሲፍ እና ብንያም በየጊዜው ይጠይቁኝ ነበር:: ለእኔ ክብር ሲሉ ከጉዞዬ አስቀድሞ አንድ የሸኝት ድግስም አዘጋጅተው ነበር:: በሚቀጥለው ምሽት ከቪክቶሪያ ባቡር ጣቢያ ተነስቼ ወደ መድረሻዬ የሚወስደኝን ጉዞ ጀመርኩ::

ከአልኽንድሮ ዴል ባዬ ትረካ የምንረዳው፣አምባሳደር ሐኪም ወርቅነህ እሸቱ ሎንዶን እያሉ ለአገራቸው ክብርና ነፃነት የሠሩትን ሥራዎች ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መሆኑን ነው:: ፋሽስት ኢጣሊያ ከአይሮፕላን በምትጥለው የቦምብ ናዳና የመርዝ ጋዝ ዝናብ፣የኢትዮጵያ ሠራዊት ለጊዜው ቢሸነፍም፣በዱር በገደል ተሰማርቶ ትግሉን ለመቀጠል ወሰነ:: በዚህም ጎራ ላይ ጥቁር አንበሳ በሚል ስም፣የአገሪቷ ውድ ልጆች ያደረጉትን ተጋድሎ ወደ ፊት እናገኘዋለን::

መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የጣሊያን ወታደሮች የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው ወደ ትግራይ ግዛት መግባታቸውን በዓለም ጋዜጦች ውስጥ ዜናው ተሰራጨ:: መስከረም ፳፬ ቀን በግብፅ ኤምባሲ በተደረገው ግብዣ ላይ ኢትዮጵያ በግፍ በመወረሯ እነ ጆን ማፌይ (John Maffey)፣ስቶርስ (Storrs) እና የሎንዶን ከንቲባው አለንቢ (Allenby) ጭምር ኢትዮጵያ ላይ በደረሰው አሳዛኝ ሁኔታ አጽናኝ ንግግር አደረጉ:: በዚሁ ዕለት፣በሃውዝ ኦፍ ሎርድስ የመጀመሪያው የንግድ ጉባዔ ሲደረግ፣ሐኪም ሚኒስትር ወርቅነህ በክብር እንግዳነት ተጠርተው፣በመኳንንቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኙ:: ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን የመውረሯ ዜና ሲሰማ፣የሌጋሲዮኑ እንቅስቃሴ ከምን ጊዜውም የበለጠ ሆኑ:: የወረራው ሁኔታ በየቀኑ በራዲዮ ይነገርና በጋዜጣም ይወጣ ስለነበረ የኢትዮጵያ ወዳጆች ደብልጥ ወደ ሌጋሲዮኑ መጡ::



ጋዜጠኞች፣የሬዲዮ ማዘያ ወኪሎች፣በኢትዮጵያ ላይ በደል መድረሱ ያስቆጫቸው እንግሊዛውያንና የሌላም አገር ሰዎች፣በአካል እየመጡና በስልክም የግዛን ስሜታቸውን ይገልጡ ነበር:: በየዕለቱ ለሚመጣው ደብዳቤ መልስ መስጠትና ሚኒስትሩ የማያስተናግዷቸውን እንግዶች ተቀብሎ ማነጋገር በእኔ ኦፊሴል ጫንቃ ላይ ወደቀ:: ከእነርሱ በየቀኑ ለሚመጡት ከሃምሳ በላይ የሚሆኑ ደብዳቤዎች መልስ ከመስጠት በተጨማሪ የሌጋሲዮኑን ክስተዳደርና የቤት ሠራተኞችን መቆጣጠር ለአንድ ሰው ከባድ እየሆነ መጣ:: ሚኒስትሩ ሥራው ከባድ መሆኑን በመገንዘባቸው ረዳት የሚሆን ሰው ሲፈልጉ ተስፋዬ [illegible] የሚባል ሰው አገኙ:: ከዚህ በፊት እንደተገለጠው የተስፋዬ እናት ግሪካዊ ሲሆኑ፣እናቱ ኢትዮጵያዊት ናቸው:: እሱ በዎምብሌደ የተመረቀ ቢሆንም የሥራ ልምድ አልነበረውም:: ስለዚህ እሱ የተመደበው ለልዩ ልዩ ጉዳይ የሚመጡትን እንግዶች በመቀበልና በስልክ በማነጋገር ሥራ ላይ ነበር:: [illegible] ገልጸውታል::

ጥቅምት ፱ ቀን የሊይስተር ዱክ በኢትዮጵያ መጠቃት የተሰማቸውን ኀዘን በመግለጽ አንድ አምቡላንስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ሰጡ:: ጥቅምት ፩ ቀን የውጭ ጉዳይ ቢሮ ሠራተኛ የሆነው ሚስተር ፓተርሰን (Patterson) በኢትዮጵያ ላይ ተጥሎ የነበረው ማዕቀብ በይፋ መነሳቱን (officially lifted) ገለጠ:: ስለዚህ እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፴፭ በዓለም መንግሥታት መሐከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት፣መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ክቡር ሚኒስትሩ ለመፈረም የሚያስችላቸው ሥልጣን እንዳላቸው ጠየቀ::

የኢትዮጵያን ጉዳይ ለማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ሚኒስትር መሆናቸው እየታወቀ፣ይህን መሰል ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢ አልነበረም:: ይሁን እንጂ ጊዜው አጣብቂኝ የተሞላበት ወቅት በመሆኑ፣መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ከንጉሡ ነገሥቱ ደብዳቤ ማግኘት አለባቸው ስለተባለ፣ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደብዳቤ መጻፍ አስፈላጊ ነበር:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ጃንሆይ ማይጨው ላይ አርሲኮናቸውን ይዘው በጦር ሜዳው ላይ ለመሳተፍ እየመሩ ነበርና የውክልና ፈቃድ ማግኘት አለመቻሉን ለሚስትር ፓተርሰን ስለነገሩት የመሣሪያ ግዢው ጉዳይ ተሰናከለ:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ጦርነቱ መዝመታቸው የሰሙት የሲፍ ወርቅነህ እና ብንያም ወርቅነህ፣አገራቸው በፋሽስት ኢጣሊያ መወረሯ ስለአስቆጫቸው ጦርነት መጀመሩን ከሰሙበት ዕለት ጀምረው ወደ አገራቸው ለመግባትና ከጠላት ጋር ለመፋለም አስፈላጊውን ዝግጅት ሲያደርጉ ነበር::

ዮሴፍ በኤሮኖቲክስ ምሕንድስና፣ብንያም ወርቅነህ በሲቪል መሐንዲስነት ተመርቀው አባታቸው ዘንድ የሄዱበት ወቅት ስለነበረ አባታቸው (ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ) በዓድዋ ጦርነት ጊዜ፣ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለመዋጋት ያደረጉትን ዝግጅት እና የከፈሉትን መስዋዕትነት ልጆቻቸው ቀደም ብለው ያውቁ ነበር:: አርባ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጣሊያን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ገብታ፣ነፃነቷን ለመንጠቅ የምታደርገው ሙከራ መገታት እንዳለበት ተገቢ መሆኑን የሚያምኑት ዕዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣ልጆቻቸውን መርቀውና አበረታተው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት እንዲችሉ አስፈላጊውን ገንዘብ እና ምክር ሰጧቸው::

ዮሴፍ ወርቅነህ ልዕልት ቤቲ ዓሊ ካንን (Princess Betty Ali Kahn) አፍቅሮ ስለነበረ፣ሲተጫጩ ጥቂት ቀን ሲቀረው ወደ አገሩ መሄድ ግድ ሆነ::



ዮሴፍና ብንያም ከዳዊትና ከዮሐንስ ጋር ሲሰነባበቱ

ጥቅምት ፯ ቀን፣ለዮሴፍ እና ለብንያም ክብር ትልቅ የእራት ግብዣ ተደረገ:: ቁርጡ ቀን ደርሶ ብንያም እና ዮሴፍ ወደ አገራቸው ለመሄድ ሴጋሲዮኑን ለቅቀው ወጡ:: አበረንዳው ላይ ፍቅረኛሞቹ ዮሴፍና ቤቲ ተቃቅፈው እንባቸውን እየተራጩ ተለያዩ::




በተመሳሳይም ከጣሊያን ጋር ለመዋጋት ከእንግሊዝ አገር ሲወጡ ሁለቱን ታናህ ወንድሞቻቸውን ዳዊት እና ዮሐንስ ወርቅነህን ተሰናበቱ:: ቁርጡ ቀን ደርሶ ብንያምና ዮሴፍ ወደ አገራቸው ለመሄድ ሌጋሲዮኑን ለቅቀው ወጡ:: : አበረንዳው ላይ ፍቅረኛሞቹ ዮሴፍና ቤቲ ተቃቅፈው እንባቸውን እየተራጩ ተለያዩ:: በተመሳሳይም ከጣሊያን ጋር ለመዋጋት ከእንግሊዝ አገር ሲወጡ፣ ወንድሞቻቸውን ዳዊት እና ዮሐንስ ወርቅነህን ተሰናበቱ:: ዮሴፍ እና ብንያም የጣሊያንን ወረራ ለመመከት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በግብፅ በኩል ነው:: መንገዳቸው በስዌዝ ካናል በኩል ስለነበረ፣በመርከብ አንድ ሳምንት ተጉዘው አሌክሳንድሪያ ወደብ ደረሱ:: እዚያ የአባታቸው ወዳጆች፣ብፁዕ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ እና ሚስተር ሚካኤል ክርያኮ (Mr. Michael Kiriako) በጣም የደመቀ አቀባበል እና ግብዣ አደረጉላቸው:: አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ስለሆኑ ከግብፅ ጋር ያላቸው ወዳጅነት የፀና ነው:: በዚህም፣ለዶስ ፓሻ (Doss Pasha) መሐመድ ፓሻ (Mohamed Pasha) እና የአሌክሳንድሪያ ፓትሪያርክ (Patriarch of Alexandria) ኢትዮጵያን በመደገፍ እና ለልጆቻቸውም ላደረጉት ጥሩ አቀባበል ጭምር፣ሐኪም ወርቅነህ የምስጋና ደብዳቤ ጻፉላቸው:: ምኒስትር ወርቅነህ በእንግሊዝኛ የጻፉትን የምስጋና ደብዳቤ ወደ ዐረብኛ በመተርጎም የረዷቸው ሚካኤል ክርያኮ ነው::




ዮሴፍ እና ብንያም አሌክሳንድሪያ (ግብፅ) የተደረገላቸው አቀባበል

በዚህ ሁኔታ ዮሴፍ እና ብንያም ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ወደ ጦር ሜዳው አመሩ::



ABYSSINIAN MINISTER'S SONS LEAVE.—*Benjamin and Joseph Martin, sons of the Abyssinian Minister in London, saying goodbye to their younger brothers when leaving for Addis Ababa to answer the mobilisation order.*



ዮሴፍ እና ብንያም አሌክሳንድሪያ (ግብፅ) የተደረገላቸው አቀባበል

በዚህ ሁኔታ ዮሴፍ እና ብንያም ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ወደ ጦር ሜዳው አመሩ::

## ፲፱፻፳፰

ዮሴፍ አይሮፕላን አብራሪ ስለነበረ፣በቀይ መስቀል አይሮፕላን ቁስለኞችን በማመላለስ ሲሠራ ነበር። ጣሊያኖች፣የቀይ መስቀል ሰፈሩን በቦምብ ሲመቱ ድንኳናቸው እና አይሮፕላኑም ተቃጠሉ። የእንግሊዝ ቀይ መስቀል አዛዥ የነበረው ዶክተር ሜሊ፣መሐንዲስ እና መድፈኛው ታናሽ ወንድሙ ብንያም ወደሚገኝበት ጦር ሰፈር ዮሴፍ ሂዶ ከእነሱ ጋር ተቀላቀለ። ከብንያም ወርቅነህ ጋር የነበረው የጦር ግንባር በከፍተኛ ወኔ በመዋጋት ላይ እንዳለ የጣሊያን አይሮፕላኖች መጥተው በቦምብና በጋዝ ጢስ አጠቃቸው። ራስ ሙሉጌታ እና ሁለቱ ልጆቻቸው ሻለቃ ታደሰ እና ኮሎኔል አሥራት፣በጋለ ጦርነቱን በመሳተፍ ላይ እንዳሉ አባትና ልጆች በዚያን ዕለት ሕይወታቸውን ለአገራቸው ክብር መሰዋቱን ዶል ቫዮ እንዲህ ብሉ ጽፏል።


> ከቀትር በኋላ ጣሊያኖች ጨለቆትን ከያዙ በኋላ በባውዛ ምድባቸው በመታገዝ ኃይላችንን በማዳከምና ቦታችንን በማፈራረስ የሕንጣሉ መከላከያችንን አፈራርሰው ከተማዋን በቁጥጥራቸው ስር አደረጓት። የኢትዮጵያን ሠራዊት ሰልፍ እየቆራረጡ፣ወደ ኋላ ደጀናችን መስመር እየተቃረቡ መጡ። ኢትዮጵያን በቦምብ እና በመርዝ ጭስ ጭምር ለማጥቃት እንዲመቻቸው ራሳችንን ለመከላከል የፈፀምነው ድርጊት ነው ለማለት አስበው ነው። ማሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ጣሊያኖች ዓላማቸውን በተግባር በማዋል፣የኢትዮጵያን ሠራዊት በናፓል ቦምብ ጭምር በመውጋት ፈጁት። በዚህ መልኩ፣ድሉ ወደ ጣሊያኖች ወገን አጋደለ። ጣሊያኖችም ወደ መሐል አገር ገሰገሱ።
>
> የኢትዮጵያ ሠራዊት ከጦር ሜዳው አፈግፍጎ ወደ መጣበት አገር በመሄድ ላይ እያለ፣አሁንም የጣሊያን አይሮፕላኖች ወደ ኋላ የሚሸሹትን የኢትዮጵያ ሠራዊት እየተከታተለ በቦምብ እና በመርዝ ጋዝ ፈጃቸው። ይህን አሳዛኝ ወሬ አምባሳደር ወርቅነህ ሲሰሙ፣በአደባባይ ቆመው እንዲሁም በራዲዮ በመናገር የዓለም ሕዝቦችን የሞራል እና የቁሳቁስ እርዳታ ጠየቁ።
>
> የሞርታር ምድቦች እና ሌሎች ክፍሎች ቀሪውን ሥራ፣እያቀላጠፉ ነው። እኔ ባለሁበት በስሜኑ አቅጣጫ የመከላከያ መስመር የመትረየስ ጥይት ሳያቋርጥ እንደ ዝናብ መውረዱን ቀጥሏል። . . . . ዙሪያዬን ሲቃኝ የሰቆቃ ስሜት ሙሉ ሰውነቴን ያንቀጠቅጠኝ ጀመር። ብቻዬን ነበርኩ። በብዙ መቶዎች የሚቆጠር ሬሳ እዚያ ተራራማ ቦታ ያለውን ሜዳ ሞልቶታል። . . ከላዬ ላይ ያስማቋረጥ የሚተኩሱ ጥይቶችን ለመሸሽ መሬት ላይ በተረፈረፈው ሬሳ ላይ በደረቴ እየተሳብኩ እንደ ምንም ብዬ ረባዳማ ቦታ ደረስኩ። በደንብ የተከለለና ጥላ ከለላ የሚሆን ቦታ ነው። ወዲያው ብዙ የሠራዊት አባሎቻችን በደንብ ተቀበሉኝ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ከጣሊያኖች ጋር ባደረገው ጦርነት በታንክ፣በቦምብና በመርዝ ጋዝ በመጠቃቱ ብዙዎቹ በጦር ሜዳ መሰዋዕት ሲሆኑ የተረፉት ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ መንገድ ጀመሩ። ያም ሆኖ፣ወደ ኋላ ያፈገፈገውን ደካማ ሠራዊት እየተከታተሉ በቦምብና በመርዝ ጋዝ ከማጥቃት አልተቆጠቡም።

ስለ ጦርነቱ ሁኔታ ከኢትዮጵያ የሚመጣው ዜና እጅግ አሳዛኝና ተስፋ አስቆራጭ ነበር።

## ፲፱፻፳፱


የሐኪም ወርቅነህ ትንንሾቹ ልጆቻቸው፣ዳዊት እና ዮሐንስ ከአባታቸው ጎን እየተገኙ ልክ እንደ አባታቸው ንግግር ሲያደርጉ ነበር። ምኒስትር ወርቅነህ፣በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተፈፀመውን ሕገ ወጥ ድርጊት ያጋለጡት በራዲዮ እና በንግግር ብቻ አልነበረም። ሁኔታውን በበራሪ ወረቀቶችና በጋዜጦች፣በተለይም ለዴሊ ቴሌግራፍ (Daily Telegraph) በየቀኑ መግለጫ ይጽፉ ነበር። ምኒስትር ወርቅነህ ለራዲዮና ጋዜጣ ቃል አቀባዮች ደብዳቤ እየጻፉ "ጣሊያኖች አገሬን ወረሯት፣ንብረት ጠፋ፣ሕዝቤን በመርዝ ጭስ ፈጁት፣እናንት ሰላም ወዳድ የዓለም ሕዝቦች፣ይህ የጣሊያኖች ግፍ እንዲቆም እርዱን"። ኢትዮጵያ አንድ መቶ አይሮፕላን ቢኖራት አገሬ ጦርነቱን በአንድ ወር ውስጥ በድል ታጠናቅቅ ነበር።

ስለዚህ የዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝብ፣የጣሊያንን ወረራ ለመግታት እድንችል፣የሃሳብ እና የገንዘብም እርዳታ አድርጉልን።




ዮሴፍ እና ብንያም ወርቅነህ በጦር ሜዳ የመድፍ አተኳኮስ ሲቀይሱ

ትንሹ ልጃቸው ዮሐንስ ወርቅነህ በበኩሉ፣የአባቱን ጥሪ በመደገፍ የቀኝ እጁን ጨብጦ ቡጢውን ወደ ላይ እያወናጨፈ፣ከፍ ባለ ድምፅ "አንድ ፍልሚያ በኢትጵያ ውስጥ ጦርነት አይሆንም። እኛ ገና አልተሸነፍንም፣ትግላችን ይቀጥላል" እያለ ሲናገር፣ ወኔውን ያላደነቀ አዳማጭ አልነበረም። "ጊጢጢው ዳዊትም የታላቅ ወንድሙን ጩኸት በማስተጋባት "ፋስቶች የእኛን ወገኖች በመርዝ ጋዝ በጭካኔ ፈጇቸው።



ዮሴፍ እና ብንያም ወርቅነህ በጦር ሜዳ የመድፍ አተኳኮስ ሲቀይሱ

ታላቅ ወንድሞቼ ለአገራቸው ክብር ለመዋጋት ሄደዋል። ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደሆነ ገና አልታወቀም። ስለዚህ እባካችሁ እርዱን" በማለት፣ ሁለት እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ፣መና ከሰማይ እንደ እንደሚጠብቅ ሰው ይናገር ነበር። በዚህም ብዙ ሰዎች ወደ ሌጋሲዮኑ እየመጡ የሚችሉትን ያህል የገንዘብ እርዳታ ሰጡ። አሌክሳንድሮ ዴል ባዮ እና እንደ እሱ ከኢትዮጵያ ጎን ሆነው ለመዋጋት የመጡት የውጭ አገር ሰዎች፣ልብስ፣ ትጥቅ፣ስንቅና ወጪ የተከፈለው በዚህ መልኩ ከተገኘ ገንዘብ ነው። ዳዊት እና ዮሐንስ በመጮህና በማልቀስ የተዳከሙ መሆናቸውን የተረዱት የሐኪም ወርቅነህ አድናቂ፣ እመቤት ሬቨን ሮምፎርድ (Lady Raven Romford) እነዚህ ልጆች እፎይታ እንዲያገኙ በማሰብ ጥቅምት ፲፯ ቀን ወደ ቤታቸው ወስደው ለአንድ ሳምንት ያህል አዝናኗቸው።




ዮሐንስ ወርቅነህ ሃይድ ፓርክ (ሎንዶን) ቆሞ ስናገር

ሁለቱ ወንድማማቾች፣ዮሐንስ እና ዳዊት፣ይህን የመሰለ አሳዛኝ ንግግር ሲያደርጉ ከአዳማጮች መሐከል ልቡ ያልተነካ አንድም ሰው አልነበረም።



ጥቅምት ፲፰ ቀን፣የተከበሩ ናይጀሪያው ሚስተር ኦቡ (Mr. Obu) ወደ ሌጋሲዮኑ መጥተው ምዕራብ አፍሪካውያን ከኢትዮጵያ ጎን የሚቆሙ መሆናቸውን ለምኒስትሩ ገለጡላቸው። ጥቅምት ፳፩ ቀን፣ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የገንዘብ እርዳታ ለመሰብሰብ በሮያል አልበርት ሆል (Royal Albert Hall) ትልቅ ግብዣ አድርገው ነበር። የስብሰባው መሪዎች፣የካንተርበሪ ጳጳስ (Archbishop of Canterbury) እና ዶክተር ኦስሞ-ላንግ (Dr. Osmo-Lang) ናቸው። ንግግር ያደረጉት፣ሰር አውስቲን ቻምበርሌን (Sir Austin Chamberlain) እመቤት ቫዮሌት ቦኖም–ካርተር (Lady Violet Bonhom-Carter) ሚስተር ሄርበርት ሞሪሰን (Mr. Herbert Morrison) እና ሎርድ ሴሲል (Lord Cecil) ናቸው። ከዚህ ግብዣ በተገኘው ገንዘብ አይሮፕላን ጭምር ያለው የቀይ መስቀል ጓድ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ በቁ። ዶክተር ሜሊ (Dr. Melly) የእንግሊዝ ቀይ መስቀል መሪ ሆነው በማግስቱ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ስለተዘጋጁ ምሽቱ ላይ መጥተው ከሚኒስትር ወርቅነህ ጋር ከተወያዩ በኋላ ተሰነባብተው ተለያዩ።



የዮሖንስ ታናሽ፣ዳዊትም እንደ ወንድሙ ሲናገር

ዶክተር ሜሊ ቀደም ሲል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሕክምና ትምህርት ቤት ልክፈት ማለታቸው ይታወሳል። በግብዣው አማካይነት በተገኘው ገንዘብ ሁለት አይሮፕላኖች ተገዙ። በዶክተር ሜሊ የሚመሩ እንግሊዛውያን የሕክምና ባለሙያዎች እና አይሮፕላኑ ከሙሉ የሕክምና ዕቃ ጋር ወደ ጦር ሜዳ ተላከ። እንደዚሁም ከስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበር አንድ ተጨማሪ አይሮፕላን ስለ ተገኘ፣ በካውንት ቮን ሮዘን አብራሪነት ወደ ኮረም ተላከ።

ታላቅ ወንድሞቹ ለአገራቸው ክብር ለመዋጋት ሄደዋል። ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደሆነ ገና አልታወቀም። ስለዚህ እባካችሁ እርዱን" በማለት፣ ሁለት እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ፣መና ከሰማይ እንደ እንደሚጠብቅ ሰው ይናገር ነበር። በዚህም ብዙ ሰዎች ወደ ሌጋሲዮኑ እየመጡ የሚችሉትን ያህል የገንዘብ እርዳታ ሰጡ። አሌኽንድሮ ዴል ባዮ እና እንደ እሱ ከኢትዮጵያ ጎን ሆነው ለመዋጋት የመጡት የውጭ አገር ሰዎች፣ልብስ፣ ትጥቅ፣ስንቅና ወጪ የተከፈለው በዚህ መልኩ ከተገኘ ገንዘብ ነው። ዳዊት እና ዮሐንስ በመጮህና በማልቀስ የተዳከሙ መሆናቸውን የተረዱት የሐኪም ወርቅነህ አድናቂ፣ እመቤት ሬቨን ሮምፎርድ (Lady Raven Romford) እነዚህ ልጆች እፎይታ እንዲያገኙ በማሰብ ጥቅምት ፲፯ ቀን ወደ ቤታቸው ወስደው ለአንድ ሳምንት ያህል አዝናኗቸው።



ዮሐንስ ወርቅነህ ሃይድ ፓርክ (ሎንዶን) ቁሞ ሰናገር.

ሁለቱ ወንድማማቾች፣ዮሐንስ እና ዳዊት፣ይህን የመሰለ አሳዛኝ ንግግር ሲያደርጉ ከአዳማጮች መሐከል ልቡ ያልተነካ አንድም ሰው አልነበረም።



ጥቅምት ፲፰ ቀን፣የተከበሩ ናይጀሪያው ሚስተር ኦቡ (Mr. Obu) ወደ ሌጋሲዮኑ መጥተው ምዕራብ አፍሪካውያን ከኢትዮጵያ ጎን የሚቆሙ መሆናቸውን ለምኒስትሩ ገለጡላቸው። ጥቅምት ፳፩ ቀን፣ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የገንዘብ እርዳታ ለመሰብሰብ በሮያል አልበርት ሆል (Royal Albert Hall) ትልቅ ግብዣ አድርገው ነበር። የስብሰባው መሪዎች፣የካንተርበሪ ጳጳስ (Archbishop of Canterbury) እና ዶክተር ኦስሞ-ላንግ (Dr. Osmo-Lang) ናቸው። ንግግር ያደረጉት፣ሰር ኦውስቲን ቻምበርሌን (Sir Austin Chamberlain) እመቤት ቫዮሌት ቦኖም--ካርተር (Lady Violet Bonhom-Carter) ሚስተር ሄርበርት ሞሪሰን (Mr. Herbert Morrison) እና ሎርድ ሴሲል (Lord Cecil) ናቸው። ከዚህ ግብዣ በተገኘው ገንዘብ አይሮፕላን ጭምር ያለው የቀይ መስቀል ጓድ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ በቁ። ዶክተር ሜሊ (Dr. Melly) የእንግሊዝ ቀይ መስቀል መሪ ሆነው በማግስቱ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ስለተዘጋጁ ምሽቱ ላይ መጥተው ከሚኒስትር ወርቅነህ ጋር ከተወያዩ በኋላ ተሰነባብተው ተለያዩ።



የዮሐንስ ታናሽ፣ዳዊትም እንደ ወንድሙ ሲናገር

ዶክተር ሜሊ ቀደም ሲል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሕክምና ትምህርት ቤት ልክፈት ማለታቸው ይታወሳል። በግብዣው አማካይነት በተገኘው ገንዘብ ሁለት አይሮፕላኖች ተገዙ። በዶክተር ሜሊ የሚመሩ እንግሊዛውያን የሕክምና ባለሙያዎች እና አይሮፕላኑ ከሙሉ የሕክምና ዕቃ ጋር ወደ ጦር ሜዳ ተላከ። እንደዚሁም ከስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበር አንድ ተጨማሪ አይሮፕላን ስለ ተገኘ፣ በካውንት ቮን ሮዘን አብራሪነት ወደ ኮረም ተላከ።

እነዚያ የሕክምና ባለሙያዎች ድንኳን ተክለው፣በጦር ሜዳ ቆስለው የሚመጡትን ሰዎች ማከም ጀመሩ። አይሮፕላኖቹ የሚያገለግሉት መድኀኒት እና ቁስለኞቹን ለማመላለሻ ነበር። በድንኳኖቹ ጣራ ላይ የቀይ መስቀል ማኅበር አርማ ተስሎ በሩቁ ይታያል። ይሁን እንጂ፣የጣሊያን አይሮፕላን ነጂዎች የዓለምን የቀይ መስቀል ሕግ ጥሰው ድንኳኖቹን በቦምብ አቃጠሏቸው። ስለዚህ ሁኔታ፣ጃንሆይ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" በሚባለው መጽሐፋቸው ቅጽ ሁለት ውስጥ የሚከተለውን ጽፈዋል።

> የእንግሊዝን ቀይ መስቀል ድንኳን በቦምብካጠፉት በኋላ ሐኪሞቹ በኮረም አቅራቢያ ዋሻ ፈልገው እና አግኝተው ኢጣሊያኖች ሊደርሱበት የማይችሉበት ብርቱ ከለላ የሚሆን ዋሻ መስሏቸው በሽተኞቹን እና ቁስለኞቹን ሁሉ በዋሻው እያስገቡ አስተኝተዋቸው ነበር። እንደ አዳኝ ውሻ እያነፈነፉ ያንን ዋሻ ስለተከታተሉት ወደ ዋሻው ሌላ ቁስለኛ ለማስገባት፣የገቡትንም ለማውጣት የማይቻል ሆነ። ቁስለኞቹ እና ተሸካሚዎችም ለመተላለፍ አቃታቸው። ስለዚህ የእንግሊዝ ቀይ መስቀል ሐኪሞች ቁስለኞቹን በጣም ኀልቆ በሚታይ ካሚዮን ከማመላለስ ይልቅ፣እየተበታተኑ በመሄድ በበቅሎ እየጫኑ ማመላለስ የሚሻል በመሆኑ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ግድ ሆነባቸው።

የእንግሊዝ እና የስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበራት በጦርነት ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ ሲያደርጉ በነበሩበት ጊዜ የደረሰውን ግፍ ካውንት ቮን ሮዘን (Count Von Rosen) ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል።

> በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በበጋው ወራት፣የስዊድን ቀይ መስቀል ሐኪም ዶክተር ጉናር አጌ (Dr. Gunnar Aghe) ለሕዝብ ያሰሙት የነበረውን ንግግር አዳመጥሁ። ይኸውም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በግፍ ስለ መውረሯ ነበር። ሁኔታውን በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ካጠናሁ በኋላ፣በቅርቡ የሞቱት የስዊድን ንጉሥ ታናሽ ወንድም ልዑል ቻርልስ በዚያ ጊዜ የስዊድን የቀይ መስቀል ማኅበር የበላይ አዛዥ ነበሩ። ወደ እሳቸው ዘንድ ሄጀ፣ለኢትዮጵያ እርዳታ ያለ ደሞዝ እና ሌላም ጥቅም ሳልሻ ከነአውሮፕላኔ ከቀይ መስቀል መልዕክተኞች ጋር አብሮ ለመሄድ መወሰኔን በመግለጽ ፈቃድ ጠየቅሁ። ወዲያው ጥቂት ሰዎችና አእሮፕላን ነጂዎች ሊሄዱ መታሰቡን ከተረዱ በኋላ እኔም አብሬያቸው እንድሄድ መመረጤን ሰማሁ። በኅዳር ወር ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. መጨረሻ ግድም በመርከብ ጅቡቲ ደርሼ ከአውሮፕላን ጣቢያ SE – ACY ማርክ የነበረችውን አውሮፕላኔን ገጣጥምሁና ሞተሩን ስሞክር፣አንድ የደች ተወላጅ የሆነ ሰው እርዳታ ያደርግልኝ ስለነበረ፣በውልብልቢቱ አጠገብ መኖሬን ዘንግቶ ሞተሩን ስለ አስነሳ ቀኝ ጭኔን ቆሰልሁ። ሆኖም ያልቆሰለውን እግሬን ከራዳር መርገጫው ጋር አስሬ በድሬዳዋ በኩል አድርጌ ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. አዲስ አበባ መግባት ቻልሁ።
>
> ከዳንሁ በኋላ "አባ ቃኘው" ይባል የነበረውን FOCKER F. VII ማርክ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል አውሮፕላን እንድነዳ በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ታዘዝሁ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያን አውሮፕላኖች ሁሉ ያስተዳድሩ የነበሩት ካፒቴን ሚሽካ ባቢቼፍ ነበሩ።



> በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩት የአውሮፕላን ጣቢያዎች ቁጥር በጣም አናሳ ከመሆኑ በላይ፣ከአዲስ አበባ በስተቀር የቤንዚን መሙያ ስፍራ ስላልነበረ ለመመለሻ የሚሆን ነዳጅ ጭኜ ወደ ጦር ግንባር መብረርና ከተራራዎች መካከል ማረፊያ ስፍራ ፈልጌ ቤንዚን እየሞላሁ መንገዴን መቀጠል ነበረብኝ። በዚህ አኳኋን ሰባ አምስት ጊዜ ከበረርኩ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጥቂት ጊዜ አስቀድሞ አውሮፕላኑ ("አባ ቃኘው") ኮረም ላይ በጠላት ስለተቃጠለ በኢትዮጵያ የነበረው በቀይ መስቀል እርዳታ የተላከውን አውሮፕላን ከካይሮ እንዳመጣ ታዝዤ ሄድሁ። እዚያ እንደ ደረስኩ አሳዛኙን የኢትዮጵያን ሠራዊት ድል መሆን ሰማሁ። ወዲያው እኔ በመንግሥታት ማኅበር ውስጥ ሆኜ ፎከር የምትባለዋን አውሮፕላን እየነዳሁ በጎሬ አቅራቢያ ማረፊያ ቦታ ፈልጌ በራስ እምሩ ይመራ ከነበረው ጦር ጋር መገናኛ እንድከፍት ስለተደረገ ተልኮዬን ያለ አንዳች እንቅፋት ለመፈጸም ቻልኩ።
>
> ቢሆንም ወደ ኬኒያ ጠረፍ ይሸሹ የነበሩትን የስዊድንና የኖርዌይ ቀይ መስቀል ሠራተኞችን ላገኛቸው አልቻልኩም። ጎሬ ስመለስ በአውሮፕላን ከወሰድኳቸው ሰዎች ውስጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ልጅ፣ፊታውራሪ ሥላሴ አንዱ ነበሩ። ወጣት ፊታውራሪ ሥላሴ እንደገና ተመልሰው ለአገራቸው ሲከላከሉ በጣሊያኖች ተይዘው በግፍ ተገድለዋል። በነሐሴ ወር ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ወደ ሉንደን እንድመለስ በታዘዝኩበት ሰሞን ጎሬ መያዙን ሰማሁ። የኢጣሊያኖችን አረመኔነት በዓይኔ ስላየሁ እና በግፍም ኢትዮጵያን ስለወጉ እና ስለ ወረሩ ልቤ በኀዘን ስለተነካ፣ ምናልባት ኢትዮጵያ ነፃነቷን ብታገኝ እርዳታዬን ለመስጠት በተስፋ ፀንቼ እቆያለሁ በዬ ወሰንኩ።

ከዚህ የካውንት ቮን ሮዘን ትረካ የምንገነዘበው፣ጣሊያኖች ምንኛ ጭካኔ እና ሕግ ወጥ ተግባር ይፈጽሙ እንደ ነበረ ነው። የጣሊያን ወራሪ ኃይል የፈጸመው በደል በሠራዊታችን ላይ ብቻ ሳይሆን፣በዓለም መንግሥታት ከለላ ስር ያለውን የቀይ መስቀል ቦታዎችንና ሐኪሞችን ጭምር በአውሮፕላን እንዳጠቁ ከዚህ ክፍ ብሎ የቀረቡት የምስክር ቃሎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። እዚህ ላይ፣ስለ ካውንት ቮን ሮዘን የማውቀውን ያህል ጥቂት መናገር ያለብኝ ይመስለኛል። ካውንት ቮን ሮዘን፣ከስዊድን ስመጥር ቤተሰብ የተወለዱ ሰው ናቸው። ስዊድን ውስጥ የራሳቸው የሆን ከቤተ መንግሥት የማይተናነስ መኖሪያ ሕንፃ እና ሰፊ መሬት አላቸው። ከዚያም የራሳቸውን አይሮፕላን ገዝተው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከስዊድን የቀይ መስቀል ማኅበር ጎን ቆመው ሰብአዊ እርዳታ ሲሰጡ ነበር። እሳቸው ከተናገሩት ቃል እንተረዳነው ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን በመውረሯ ተቆጭተው ከስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበር ጋር በመሆን የተቻላቸውን ያህል ኢትዮጵያን ረድተዋል። ጣሊያኖች ማሸነፋቸው ተረጋግጦ ወደ ዋናው ከተማ ማምራታቸውን ሲያውቁ፣ ካውንት ቮን ሮዘን ወደ አገራቸው ለመሄድ ሲነሱ ቃል በገቡት መሠረት፣ነጻነታችን እንደ ተመለሰ ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ወዲያውኑ የኢትዮጵያ የአየር ኃይል ማሠልጠኛ እንዲቋቋም ከረዱት ሰዎች አንዱ በመሆናቸው፣አመራሩን እንዲይዙ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቀዱላቸው።

በአመራር ሰጭነታቸው ወዲያውኑ ሌሎች ስዊድናዊያን አውሮፕላን አብራሪዎች እና ሜካኒኮች አስመጥተው ሥልጠናው ተጀመረ። ዛሬ የኢትዮጵያ አየር ኃይልና እንዲሁም የአየር መንገዳችን ካለበት ደረጃ ለመድረስ የበቃው እሳቸው ከጀመሩት የሥልጠና ጥንስስ በመነሳት ነው።
ካውንት ቮን ሮዘን ለኢትዮጵያ የሠሩት ሌላ ትልቅ ነገር ደግሞ በወሎው ረሀብ ጊዜ ያደረጉት ሰብአዊ እርዳታ ነው። ይኸውም፣ከ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ጀምሮ በወሎ እና በትግራይ ሕዝብ ላይ የተከሰተውን በረሀብ አለንጋ መጠብጠብ ለመከላከል፣ከላየንስ ክለብ እና ከሌሎች ዓለም አቀፍ እርዳታ ሰጪዎች የሚገኘውን እህል ወደ ተረጂዎቹ ቶሎ ማድረስ መቻላቸው ነው። እህሉን በመኪና ማጓጓዝ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ስለ ሆነ፣ይህን ችግር የተረዱት ቮን ሮዘን፣የምግብ እርዳታውን ለተረጂዎቹ በቶሎ ለማድረስ አይሮፕላናቸውን ዝቅ አድርገው በማብረር ከአየር ላይ እህል በመወርወር በፈጸሙት ተግባር በብዙ መቶ ሺሕ የሚቆጠሩ ሰዎች ከሞት አድነዋል። ይህን ተግባራቸውን ድርቅ ባለበት ቦታ ሁሉ ሲያከናውኑ ቆይተዋል። በ፲፱፻፸ዎቹ መጀመሪያ ላይ፣በሲያድ ባሬ የሚመራው የሱማሌ ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ ወረራ ፈጸመ። በዚህ ወረራ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከመንደራቸው በመፈናቀላቸው እርዳታ መስጠት አስፈለገ።

ከወረራው ቀደም ብሎ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ተቋቁሞ ስለነበረ፣የድርጅቱ ሥራ መሪ አቶ ሽመልስ አዱኛ ከሥራ ባልደረቦቻቸውና ከካውንት ቮን ሮዘን ጋር ሆነው፣የችግሩን መጠን ለመገምገምና ሁኔታውን ለማጥናት ወደ ጎዴ ሄዱ። የሱማሌ ወራሪዎች በድንገት ደርሰው አደጋ ሲጥሉ፣በርካታ ሰዎች ተገደሉ። በዚያን ዕለት ከተገደሉት መሐከል ትልቁ የኢትዮጵያ ወዳጅና ባለውለታ ካውንት ቮን ሮዘን አንዱ ናቸው።አቶ ሽመልስ አዱኛ እና ጥቂት ሰዎች ሕይወታቸው ተረፈ። ሌሎች መኮንኖች ሲቪሎች እና ሕፃናት ተማርከው ወደ ሞቃዲሾ ተወስደው ስለ ነበረ፣በሕይወት የተረፉት በእስር ቤት ከማቀቁ በኋላ፣በዓለም ቀይ መስቀል ውትወታ ከሞት የተረፉት ከ፲፩ ዓመት በኋላ ወደ አገራቸው ለመግባት በቅተዋል።
የጣሊያን ፋሽስቶች በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጽሙት ወረራና በደል አንዳንድ የዓለም ማኅበር አባላትን ስላስቆጣ፣ኅዳር ፰ ቀን፣በጣሊያን መንግሥት ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ መጣሉ ተነገረ። በዚህ ውሳኔ የተናደደው የፋሽስቶች መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ "በጣሊያን ላይ የዓለም ሕዝብ የጥፋት ጣቱን ቀስሯል" በማለት በአደረገው ቅስቀሳ፣መላው የጣሊያን ሕዝብ ከጎኑ እንዲቆም ረዳው።

ብሄራዊ ስሜቱን በዚህ ዓይነት ፕሮፓጋንዳ ስለቀሰው መላው የጣሊያን ሕዝብ ማለት ይቻላል፣ወንዱም ሴቱም የጋብቻ ቀለበቶቻቸውን፣የአንገት ሀብላቸውን ሳይቀር የጦርነቱን ወጪ ለመሸፈኛ እንዲሆን በመስጠታቸው፣ የኢኮኖሚ ማዕቀቡን ፋይዳ ቢስ አደረገው። ሆኖም የእንግሊዝ መንግሥት በኩል ማዕቀብ እንዲደረግና በስዊዝ ካናል በኩል የጦር መሣሪያ እንዳያልፍ ኬላው ዝግ እንዲሆን ታቅዶ ነበር። ነገር ግን የእንግሊዝ መንግሥት ይህን የመሰለውን እርምጃ ለመውሰድ ከጣሊያን ጋር ለመዋጋት ዝግጁ አልነበረም እና የጣሊያንን ቁጣ ሲገታው አልቻለም።



ሐኪም ወርቅነህ በበኩላቸው የጣሊያንን ግፍ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያጋልጡ ነበርና፣ሕንድ አገር ኗሪ የነበሩት፣የመንፈስ አባታቸው የሐምሌት ክላርክ (Hamlet Clark) ልጅ፣ዳዊት ክላርክ (David Clark) ኅዳር ፲፰ ቀን መጥቶ ስለ ወቅቱ ሁኔታ አወያያቸው። ቀደም ሲል የተጸፈው የጣሊያን አየር ኃይል የቀይ መስቀል ድንኳኖች በቦምብ ማጋየት እና በአካባቢው የነበሩትን ሐኪሞችና ሠራተኞች በመርዝ ጋዝ ማጥቃታቸው በታኅሣሥ ወር በዜና ማሰራጫዎች ይፋ ወጣ። በዚህ ምክንያት የሎንዶን ከተማ ከንቲባ ተለዋጭ መቀመጫ በሆነው ማንሽን ሐውዝ (Mansion House) ታኅሣሥ ፫ ቀን ትልቅ ስብሰባ ተካሄደ። በዚያን ቀን ንግግር ያደረጉት፣የካንተርበሪ ጳጳስ (Archbishop of Canterbury) ሎርድ ሉጋርድ (Lord Lugard) ሰር አውስቲን ቻምበርሊን (Sir Austin Chamebrlain) እና ሚስስ ሳንድፎርድ (Mrs. Sandford) ነበሩ። ሚስስ ሳንድፎርድ ኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ዘመን ነዋሪ የሆኑና አዲስ አበባ ውስጥ በሚደረገው ማኅበራዊ ሥራ ንቁ ተሳትፎ ያላቸው ሴት ናቸው። ታኅሣሥ ፲፩ ቀን፣ለኢትዮጵያ ወገናዊነት የሚያሳዩት ሰር አንቶኒ ኤደን (Sir Anthony Eden) የእንግሊዝ ጠቅላይ ምኒስትር ሆነው ተመረጡ። የእኛ ምኒስትር ሐኪም ወርቅነህ የፈረንጆቹን አዲስ ዓመት ዋዜማ፣ከልጆቻቸው፣ከእመቤት ኤቴል ጀምስ (የቀድሞዋ ኤቴል ፋብሪከስ) እና ከሚስስ ያማር ሆላንድ ጋር በዓሉን አከበሩ። ቀደም ሲል እንደ ተገለጠው፣የኢትዮጵያ ሠራዊት በቆራጥነት ተዋግቶ ወደ ማሸነፉ ሲቃረብ፣ጣሊያኖች በቦምብና፣በዓለም መንግሥታት በተከለከለ የመርዝ ጋዝ በመጠቀም፣ጦሩን ፈጁት። በዚህ አኳኋን በጦር ሜዳ የሚዋጋቸውን ይቅርና እየሸሸ ወደ ኋላ የሚያፈገፍገውን በአይሮፕላን እየተከታተሉ በቦምብና በመርዝ ጋዝ ፈጁት። የሠራዊቱን መዳከም ሲያውቁ፣ጃንሆይ ሚያዚያ ፳፪ ቀን አዲስ አበባ ገቡ። ንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥታቸው እንደ ደረሱ፣በሽምቅ ውጊያ ለመከላከል ምቹ ነው ወደ ተባለው ወደ ጎሬ ሂደው፣መንግሥታቸውን መልሰው ለማቋቋም አቀዱ። በዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ባለሥልጣናት ተሰባስበው ሰፋ ያለ ክርክር ተደረገ። የባለ ሥልጣናቱ ውሳኔ "ጃንሆይ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከመሄድ ይልቅ፣ ወደ አውሮፓ ሄደው (ባህር ተሻግረው) በመንግሥታት አደባባይ ኢትዮጵያ ፍርድ እና እርዳታ እንድታገኝ ቢታገሉ ይሻላል" በሚል ተወስኖና ሚያዚያ ፳፬ ቀን አዲስ አበባ ላይ ከነቤተሰቦቻቸው በባቡር ተሳፍረው ሚያዚያ ፳፭ ቀን በአራት ሰዓት ጅቡቲ ገቡ። በመቀጠል ወደ ኢየሩሳሌም ተሸገሩ። ከአገር የወጡበት ምክንያት፣ኢትዮጵያ በኃይል የተወረረች አገር በመሆኗ ጣሊያን በመሣሪያ ብዛት፣ኢትዮጵያ ገብታ እስከ አሁን የያዘችውን ስፍራ ለቅቃ እንድትወጣ ያለም መንግሥታት ማኅበር የተቻላቸውን ያህል ግፊት እዲያደርጉ ለመጠየቅ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን ሐሳባቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፈው ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ጄኔቭ ለሚገኘው የዓለም መንግሥታት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ላኩ። በተጨማሪም እሳቸው ራሳቸው በአካል ተገኝተው ለዓለም መንግሥታት አቤቱታ ለማቅረብ እንዲመቻቸው ወደ ሎንዶን ለመግባት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ሙከራ ማድረግ አስፈለገ።

* ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፡- ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ

ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሎንዶን መምጣት የእንግሊዝ መንግሥት ጥሩ ፊት ባያሳይም፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በቅርብ ለሚያውቋቸው የመንግሥት ባለ ሥልጣናትና ታላላቅ ሰዎች የጃንሆይን መምጣት እንዲደግፉ ብዙ ጥረት አደረጉ። ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው፣እንግሊዞች እና አሜሪካኖች የእሳቸውን ወደ ግዛታቸው እንዲገቡ ሁለቱም መንግሥታት አይፈልጉም ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት የፋሽስት እና ናዚስት መንግሥታት በሕዝባቸው ድጋፍ ጉልበታቸው እየፈረጠመ፣የጦር ኃይላቸው በመሣሪያ ምርት እየተጠናከረ ከመጣው ሁለት አገሮች ጋር ላለመጣላት የሚያደርጉት ጥንቃቄ መሆኑ ግልፅ ነበር። ይሁን እንጂ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣ከውጭ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በምሥጢር ተነጋግረው በተገኘው አዎንታዊ መልስ፣ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ህቡዕ ስምምነት መሠረት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሎንዶን ለመሄድ ተዘጋጁ።

አንደኛ፡- ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመንግሥት መሪነት ሳይሆን እንደ አንድ ግለሰብ ለሕክምና ሎንዶን እንዲገቡ*

ሁለተኛ፡- አብረዋቸው የሚመጡ አጃቢዎቻቸው ቁጥር ከአምስት ሰው እንዳይበልጥ*

ሦስተኛ፡- ሎንዶን ሲደርሱ ምንም ዓይነት የክብር አቀባበል እንደማይደረግ

አራተኛ፡- ሎንዶን በሚቆዩበት ጊዜ ምንም ዓይነት ይፋ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳያደርጉ

አምስተኛ፡- በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ አደጋ እንዳይደርስ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው

እነዚህ አምስት ዓቢይ ነጥቦች ይፋ ባይወጡም ከቃል ስምምነት የተደረሰው፣በአንድ በኩል፣የእንግሊዝ እና የጣሊያን መንግሥት እንዳይቃቃሩ ስለሚረዳ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ንጉሠ ነገሥቱን በመወከል፣ምኒስትሩ (ሐኪም ወርቅነህ) ስለ የኢትዮጵያ ጉዳይ ተፈላጊውን ሥራ ለመሥራት እንዲያመች ታስቦ ነው። በዚህ ሁኔታ ጃንሆይ ወደ እንግሊዝ አገር ለመግባት እንዲችሉ የተጠየቀው ፈቃድ በመገኘቱ፣ግንቦት ፲፭ ቀን ከኢየሩሳሌም ተነስተው ሃይፋ ደረሱ እና ኬፕታውን በሚባል የእንግሊዝ የጦር መርከብ ላይ ተሳፍረው ወደ ጅብራልታር ተጓዙ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄዱ መሆናቸው እንዳይታወቅ፣እስከ ጅብራልታር ድረስ ተሳፍረው ከመጡበት የእንግሊዝ መርከብ ወረዱ። ከዚያም የአርያን ላይን (Aryan Line) ንብረት በሆነው የንግድ መርከብ ተሳፍረው ሳውዝ ሃምተን ወደብ ደረሱ። ቀደም ሲል በተደረገው ህቡዕ ስምምነት መሠረት "ሎንዶን ሲደርሱም እንደ ግል መንገደኛ ተቆጥረው በአገር መሪ ደረጃ አቀባበል አልተደረገላቸውም"*። ሆኖም ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣የእሳቸውን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ ታላላቅ ሰዎችን ይዘው ወደ ሳውዝ ሃምፕተን (South Hampton) ወደብ ሄዱ። እነዚህ የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑት ሰዎች ወደቡ ላይ ቆመው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ይጠባበቁ ነበር።



መርከቡ መልሕቅ ከጣለ በኋላ፣ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ መርከቡ ውስጥ ገብተው ከጃንሆይ ጋር ተገናኙ። ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱን አስቀድመው፣ሐኪም ወርቅነህ እና አቶ ወልደ ጊዮርጊስ (በኋላ ጸሐፊ ትዛዝ) እየተከተሉ ሌሎች አብረዋቸው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ጭምር ከመርከብ ወረዱ። መርከቡ ወደብ ጃንሆይን ለመቀበል የመጡት እነዚያ ጥቂት የኢትዮጵያ ወዳጆች፣ረጅም ዕድሜ ለንጉሥ ኃይለ ሥላሴ፣የኢትዮጵያ ነጻነት ለዘላለም ይከበር እያሉ መልካም አቀባበል አደረጉላቸው። በዚህ የአቀባበል ሥርዓትም ይሁን በሌላ ጊዜ ማንም የእንግሊዝ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተገናኝቶ አያውቅም። ወደ እንግሊዝ አገር እንዴት እንደመጡ "ሕይወቴ እና የኢትዮጵያ እርምጃ" በሚባለው መጽሐፍ ጃንሆይ ከዚህ የሚከተለውን ጽፈዋል።

> በኋላ እቴጌንና ቤተ ዘመዶቻችንን፣ከእኛም ጋር የመጡትን የጦር አለቆች በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አድርገን፣ከልጆቻችን አልጋ ወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰንንና የሐረር መስፍን መኮንንን፣ሌቴቱ ልጃችንን ፀሐይን፣ለሰሜኑ ጦር ጠቅላይ (አዛዥ) አድርገን የነበረውን ራስ ካሣን አስከትለን በግንቦት ፲፭ ቀን ከኢየሩሳሌም ወደ ሐይፋ ወረድን። ከዚያም ኬፕታውን በሚባል በእንግሊዝ የጦር መርከብ ተሳፍረን ወደ ጅብራልታር ተጓዝን። ከጅብራልታርም አሪያን ላየን በሚባል በመንገደኞች መርከብ ተዛውረን ሳውት ሃምቶን በሚባል በእንግሊዝ የወደብ ከተማ ከመርከብ ወርደን ከዚያ በባቡር ወደ ሎንደን ተጓዝን።




ሐኪም ወርቅነህ ጃንሆይን መርከብ ውስጥ ተቀብለዋቸው አብረው ሲወርዱ






ሐኪም ወርቅነህ ጃንሆይን መርከብ ውስጥ ተቀብለዋቸው አብረው ሲወርዱ




ከዚህ ከፍ ብ፤ ባሉት ፎቶግራፎች እንደሚታየው፣ግርማዊነታቸው ሎንዶን እንደገቡ ክልዑል አልጋ ወራሀ አስፋወሰን ፣ልዕልት ፀሓይእና ከልዑል መኮንን ጋር በመሆን የሌጋሲዮኑን ቤትና ግቢ ጎበኙ።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው፣ሐኪም ወርቅነህ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ለማግኘት ለጋዜጠኞችና ለሌሎችም አገራችንን ይደግፋሉ ተብለው ለሚታሰቡ ሁሉ በደብዳቤም በንግግርም ያሰሙ ነበር። ግርማዊነታቸው ወደ እንግሊዝ አገር የመጡበት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን ስሞታ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ለማቅረብ ስለነበረ፣ይህን ለማስፈፀም የሚቻልበትን መንገድ ማፈላለጋቸውን እየቀጠሉ ሳለ ግርማዊነታቸው ወደ ጄኔቭ ሄደው ንግግር እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ደብዳቤ አዘጋጁ። ይህን ደብዳቤ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ለመስጠት ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንዞ ታእዛዝ ወደ ገኔቭ ሄዱ። እንደተመኙትም ንጉሠ ነገሥቱ ንግግር እንዲያደርጉ በመፈቀዱ ይህን ቸር ወሬ ወዲያውኑ ለጃንሆይ በቴሌግራም አሳውቀው ሁለቱም አብረቀው ወደ ሎንዶን ተመለሱ። ይህንም ሕይወቴ እና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚባለው መጽሐፍ ቅጽ ፪ ገጽ ፴፬ ላይ ጃንሆይ እንደሚከተለው ገልጸውታል። "......... አዛዥ ወርቅነህ ግን ለጉባዔው የሚቀርበውን ራፖር ይዘው አስቀድመው ሄደው ስለነበረ፣ከአቶ ሎሬንዞ ጋራ ሆነው በጄኔቭ ሲያስተናግዱ ሰነበቱ" ብለዋል።









ከዚህ ከፍ ብ፤ ባሉት ፎተግራፎች እንደሚታየው፣ግርማዊነታቸው ሎንዶን እንደገቡ ክልዑል አሊጋ ወራህ አስፋወሰን ፣ልዕልት ፀሓይእና ከልዑል መኮንን ጋር በመሆን የሌጋሲዮኑን ቤትና ግቢ ጎበኙ።

ክፍ ብሎ እንደተገለጸው፣ሐኪም ወርቅነህ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ለማግኘት ሊጋዜጠኞችና ለሌሎችም አገራችንን ይደግፋሉ ተብለው ለሚታሰቡ ሁሉ በደብዳቤም በንግግርም ያሰሙ ነበር። ግርማዊነታቸው ወደ እንግሊዝ አገር የመጡበት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን ስሞታ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ለማቅረብ ስለነበረ፣ይህን ለማስፈፀም የሚቻልበትን መንገድ ማፈላለጋቸውን እየቀጠሉ ሳለ ግርማዊነታቸው ወደ ዤንቭ ሄደው ንግግር እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ደብዳቤ አዘጋጁ። ይህን ደብዳቤ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ለመስጠት ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንዞ ታእዛዝ ወደ ገኔቭ ሄዱ። እንደተመኙትም ንጉሠ ነገሥቱ ንግግር እንዲያደርጉ በመፈቀዱ ይህን ቸር ወሬ ወዲያውኑ ለጃንሆይ በቴሌግራም አሳውቀው ሁለቱም አብረቀው ወደ ሎንዶን ተመለሱ። ይህንም ሕይወቴ እና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚባለው መጽሐፍ ቅጽ ፪ ገጽ ፴፬ ላይ ጃንሆይ እንደሚከተለው ገልጸውታል። “ . . . . . . . . አዛዥ ወርቅነህ ግን ስጉባዔው የሚቀርበውን ራፖር ይዘው አስቀድመው ሄደው ስለነበረ፣ከአቶ ሎሬንዞ ጋራ ሆነው በጄኔቭ ሲያስተናግዱ ስነበቱ” ብለዋል።

ግርማዊነታቸው ዤኔቭ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ መፈቀዱ በመታወቁ ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንስ ታእዛዝ የግርማዊነታቸውን ንግግር እንዲያዘጋጁ ታዘዙ:: ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንዞ ታእዛዝ ሁለቱም በየበኩላቸው ንግሩን አዘጋጁ:: ጽሑፉ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ጃንሆይ እንዲያነቡት ሰጧቸው:: ጽሑፎቹን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጥሞና አንብበው ሁለቱንም ጽሑፎች ወደዷቸው:: ይሁን እንጂ፣ ሎሬንዞ ታዕዛዝ የጻፉትን ጃንሆይ ይበልጥ ስለ ወደዱት ሐኪም ወርቅነህ ከጻፉት ውስጥ ተመርጦ ከሎሬንዞ ታዕዛዝ ጽሑፍ ጋር ተዋህዶ ንግግሩ እንዲዘጋጅ ወሰኑ:: በዚህ መሰረት ንግግሩ በአማርኛ ተዘጋጅቶ ቀረበላቸው::



ሐኪም ወርቅነህ የንግግሩን ረቂቅ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያሳዩ

ከዚያም ወደ ፈረንሳይኛና ሌሎች ቋንቋዎች ተተረጎመ:: ይህን መሰል ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ጃንሆይ ወደ ዤኔቭ ለመሄድ ተዘጋጁ::



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐኪም ወርቅነህን እና ሌሎችንም ሰዎች አስከትለው ለዓለም ማኅበር አባላት ንግግር ለማድረግ ጀኔቭ ሲደርሱ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው::



ጃንሆይ ጀነቭ ሲደርሱ ሞቅ ያለ አቀባበል ሲደረግላቸው በአቀባበሉ ሥርዓት አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የተደሰቱ መሆናቸው ባሳዩት ፈገግታ ይታወቃል

ከዚህ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ንግግሩ በፈረንሳይኛ እና በሌሎችም ቋንቋዎች የተዘጋጀ ቢሆንም፣ግርማዊነታቸው በአማርኛ ቋንቋ ለማሰማት የጉባዔውን ሊቀ መንበር አስፈቀዱ:: ንግግር ማድረግ ሲጀምሩ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት ጣሊያኖች እና የእነሱ አጫፋሪዎች በፉጨት እና በዘለፋ ንግግራቸውን እንዲያቋርጡ ለማድረግ ማወክ ሞክረው ነበር:: የሚበጠብጡትን ሰዎች ሰብሳቢው ካስወጧቸው በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጀምረው የነበሩትን ንግግር ጨረሱ:: ንጉሠ ነገሥቱ ረብሻው መንፈሳቸውን ሳይበግረው፣ደርበብ ባለ ሞገስ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ተናግረው ሲጨርሱ አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ:: የዚያን ዕለቱ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንግግር፣ከዓለም ታላላቅ ታሪካዊ ንግግሮች አንዱ በመሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ሲጠቀስና ለወደፊትም ሲጠቀስ ይኖራል:: ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመችውን በደል በዚህ መልኩ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ካሳወቁ በኋላ ወደ ሎንዶን ተመለሱ:: ከዚያ በኋላ ሁኔታው በሚፈቅደው መንገድ ኢትዮጵያ የተፈጸመባትን በደል እንድታሰማ የእንግሊዝ መንግሥት ፈቃደኛ ባይሆንም አንድ ሁለት ጊዜ ከብዙሃን መገናኛ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ፣ጣሊያን ቀኙን ማግኘቷ ሲታወቅ ብዙዎቹ ዜጎቿ ወደ ሽምቅ ውጊያ ገቡ::

ግርማዊነታቸው ዤኔቭ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ መፈቀዱ በመታወቁ ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንሶ ታእዛዝ የግርማዊነታቸውን ንግግር እንዲያዘጋጁ ታዘዙ:: ሐኪም ወርቅነህ እና ሎሬንዞ ታእዛዝ ሁለቱም በየበኩላቸው ንግሩን አዘጋጁ:: ጽሑፉ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ጃንሆይ እንዲያነቡት ሰጧቸው:: ጽሑፎቹን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጥሞና አንብበው ሁለቱንም ጽሑፎች ወደዷቸው:: ይሁን እንጂ፣ ሎሬንዞ ታዕዛዝ የጻፉትን ጃንሆይ ይበልጥ ስለ ወደዱት ሐኪም ወርቅነህ ከጻፉት ውስጥ ተመርጦ ከሎሬንዞ ታዕዛዝ ጽሑፍ ጋር ተዋህዶ ንግግሩ እንዲዘጋጅ ወሰኑ:: በዚህ መሰረት ንግግሩ በአማርኛ ተዘጋጅቶ ቀረበላቸው::



ሐኪም ወርቅነህ የንግግሩን ረቂቅ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያሳዩ

ከዚያም ወደ ፈረንሳይኛና ሌሎች ቋንቋዎች ተተረጎመ:: ይህን መሰል ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ጃንሆይ ወደ ገኔቭ ለመሄድ ተዘጋጁ::



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐኪም ወርቅነህን እና ሌሎችንም ሰዎች አስከትለው ለዓለም ማኅበር አባላት ንግግር ለማድረግ ጄኔቭ ሲደርሱ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው::



ጃንሆይ ጄነቭ ሲደርሱ ሞቅ ያለ አቀባበል ሲደረግላቸው በአቀባበሉ ሥርዓት አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የተደሰቱ መሆናቸው ባሳዩት ፈገግታ ይታወቃል

ከዚህ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ንግግሩ በፈረንሳይኛ እና በሌሎችም ቋንቋዎች የተዘጋጀ ቢሆንም፣ግርማዊነታቸው በአማርኛ ቋንቋ ለማሰማት የጉባዔውን ሊቀ መንበር አስፈቀዱ:: ንግግር ማድረግ ሲጀምሩ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት ጣሊያኖች እና የእነሱ አጫፋሪዎች በፉጨት እና በዘለፋ ንግግራቸውን እንዲያቋርጡ ለማድረግ ማወክ ሞክረው ነበር:: የሚበጠብጡትን ሰዎች ስብሳቢው ካስወጧቸው በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጀምረው የነበሩትን ንግግር ጨረሱ:: ንጉሠ ነገሥቱ ረብሻው መንፈሳቸውን ሳይበግረው፣ደርበብ ባለ ሞገስ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ተናግረው ሲጨርሱ አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ:: የዚያን ዕለቱ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንግግር፣ከዓለም ታላላቅ ታሪካዊ ንግግሮች አንዱ በመሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ሲጠቀስና ለወደፊትም ሲጠቀስ ይኖራል:: ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመችውን በደል በዚህ መልኩ ለዓለም ምንግሥታት ማኅበር ከአሳወቁ በኋላ ወደ ሎንዶን ተመለሱ:: ከዚያ በኋላ ሁኔታው በሚፈቅደው መንገድ ኢትዮጵያ የተፈጸመባትን በደል እንድታሰማ የእንግሊዝ መንግሥት ፈቃደኛ ባይሆንም አንድ ሁለት ጊዜ ከብዙሃን መገናኛ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ፣ጣሊያን ቀኙን ማግኘቷ ሲታወቅ ብዙዎቹ ዜጎቿ ወደ ሽምቅ ውጊያ ገቡ::

ጥቂቶቹ ደግሞ ወደ ጎረቤት አገርና እስከ ቅርብ ምሥራቅ፣ማለት ግብፅና ኢየሩሳሌም ተሰደዱ። አዲስ አበባ ውስጥ የእንግሊዝ አምባሳደር የነበሩት ሰር ባርተን (Ambassador Sir Barton) እንዲሁም ቄስ ማቲው (Rverened Mathew) እና ሌሎችም ሆነው የኢትዮጵያን ስደተኞች ለመርዳት አንድ ማኅበር ሎንዶን ውስጥ አቋቋሙ። በርካታ ሰዎች የሚሰጡትን የእርዳታ ገንዘብ ቄስ ማቲው፣ወደ ካይሮና ኢየሩሳሌም በመሄድ ስደተኞችን ይረዱ ነበር። ቄስ ማቲው እና የእንግሊዝ ቀይ መስቀል ማኅበር አባላት ለኢትዮጵያ ያደረጉት ውለታ ምንጊዜም የማይረሳ ነው።

አሌክሳንድሮ ዴል ቫዮ የእንግሊዝ ቀይ መስቀል ወደሚገኝበት ኮረም ሂዶ ስለ ነበረ ከዮሴፍ እና ብንያም ጋር በጦር አውድማ ላይ ተገናኙ። ጣሊያኖች ኮረም የነበረውን የቀይ መስቀል ጊዜያዊ ሰፈር በቦምብ እንዳቃጠሉ ዶክተር ሜሊ፣ዴል ባዩ፣ዮሴፍ እና ብንያም፣ከአደጋው በመትረፋቸው ከዚያ አደገኛ ቦታ ከሚያፈገፍገው ሠራዊት ጋር አዲስ አበባ ገቡ። አዲስ አበባ ውስጥ "የጥይት ተኩስ በየቦታው ይሰማል። ድፍን ከተማዋ በእሳት ተያይዛለች። ሰዎች በመንገድ ላይ መጋደላቸውን እንደ ቀጠሉ ነው። አልፎ አልፎ የእንግሊዝን ሌጋሲዮን ከሚጠብቁት የሕንድ ወታደሮች ጋር የተኩስ ልውውጥ ይደረጋል። ለዚህም ምክንያቱ፣ሀብታም አርመኖችና ግሪካውያን ነጋዴዎች፣ዐረቦችም ጭምር ሸሽተው ወደ እንግሊዝ ሌጋሲዮን ይገቡ ስለ ነበረ፣ዘራፊዎች እነሱን እየተከተሉ ይመጡ ስለ ነበረ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፣ከማይጨው መልስ ጃንሆይ በላስታና በኋላም በሰላሌ በኩል አድርገው አዲስ አበባ ገብተው በወጡ አምስተኛው ቀን፣ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ጣሊያኖች አዲስ አበባ ገቡ። በዚያ ቀን ረቡዕ ዕለት ማለዳ ላይ፣በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች በእነ ኃይለ ማርያም ማሞ መሪነት፣ጫጫ በሚባል ሰፍራ ሸዋ ውስጥ አምስት ካሚዮኖች ተቃጠሉ። ከሞቱት በስተቀር አራት ጣሊያኖች ተማረኩ። በዚህ ገድል የተጀመረው የአርበኞች ትግል በሌሎች ስፍራዎችም እንደ ሰደድ እሳት ተቀጥሏሎ ጣሊያኖች በማንኛውም ክፍለ ሀገር ከተማውን እንጅ ባላገሩን እንዳይዙ በእጅጉ ተገደቡ።

ጣሊያኖች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት፣አሌክሳንድሮ ዴል ባዮ ያየውን ሲጽፍ "የእንግሊዝ የአምቡላንስ ኃላፊ ዶክተር ሜሊ ቁስለኞቹን ለማሰባሰብ ከሌጋሲዮኑ ለመውጣት ሞክሮ ነበር። የቀይ መስቀል ባንዲራውን እያውለበለበ ሃያ ሜትር ያህል እንኳን መጓዝ አልቻለም። ወዲያው የጥይት ናዳ አወረዱበት" በማለት የዶክተር ሜሊን አሳዛኝ አሟሟት ጽፎታል። ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲገቡ፣ዮሴፍ እና ብንያም ወርቅነህ፣ወደ ጫካ ገብተው የሽምቅ ውጊያ ለማካሄድ ወሰኑ። ለዚህም ብለው ጉዟቸውን ወደ አምቦ አቀኑ። አምቦ እንደ ደረሱ ፫፻ የሚሆኑ ወታደሮች እና መኮንኖች ከአምቦ ተነስተው ወደ ጎሬ ለመሄድ በመዘጋጀት ላይ ነበሩ።



ወንድማማቾቹ ከእነዚህ ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ጋር አብረው በመሄድ፣የግቤን ወንዝ ተሻግረው፣ቀኑ በመምሸቱ እበረሃ ውስጥ አደሩ። በማግስቱ ማልደው ተነስተው ቢሎ ደርሰው ከደጃዝማች ሀብተማርያም ጋር ተገናኙ። ደጃዝማች ሀብተማርያም የጦር መኮንኖቹ እና ሲቪሎቹ የመጡበትን ምክንያት ጠይቀው ዓላማቸውን ከተገነዘቡ በኋላ ወደ ጎሬ እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው።

ታደሰ ሜጫ ስለ ሆለታ መኮንኖች እና አብረዋቸው ስለሚዘምቱት ሲቪል ሰዎች «ጥቁር አንበሳ» በሚባለው መጽሐፍ እንዲህ ብሏል።

> የጦር መኮንኖች እና ብዙ ታላላቅ ሲቪሎች በየጊዜው ስብሰባ እያደረጉ ካሁን በፊት የነበረው ወታደርና ሌላም ሰው በሚገባ የሠለጠነ፣የጦር ታክቲክ ለምዶ ጠላት በየመሸገበት ስፍራና አዲስ አበባ ድረስም እየሄድን የማጥቃት ጦርነት የምናደርግበት ፕላንና ዘዴ ማጥናት እና ማዘጋጀት ጀመርን። በመጨረሻው ስብሰባ አንድ የምክር ክፍል እንዲቋቋም እና ሥራው ይኸው ጉባዔ በሚቆርጠው (በሚወስነው) ሃሳብ እንዲካሄድ ተወስኖ የጦሩ ስም «ጥቁር አንበሳ» ተብሎ በዚሁ ጉባዔ ተመሠረተ።

የጥቁር አንበሳ ማኅበርን ሕግ አስፈጻሚ እንደራሴዎች ሆነው ሥራውንም እንዲያኪያሂዱ ከተመረጡት ሲቪሎች እና የጦር መኮንኖች መሐከል የዮሴፍ ወርቅነህና የብንያም ወርቅነህ ስም ይገኝበታል። ታደሰ ሜጫ በኃላፊነት የተመደቡትን፣መሪዎቹን ጨምሮ የ፳፰ ሰዎች ስም በቅደም ተከተል ጽፏል። እኔም በዚህ ስም ዝርዝር ከተመደቡት መሐከል፣ከአንድ እስከ ስድስት ያሉትን እንደ ኃላፊነታቸው በቅደም ተከተል ከዚህ በታች ጽፌዋለሁ፡

| | | |
|---|---|---|
| ፩. | ዶ/ር ዓመለ ወርቅ በየነ | ፕሬዚደንት |
| ፪. | ኮለኔል ክፍሌ ነሲቡ | አባል |
| ፫. | ሌ/ኮለኔል ከተማ በሻህ | አባል |
| ፬. | ልጅ ይልማ ደሬሳ | አባል |
| 5. | ልጅ ዮሴፍ ወርቅነህ | አባል |
| ፮. | ልጅ ብንያም ወርቅነህ | አባል |

ከፍ ብሎ ስማቸው ከተዘረዘረው በተጨማሪ ሌተና ኮለኔል በላይ ኃይለ አብ የቡድኑ የበላይ አሠልጣኝ ሲሆኑ፣የቀሩት ሃያ አንዱ የአመራሩ አባል በመሆን ተደለደሉ። የሆለታ መኮንኖች እና ከሌላም ስፍራ የመጡት ሁሉ፣በፍቅር እና በወንድማማችነት ተሳስረው፣አንተ ትብስ፣አንተ ትብስ በመባባል ከጠላት ጋር ለመዋደቅ እና የሽምቅ ውጊያ ለማካሄድ ዕቅድ ነደፉ። ለዚህ ዓላማ ቆሙት፣ ቁጥራቸው ወደ ስድስት መቶ የሚጠጉት ሲቪሎች፣መኮንኖችና ወታደሮች ጣሊያኖች ካሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ይፋለሙ ጀመር። በአንድ መንፈስ እና በጋለ ወኔ ባደረጉት ውጊያ ጠላትን እያርበደበዱ፣ጎሬ ውስጥ ሦስት አይሮፕላኖች አቃጥለው እና ብዙ ጠላቶች ገድለው አኩሪ ታሪክ አስመዘገቡ። ክቡር ልዑል ራስ እምሩ፣ወደ ስድስት መቶ የሚሆኑ ከማይጨው የተመለሱትን ጦር አስከትለው ወደ ጎሬ መጡ።

ራስ እምሩ ወደ ጎሬ የመጡት ወጣቶቹ አይሮፕላኖቹን ከአቃጠሉ በኋላ ነው። እሳቸው ጎሬ እንደ ደረሱ የጥቁር አንበሳ አባላትና ሠራዊት በአክብሮት ተቀበሏቸው። በመቀጠልም እኚህን ታላቅ ሰው በማክበር አመራሩን ለእሳቸው ሰጡ። ይህን በተመለከተ፣ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ኢትዮጵያና የሕይወቴ እርምጃ በሚባለው ፪ኛ መጽሐፍ ገጽ ፷፯ ላይ "ፊታደ ሥላሴ ጎሩይ፣እልፍኝ አስከልካያችን ቀኛዝማች በልሁ ደገፉ፣የአዛዥ ወርቅነህ ልጆች ብንያም እና ዮሴፍ በጋምቤላ በኩል ተላልፈው መልክታችንን ለራስ እምሩ እንዲያደርሱ አደረግን። ፊታደ ሥላሴ ጉሩይ ተመልሶ ከእኛ ዘንድ ደርሶ እንደገና ወደ ጎሬ ተመለሰ" ብለው ጽፈዋል።

ጉልበቱ እየፈረጠመ የመጣው የጥቁር አንበሳ ጦር እስከ ጅማና አምቦ ድረስ በመሄድ ብዙ ውጊያዎችን አድርጎ የጣሊያንን ሠራዊት ቁም ስቅሉን እያሳየ ወደ ጎሬ ይመለስ ነበር። ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የጥቁር አንበሳ ጦር ስለተጠናከረ የጣሊያንን መንጋ እያበረረ ፈጀው። የአይሮፕላኖቹ መቃጠልና የጥቁር አንበሳ አርበኞች ጉልበት መፈርጠም ያሰጋው የጣሊያን መንግሥት ያስ የሌለውን ጦርና መሣሪያ አስይዞ ወደ ጎሬ ላከ። ይህ በሁሉም መልኩ የተደራጀ የጣሊያን ሠራዊት፣ከወንዙ ማዶ ተደብቆ ሲጠብቅ የጣሊያን የማዕረግ ልብስ የለበሱ መልዕክተኞች፣ደጃዝማች መሺድ ከሚባሉ ኢትዮጵያዊ ጋር ነጭ ባንዲራ ይዘው መጡና ከክቡር ራስ እምሩ ጋር ተገናኙ። ጥቂት ደቂቃዎች ከእሳቸው ጋር ተነጋገሩና ተመልሰው ሄዱ። የጠላት መልክተኞቹ የመጡት የጥቁር አንበሳ ሠራዊት እጁን በሰላም እንዲሰጥ አለበለዚያ የጎሬን ሕዝብ በቦምብ የሚያጋዩ መሆናቸውን ለመንገር ነበር።

በጥቁር አንበሳ በኩል፣ዶክተር ዓመለ ወርቅ፣ባላምባራስ ደምሴና ባላምባራስ ቸርነት መልሱን ይዘው ወደ ጣሊያኖቹ ሹም ዘንድ ሄዱ። በመጀመሪያ እጅ ላለ መስጠት በማሰብ፣ጎሬን ለቅቀን እንወጣለን እንጂ እጃችንን አንሰጥም አሉ። በጣሊያን በኩል የነበረው አቋም፣ሕዝቡን በቦምብ እና በጋዝ ጢስ መፍጀት ስለነበረ፣ይህ ጥቆማ ሲደርሳቸው፣እጅ ለመስጠት ወሰኑ። በዚህ ሃሳብ ስምምነት ላይ ተደረሰ እና መሣሪያቸውን አስቀምጠው ጠበቁ። ባንዶቹና ጣሊያኖቹ በገፍ (በብዛት) መጥተው የጥቁር አንበሳን አባላት ከብበው ያዟቸው። ታላላቅ ሰዎች የተባሉትን በአይሮፕላን ወደ ጅማ ሲወስዱ፣የቀሩት በካሚዎን ተጭነው ወደ አዲስ አበባ ተላኩ። የተማሩ ናቸው የተባሉት ተመርጠው የእስረኛ ቁጥር በደረታቸው ላይ እየተለጠፈ ፎቶግራፍ እየተነሱ በእስር ቤት ታጎሩ። ብዙዎቹ እስር ቤት ውስጥ እያሉ የቁም ስቅላቸውን አዩ። የግራዚያኒ ግፍ በዚህ ብቻ አልቆመም። የኔፕልስ ልዕልት ልጅ መውለዷን ምክንያት በማድረግ ጀነራል ግራዚያኒ የደስታ መግለጫ እንዲሆን በማሰብ፣ለድሆች ገንዘብ ለመስጠት ወስኖ እሱ ይኖርበት ወደ ነበረው፣የዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢ እንዲመጡ አዘዘ። ወደ ሦስት ሺ የሚሆኑ ድሆች እንዲሁም በአዲስ አበባ የነበሩ የጣሊያን ሹሞች ወደ ግቢ ገብተዋል። ለድሆቹ ሊሰጥ የተመደበው፣የነፍስ ወከፍ ሁለት ብር ምፅዋት ከመጀመሩ በፊት፣ሁለት የእጅ ቦምቦች ተወርውረው ግራዚያኒና ሌሎች ሹማምንትም ቆሰሉ። አካባቢው በጥይት እሩምታ ቀውጢ ሆነ።



ቦምቦቹን የወረወሩት አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ከስፍራው ሸሽተው ወደ ሱዳን ለመግባት ሞክረው ነበር። ነገር ግን ጠረፉን ለመሻገር ጥቂት መንገድ ሲቀራቸው፣ባልታወቁ ሰዎች ተገደሉ። ሆኖም በእነሱ ምክንያት መላው የአዲስ አበባ ሕዝብ፣ለሦስት ቀናት በጥይት ተቆላ፣ቤቶችና ሰዎች በእሳት ጋዩ። ሕፃናት ወደሚቃጠለው ቤት እየተወረወሩ በእሳት እየተለበለቡ ሞቱ። ወንዶቹ ከካሚዎን ጋር ታስረው፣ጭንቅላታቸው መሬት ላይ ተጎትቶ፣አንጎላቸው ተፈጥፍጦ፣በመንገድ ላይ እንደ ጭቃ ወይም ሬንጅ ተረጩ። የካቲት ፲፪ ቀን በተከሰተው ግርግር ምክንያት በእስር ቤት የነበሩት የተማሩ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ከታሰሩበት ቦታ እየተወሰዱ ተረሸኑ። በዚያን ዕለት አቡነ ጴጥሮስን ጨምሮ ከሁለት መቶ በላይ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች በግፍ ተገደሉ። በዚህ ዓይነት ግፍ ከተገደሉት ወጣች መሐከል፣ዮሴፍ እና ብንያም ወርቅነህ፣ፊታደ ሥላሴ ጉሩይ፣ደበበ እና መሸሻ ገብሩ እንዲሁም በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ የሚባሉትን መጥቀስ ይቻላል።



ዮሴፍ፣ብንያም ወርቅነህና እና ሌሎችም የጥቁር አንበሳ አባላት
ጎሬ ላይ እጅ ከሰጡ በኋላ ወደ እስር ቤት በመወሰድ ላይ እያሉ

በዚህ ፎቶግራፍ ላይ እንደሚታየው፣ጣሊያኖች ወጣት ምሁራንን ሰብስበው በደረታቸው ላይ ስማቸውን በመጻፍ ከመዘገቡ በኋላ አንድ በአንድ እየወሰዱ የረሸኗቸው ወጣቶች ቁጥር ከ፪፻፶ በላይ መሆኑን፡አፄ ኃይለ ሥላሴ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ውስጥ "ታላላቆቹ የጦር ባለሥልጣኖቻችን ተገደሉ። ራስ እምሩም ተማረከ" ብለው ጽፈዋል። የእነዚህ አገር ወዳድ ለጋ ወጣቶች መርዶ እንግሊዝ አገር ደረሰ።

## የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ግርግር ምክንያት ከተገደሉት ምሁራን ወጣቶች መሐከል የጥቂቶቹ ፎተግራፍ እነሆ።




ዮሴፍ ወርቅነህ እሸቴ



ብንያም ወርቅነህ እሸቱ



መሸሻ ገብሩ ደስታ




ደበበ ገብሩ ደስታ





በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ

ፎተግራፉ ያልተገኘው
ፊቃደ ሥላሴ ኅሩይ



የወጣቶቹ መረሸን መርዶ ለወጣቹ አባቶች ሲነገራቸው

## ፲፱፻፴፩

መርዶውን የሰሙት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ክቡር ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣ልዑል ራስ ካሣ፣እና እጌ ኃይለ ሥላሴ ኀዘን ላይ ተቀመጡ:: ይህ ለጆሮ የሚከብድ ድርጊት በዕውነት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት የሚፈልግ ሰው፣አዲስ አበባ የሚገኘውን የየካቲት ፲፪ን ሐውልት መመልከት ይችላል:: በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት ውስጥ አዲስ አበባ ብቻ፣ሕይወቱን ያጣው ሰው ቁጥር ከ፴ ሺሕ (30,000) ይበልጣል::

ከዚህ በላይ የሚታየው ፎተግራፍ፣ሐኪም ወርቅነህና ብላቴን ጌታ ኅሩይ የልጆቻቸው መርዶ ሲነገራቸው ነው:: ምንም እንኳን ጣሊያኖች ሕዝቡን ለማስፈራራት ያለ ርኅራኄ ማሰቃየት እና መግደላቸውን ቢቀጥሉም አርበኞቹ መሐል ከተማ ድረስ ገብተው እየተታኮሱ፡ብዙ ጣሊያኖች ገድለው እና ከተማዋንም ዘርፈዋ መሄዳቸውን አላቋረጡም:: በአርበኞቹ እንቅስቃሴ እጅግ የተደናገጠው ማርሻል ግራዚያኒ ወደ ሮማ ያስተላለፈውን ጽሑፍ፣የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ እንደሚከተለው መዝግቦታል::

> አሁን ያሉት የኢጣሊያ ወታደሮች ፻፲፩ ሺሕ (111,500) ናቸው:: አሁን የሚያስፈልገው የዋናው ከተማ ፀጥታ የተጠበቀና አስተማማኝ እንዲሆን በወታደርና በሌላም ዘዴ መታጠር አለበት:: በባቡሩ ሐዲድ ላይ ፀጥታውን የሚጠብቅ ተንቀሳቃሽና የተጠናከረ ኃይል ያስፈልጋል:: የሸዋ ሕዝብ ታማኝ መስሎ በሽፍታዎች የተጠናከረ ስለሆነ ደብረ ብርሃን እና ፍቼ ከተማ ጠቅላይ ቢሮው ሆኖ ጠንካራ ተዘዋዋሪ አዳኝ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ዋናው ከተማ የሚገቡትን ሽፍቶች እንዲቆጣጠር ይደረጋል:: እንደዚሁም ተመሳሳይ የሆነ የጦር ክፍል በምዕራብም የመገናኛ መስመሮችን እንዲጠብቅና እንዲቆጣጠር ያስፈልጋል::

ለዚህ መልዕክቱ ግራዚያኒ ምንም መልስ ባለማግኘቱ ተስፋ ቆርጦ፣ከዚህ በታች ያለውን ትዕዛዝ አስተላለፈ::

> ለዚህ አገር ሕዝብ ፖለቲካ አያስፈልገውም፣ማባበልም አይገባም:: ሰው ሲበሳጭ ይሸፍታል የሚለውን አላምንበትም:: የመጨረሻ የምነግራችሁ ትንሽ ትልቅ ሳትሉ . . . . . . . . . . .እንድትፈጁት:: ይኸ የእኔ መመሪያ ነውና የአማራን ጎሳ በሙሉ ጨርሱት:: ርኅራኄ ማድረግ አያስፈልግም፣ጨርሷቸው፣ፍጇቸው:: አማሮች ካላለቁ ሰላም እንደማይገኝ አውቃለሁ:: አስቸጋሪ ሕዝቦች ናቸው፣ በአለቁና ከቢሮዬ ቁጭ ባልኩ?

የኢትዮጵያ መጠቃት እንዲህ በቀላሉ ተዳፍኖ ይቀራል ብሎ ያመነ ኢትዮጵያዊ ባለ መኖሩ፣አገር ውስጥ የሚደረገው የሽምቅ ውጊያ በየቀኑ እያየለ የመሄዱ ወሬ ተሰማ:: ይህንንም ምኒስትር ወርቅነህ፣በጋዜጣ ይጽፉ በስብሰባም ላይ ይናገሩ ነበር:: ለኢትዮጵያ የገንዘብ እርዳታ እንዲደረግ ምኒስትር ወርቅነህ በየጊዜው ይጠይቁ ስለነበረ፣ በኀዘን ስሜታቸው የተነካ፣ሀብታም ያልሆኑም እንኳን ሳይቀሩ እርዳታ ይሰጡ ነበር:: እርዳታ ይገኝ የነበረው በአብዛኛው "አቢሲኒያን አሶሲዬሽን" እና "የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ማኅበር" ከሚባሉት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጭምር ነበር:: ከዚህም ጎን ኢትዮጵያን በችግሯ ለመርዳት "ኤምፐረርስ ወይም ኢትዮጵያ ፈንድ" በሚል ስም ለኢትዮጵያውያን እርዳታ የሚሆን ገንዘብ ከብሪታኒያ የሰበሰብ ነበር::

## ፲፱፻፴፪

እርዳታውን በተመለከተ፣የሌጋሲዮኑ ፀሐፊ አቶ አማኑኤል አብርሃም እንዲህ ብለዋል::

> የኢትዮጵያ መንግሥት ፈርሶ፣ንጉሠ ነገሥቱ ተሰድደው ሥራ የሚካሄድበት ገንዘብ ከኢትዮጵያ ማግኘት ባልተቻለበት በዚያ ቀውጢ ዘመን፣ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ድረስ ሎንዶን የነበረው ሌጋሲዮን ሲካሄድ የቆየው እንዲሁም ስደተኞን በየጊዜው ለመርዳት የተቻለው፣ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በልመና ካጠራቀሙት ገንዘብ ላይ ነበር::

ከፍ ብለን እንደ ተመለከትነው አመቺ ጊዜ እየጠበቁ በማጭበርበርና በማወናበድ ገንዘብ ለማግኘት የሚጥሩ ብዙዎች እንደሚመጡ፣ምኒስትር ወርቅነህ በሚገባ ዐውቀዋል:: የፕሮግሬስ ማኅበር (African Progress Society) መሪ፣ብራዘር ብሮድኸርስትን (Brother Broadhurst) የመሳሰሉት፣ የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ችግር ምክንያት በማድረግ እናግዛችኋለን በማለት በማጭበርበር ገንዘብ ለማግኘት ይሯሯጡ የነበሩት ሰዎች ወደፊት ትርፍ ለማካበት ከፍተኛ ጉጉት ያላቸው ናቸው:: እነዚህን የመሰሉትን ሰዎች ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ተደረገ:: ይህን ጉዳይ እንዲከታተል መላኩ በያን የሚባለው ወጣቱ ሐኪም ተመረጠ:: መላኩ በየና ማን ነው?

## መላኩ በያን



Dr. Melaku Bayen graduated from Howard University as the first Ethiopian medical doctor in the United States. He co-founded the Ethiopian Research Council and the Ethiopian World Federation while raising money and recruiting African American experts to help develop Ethiopia.

መላኩ በያን ከእናቱ ከእመቤት ደስታ እና ከአባቱ ከግራዝማች በያን በወሎ ክፍለ ሀገር ሚያዚያ ፲፱ ቀን ፲፰፻፺፪ ዓ.ም. (April 27, 1900) ተወለደ። እናቱ እመቤት ደስታ የልዑል ራስ መኮንን የቅርብ ዘመድ ስለሆኑ፣መላኩ ገና የ፮ ወር ጨቅላ በነበረበት ጊዜ ወላጆቹ ወደ ሐረር ይዘውት ሄዱ። መላኩ ለ፲፪ ዓመት ያህል ሐረር በቆየበት ዘመን ከደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ጋር ይገናኝ ነበር። እሳቸው ራስ ተብለው የመንግሥት እንደራሴ ሆነው ሲሾሙ ንቁ ወጣቶችን እየመለመሉ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር መላክ ጀመሩ። የትምህርት ዕድል ካገኙት ወጣቶች መሐከል መላኩ በያን አንዱ ሆነ። ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፲፫ ዓ.ም. መላኩ በያን፣ወርቁ ጎበና እና በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ የሚባሉት ወጣቶች ወደ ሕንድ አገር ለትምህርት ተላኩ።

ሦስቱም ልጆች ሕንድ ከደረሱ በኋላ በምቤይ ውስጥ በሚገኝ በእንግሊዞች በሚመራ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ጀመሩ። ሕንድ በዚያን ዘመን የእንግሊዝ ቅኝ አገር ስለነበረች፣እንግሊዛውያን መምህራኖቹ በዘር የበላይነት የሚያምኑ ስለነበሩ በትምህርት ጊዜ ሳይቀር የእንግሊዝን የበላይነት እየደጋገሙ ለተማሪዎቻቸው ይነግሯቸው ነበር። ከነጻዪቱ ኢትዮጵያ የመጡትን ወጣቶች፣የእንግሊዞቹ የዘወትር የትምክህት አነጋገር ያበሳጨቸው ጀመር። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆነና ከዕለታት አንድ ቀን አንዱ አስተማሪ ከክፍላቸው ገብቶ ሲያስተምር "ኢትዮጵያን አንድ ቀን መቆጣጠር የእንግሊዝ ፈንታ ይሆናል*" ብሎ በመናገሩ እነ መላኩ በጣም ተበሳጭተው ትምህርት ቤቱን ለቅቀው ወደ አሜሪካ ለመሄድ ተስማሙ። ይህን ሐሳባቸውን ለማሳካት ለበጎ አድራጊያቸው ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ደብዳቤ ጽፈው ላኩላቸው።እንጂ አጋጣሚ ሆኖ፣አዲስ አበባ ሐኪም ቤት ይሠራ የነበረው ዶክተር ቶማስ አ. ላምቢ (Dr. Thomas A. Lambie) ለእረፍት ወደ ቦምቤይ ይሄድ ነበረና፣ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የጻፉላቸውን የይሁንታ የመልስ ደብዳቤ ይዞላቸው መጣ። ዶክተር ላምቢ የእረፍት ጊዜውን ጨርሶ ወደ አሜሪካ ሲሄድ፣መላኩ በያን፣ወርቁ ጎበና እና በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ የሚባሉትን ሦስቱንም አስከትሎ በሚያዚያ ወር ፲፱፻፲፬* ዓ.ም. አሜሪካ ሲደርሱ አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን ለአሜሪካው ፕሬዚደንት ዋረን ጂ. ሃርዲንግ (Warren G. Harding) የጻፉትን የአደራ ደብዳቤ ይዘው ነበር። ፕሬዚደንት ሃርዲንግ ደብዳቤው ሲደርሰው፣ ወጣቶቹን በአክብሮት ከተቀበላቸው በኋላ እሱ በተማረበት እና በኋላም የክብር ዶክቶሬት ዲግሪ ከተቀበቀለበት መስኪንግኸም ኮሌጅ እንዲገቡ ረዳቸው። ይሁን እንጂ፣በኮሌጁ ውስጥ ለመማር ይችሉ ዘንድ የመግቢያ ፈተና ሲሰጣቸው ምንም እንኳን ቀደም ሲል በአገራቸውና በውጭ አገር በትምህርት ቤት የቆዩ ቢሆኑም ኮሌጅ ገብተው ለመማር የሚያስችል ዕውቀት ስላልነበራቸው ፈተናውን ሳያልፉ ቀሩ። ስለዚህ የነበራቸው አማራጭ እዚያው መስኪንግኸም ኮሌጅ (Muskinghum College) ውስጥ በሚገኘው ልዩ የመሰናዶ ትምህርት ቤት መግባት ነበር። በዚህ መሠረት እንግሊዝኛ ቋንቋ እና ሌሎችንም ትምህርቶች ተምረው በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. የ፲፪ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው በማለፋቸው መስኪንግኸም ኮሌጅ ለመማር ተፈቀደላቸው።



እዚህ የነጮች ልጆች ብቻ እሚማሩበት ኮሌጅ ኢትዮጵያውያኑ ወጣቶች ሲገቡ፣የዘር ግጭት እንዳይፈጠር ተሰግቶ ነበር። አባታዊ አመለካከት የነበረው የኮሌጁ ፕሬዚደንት ጄ. ኖክስ ሞንትጎመሪ (J. Knox Montgomery) ባደረገው ጥረት፣ያለ አንዳች ችግር ትምህርታቸውን ለመቀጠል ቻሉ። እዚህ ኮሌጅ ውስጥ እንኳን የትምህርት ቤቱ ጓደኞቻቸው፣የአመጸኛው ኩ፣ ክሉክስ ክላን (Ku Klux Klan) አባላት ሳይቀሩ በጥሩ ሁኔታ ተቀበሏቸው። በተለይ የትምህርት ጓደኞቻቸው ፍቅራቸውን ለመግለጥ ማቲዎስ፣ማርቆስ እና ሉቃስ በሚል የቅጽል ስም ይጠሯቸው ጀመር። ይሁን እንጂ ከእነዚህ የቤተ መንግሥት ቅምጥሎች መሐከል፣ከሁሉቱ ጓደኞቹ በይበልጥ ለአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ዘመድ የሆነው ወርቁ ጎበና፣እንደ ሁለቱ ዘመዶቹ ኮሌጁ ውስጥ ቆይቶ ትምህርቱን ጨርሶ በዲግሪ ለመመረቅ አልበቃም። በኮሌጁ ውስጥ ሽቅርቅር የሆነው ወርቁ ጎበና ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ በፍራንኮ ኢትዮጵያ ኩባንያ ውስጥ የደህንነት ኃላፊ ሆኖ መሥራቱ ይነገራል። በሌላ በኩል ደግሞ፣መላኩ በያን እና በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ትምህርታቸውን በትጋት ሲከታተሉ ቆዩ። በሻህ ውረድ ኮሉምቢያ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ንግድና ጋዜጠኛነት ከተማረ በኋላ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ። መላኩ በያን በ፲፱፻፳ ዓ.ም. የመጀመሪያ ዴግሪውን በኬሚስትሪ ከመስኪንግኸም ኮሌጅ ከተቀበለ በኋላ ኦሃዮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የድህረ ምረቃ ትምህርት ሲከታተል ነበር። እዚህ ዩኒቨርሲቲ እያለ ነበር፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ አሜሪካ መጥተው ስለ ጣና ግድብ የመጡበትን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ጥቁር አሜሪካውያንን ሃርሌም በሚገኝ አደራሽ ጋብዘው ያነጋገሩት። በዚህ ስብሰባ ላይ መላኩ በያንም ተገኝቶ ስለነበረ ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጋር ተዋወቀ። የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ደጋፊ የሆኑት ሐኪም ወርቅነህ፣ጥቁር አሜሪካኖቹ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እንዲሠሩ ሲጋብዟቸው እና ስለ አገር ጉዳይ ሲናገሩ መላኩ በያን በጥሞና በማዳመጡ ልቡ በጣም ተነክቶ ነበር። ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ መላኩ በያንን ለብቻው ጠርተው ለጥቂት ሰዓታት በአነጋገሩበት ወቅት የሰጡትን አባታዊ ምክር፣ዊሊያም ስኮት የሚባል ደራሲ እንዲህ ሲል ጽፎታል።

> በ፲፱፻፳ ዓ.ም. ማርቲን፣ወጣት መላኩ በያንን ሲመክሩት "ለአገርህ ቀምታደርግላት ትልቅ ውለታ፣በሺሕ የሚቆጠሩ አሜሪካ የሚኖሩ ጥቁሮች እና ዌስት ኢንዲያኖችን አግባብተህ ኢትዮጵያን እንዲያለሙ ሽታደርግ ነው።"
>
> In 1927 Martin had advised young Beyan that the greatest service he could render his country was "to influence thousands of black people in the U.S.A. and the West Indies and let them come and develope Ethiopia."

መላኩ በያን ይህን የመሰለ ምክር ከአገኘ በኋላ ከዓለም አቀፍ የጥቁር ወንድማማችነት ንቅናቄ ጋር መቆራኘቱ የስሜት ብቻ ሳይሆን ጥቅም እንዳለው ለመገንዘብ ችሏል።

በዚህን ጊዜ ነበር የነጭ ተማሪዎች መናኸሪያ ከሆነው ኦሃዮ ዩኒቨርሲቲ ወጥቶ ሙሉ በሙሉ የጥቁሮች ትምህርት ቤት ወደ ሆነው ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲ ተዛውሮ ሕክምና ለመማር በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ተመዘገበ። ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲን ለምን መረጥክ ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ እነሆ፦

> ለዘር ወገናዊነት በአለኝ እምነት፣ከወገኖቼ ጋር የበለጠ ለመገናኘት ያስችለኛል ብዬ ስለ አሰብኩ ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ ትምህርት ለመቀጠል ፈለግሁ።

ኦሃዮ ዩኒቨርሲቲ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እና አሁንም ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲ እያለ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ጥቁሮች እኩልነት እና ስለ ዘር መድልኦ አጥብቆ በመከራከር የጥቁሮች ኅብረት እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ጀመር። የእሱ የፓን አፍሪካኒዝም ደጋፊነት የስሜት ብቻ ሳይሆን፣የጥቁሮች ኅብረት አስፈላጊ መሆኑን በጽኑ የሚያምንበት ጉዳይ በመሆኑ ጭምር ነው። ለዚህም ነው ዶሮቲ ሃርሊይ የምትባለዋን ጥቁር ሴት ያገባው። የጥቁር አሜሪካኖች በሆኑት የዜና ማሰራጫ አውታሮች ሁሉ የመላኩ በያን ስም ተደጋግሞ ስለሚነሳ ታዋቂ ሰው ለመሆን በቃ። በዚህም በ፲፱፻፳፱ እና ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. መሐከል በመንግሥት ግብዣ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ፣ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው አፍሮ-አሜሪካኖች በኢትዮጵያ ተጋብዘው እንዲመጡ በማድረጉ የሐኪም ወርቅነህን ምክር ተግባር ላይ አውሎታል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሠሩ ከመጡት መሐከል፣አይሮፕላን ነጂዎቹ ህዩበርት ጁሊየን እና ኮሎኔል ሮቢንሰን፣ዶክተር ጆን ቢ. ዌስትና የትምህርት ባለሙያው ሲሪል ፕራይስ የተባሉ አዋቂዎች ይገኙባቸዋል። መላኩ በያን በሰኔ ወር ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. የዶክቶሬት ዲግሪውን ከተቀበለ በኋላ በማይጨው ጦርነት ዋዜማ ላይ ባለቤቱን ዶሮቲንና "ትንሹ መላኩ በያን" ተብሎ የሚጠራውን የሦስት ዓመት ልጁን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። አዲስ አበባ በአንድ ፎቅ ቤት ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር እየኖረ፣በአሜሪካ ሚስዮን (ሳምቢ) ሆስፒታል የሕክምና ልምምዱን ተያያዘው። እንደ አጋጣሚ ሆኖ በአሠልጣኝነት የተመደበለት ሰው፣መስኪንግሽም ኮሌጅ ሲማር ጓደኛው የነበረ እና ከኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርሲቲ በሕክምና ከተመረቀ በኋላ የፕሬሲቢቴሪያን ሚስዮን ቀጥሮት የመጣ ዶክተር ሮበርት ዊሊያም የሚባል ሰው ነበር።

በሕክምና ሙያው ቅቂት ወራት ልምምድ በማድረግ ላይ እያለ የጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦርነት በመፋፋሙ፣መላኩ በያን እና ዶክተር ሮበርት ዊሊያም ሆክማን በጥቅምት ወር ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ወደ ኦጋዴን ዘመቱ። እነዚህ ሁለት የቀድሞ የትምህርት ቤት ጓደኞችና ሐኪሞች፣የቀይ መስቀል አባል በመሆን በደቡብ ግንባር እስከ ኅዳር ወር ድረስ ቁስለኞችን በማከም ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ዕድለ ቢሱ ሮበርት ሆክማን በጣሊያኖች ጥይት ተመትቶ ሕይወቱ ዐለፈ። ዶክተር ሆክማን ሲሞት፣ዶክተር መላኩ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ጋር የሰሜኑ ጦር ወደተሰለፈበት ደሴ እና ማይጨው ግንባር ዘምቶ ለሁለት ወራት የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ ቆየ። ከጣሊያን አይሮፕላኖች የሚወረወረው የቦምብና የመርዝ በርሜል ናዳ ስለ አየለ ጦርነቱ ሊፈታ ቻለ።



በዚያ የጦር ሜዳ አካባቢ የነበሩት የእንግሊዝ፣የደች እና የግሪክ ቀይ መስቀል አባላት ነፍሳቸውን ለማዳን ድንኳናቸውን ነቅለው ወደኋላ ለማፈግፈግ ተገደዱ። በሚያዚያ ወር ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ መላኩ በያን አብሮ እንደ መጣ ይነገራል። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ እንደደረሱ ከሹማምንቶቻቸው ጋር ከተመካከሩ በኋላ ወደ ዠኔቭ ሄደው ለመንግሥታቱ ማኅበር አቤቱታ እንዲያቀርቡ ተወሰነ። እሳቸው በአገር በማይኖሩበት ጊዜ የመንግሥቱን አመራር፣የኢትዮጵያ ምክር ቤት ፕሬዚደንት የሆኑት ቢትወደድ ወልደ ጻዲቅ እንዲይዙትም አብሮ ተወሰነ። በውሳኔው መሠረት ቢትወደድ ወልደ ጻዲቅ ጎሬ ላይ መሽገው የመንግሥቱን ሥራ እንዲሠሩ ተደርጎ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣናቸውን አስረክበው ወደ አውሮፓ ለመሄድ በባቡር ወደ ጅቡቲ አመሩ። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ውጭ አገር አብረው ከሄዱት መሐከል መላኩ በያንና ቤተሰቡም ነበሩ። እንግሊዝ አገር ጥቂት ወራት ከቆዩ በኋላ፣መላኩ በያን እና ቤተሰቡ ንጉሠ ነገሥቱን ተሰናብተው በመስከረም ወር ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ኒው ዮርክ ገቡ።

መላኩ በያን አሜሪካ እንደ ደረሰ፣ለኢትዮጵያ ድጋፍ ለማግኘት የነበረው ዕቅድ አሜሪካ ውስጥ በተከሰተው የዘር ብጥብጥ ምክንያት ለጊዜው ተገታ። በዚህ ላይ ደግሞ የፓን አፍሪካኒዝም መሪ የነበረው ማርቆስ ጋርቪይ ከአሜሪካን አገር እንዲወጣ መደረጉ ሌላው የራስ ምታት ነበር። ብጥብጡ እና ሌሎችም እንቅፋቶች ጋብ ሲሉ፣ዶክተር መላኩ ለአገሩ ኢትዮጵያ ድጋፍ ለማግኘት ደፋ ቀና ማለት ጀመረ። በኅዳር ወር ለኃይለ ሥላሴ የእርዳታ ገንዘብ ማሰባሰቢያ (Haile Selassie Fund Drive) በሚል ስም የተጀመረውን የእርዳታ ድርጅት ጨምሮ የተባበሩት ለኢትዮጵያ እርዳታ (United Aid for Ethiopia) የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን (Ethiopian World Federation) ከመሰሉት ሌሎች ድርጅቶችም ጋር አብሮ መሥራት ጀመረ። ይሁን እንጂ የተገኘው የገንዘብም ይሁን የመሣሪያ እርዳታ አመርቂ አልነበረም። ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰችውን ጥቃት በማስተዋወቅ በኩል ግን እጅግ በጣም ከፍ ያለ ቅስቀሳ ለማድረግ ተተችሏል። ለዚህም ነው ከጣሊያን ወረራ እና ከጥቁሮች መብት ትግል ጋር በተያያዘ ጉዳይ የመላኩ በያን ተግባር በአሜሪካ የጥቁሮች መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ አትኩሮት የተሰጠው።

መላኩ በያን ለአገሩ ኢትዮጵያ እና ለጥቁሮች መብት ሦስት ዓመት ሙሉ በአደረገው የፖለቲካ ትግል ጫና፣ሰውነቱ ደክሞ እና አእምሮው ተቃውሶ ለከፍተኛ ሕመም ተዳረገ። በነሐሴ ወር ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. የተከሰተበትን በሽታ ታክሞ ትንሽ ሻል ስላለው ትግሉን እንደገና በጀመረ ጥቂት ወራት ውስጥ በሽታው ስላገረሸበት ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. በመጋቢት ወር ኒው ዮርክ በሚገኘው የሮክላንድ መንግሥት የአእምሮ ሆስፒታል ገብቶ መታከም ጀመረ። ሐኪሞቹ ብዙ ጥንቃቄ ቢያደርጉለትም በሳምባ በሽታ (lobar pneumonia) ከመለከፍ ሊከላከሉለት አልቻሉም። ይህ ታላቅ የኢትዮጵያ ልጅ፣ጣሊያን ውድ አገሩን በወረረችበት ልክ በአራተኛው ዓመት፣ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. ዐረፈ።

የአዛዥ ሐኪም ወርቀነህን እና የከንቲባ ገብሩ ደስታን ፈለግ ተከትሎ፣ለፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ በታላቅ ወኔ ሲታገል የነበረው መላኩ በያን በለጋ ዕድሜው መቀጨቱ በእጅጉ ያስቆጫል። ለ፲፫ ዓመታት ኦሃዮ እና ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲዎች ተምሮ፣በጋብቻ እና በመብት ትግል ከአቻዎቹ ጋር አሜሪካን አገር አብሮ የኖረ ወደር የሌለው ሰው ነበር። ለ"አገሩ ኢትዮጵያ እና የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ትልቅ አጋር እና መሪ ሊሆን የሚችለውን መላኩ በያንን አጡ" በማለት በአሜሪካ ጋዜጣዎች ተጽፎለታል። በኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ የተጻፈው ደግሞ "በጣም ጠቃሚ ከሆኑት እና ከወገናቹ ወጣት መሪዎች መሐከል ተስፋ የተጣለበት፣ለዓለም አቀፍ የዘር ትብብር ተቋም ደፋ ቀና ሲል የነበረው ሐኪም (መላኩ በያን) መሞቱ ለድርጅቱ ትልቅ ጎዳት ነው" ይላል።

> "One of the most useful and promising young leaders of the race. The cause international racial solidarity to which Beyan was so devoted had suffered a great loss with the doctor's death."
>
> Voice of Ethiopia

ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ መላኩ በያን የሚከተለውን ጽፈዋል።

> ዶክተር መላኩ በያን ከሕፃንነት ጀምሮ ያሳደግነው የእልፍኝ አሽከራችን ነበር። ትጋቱንና አስተዋይነቱን ተመልክተን በ፲፱፻፲፫ ዓ.ም. ለትምህርት ወደ አሜሪካ ስለ ላክነው በትምህርቱ ከመጠንከሩ የተነሳ የሕክምና ዶክተር እስከ መሆን በቃ። ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ አገሩን ኢትዮጵያንና እኛን ንጉሠ ነገሥቱን ለማገልገል መጥቶ ከእኛ ሳይለይ እስከ ማይጨው ዘመተ። በጦርነት የቆሰሉትንም ወታደሮች በትጋት ለመርዳት ፍላጎቱ ስለሆነ በቀዶ ጥገና ሕክምና በየቀኑ የፈጸመውን ብዙ አገልግሎት ሰምተናል።
>
> ዶክተር መላኩ በያን ከጦርነቱ በኋላ ተከትሎን ወደ እንግሊዝ አገር መጣ። ከዚያም ወደ አሜሪካ ሔዶ ኢትዮጵያን ለመርዳት በሚችልበት ሁናቴ ሁሉ ያገለግል ጀመር። የአፍሪካ ተወላጆች የሆኑት አሜሪካውያን እንዲሰበሰቡና ለኢትዮጵያ የድጋፍ ድምፅ እንዲሰጡ በማድረግ ብዙ ሥራ ሠርቷል።
>
> አውሮፓ ላይ ወደ ተነሣው ጦርነት ኢጣሊያ ልትገባ ነው የሚለውን ወሬ እየሰማንና የአገራችንን ነፃነት በተስፋ እየተጠባበቅን ተቀምጠን ሳለን ታማኝ አገልጋያችን ዶክተር መልአኩ በያን በግንቦት ወር ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. አሜሪካ ላይ የመሞቱ መርዶ ተነግሮን በባዝ መኖሪያችን ኀዘን አደረግን።

ለዚህ ውድ የኢትዮጵያ ልጅ፣የካቲት ፲፪ ተብሎ በሚታወቀው ሆስፒታል ውስጥ "መላኩ በያን ወርድ" በማለት በስሙ የሚጠራ የመታከሚያ ክፍል መንግሥት አቋቁሞለታል።



ይገባዋል እላለሁ! ለሌሎቹስ? የሚል ጥያቄ ግን አለኝ። ስለ መላኩ በያን ሲነገር፣አንድ በግልጽ መታወቅ ያለበት ጉዳይ አለ። ይህም ብዙ ጊዜ በብዙሃን መገናኛ እና በሰውም ዘንድ መላኩ በያን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሐኪም ነው የመባሉ ጉዳይ ነው። በእውነት ለመናገር ካስፈለገ፣መላኩ በያን የሕክምና ዲግሪ የተቀበለው በ፲፱፻፳፬ ዓ.ም. ሲሆን፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በሕክምና ሥራ ከቆዩ ፶፮ ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው። ከዚህም በላይ ደግሞ ሐኪም ወርቅነህ፣አፄ ምኒልክን ጨምሮ በርካታ ሰዎችን በማከም፣ሆስፒታል በማስተዳደርና በራሳቸው አነሳሽነት ሐኪም ቤት በመክፈት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሐኪም ናቸው። ክፍ ብሎ ከተጻፈው የዶክተር መላኩ በያን ታሪክ እንደተገለጸው፣መላኩ በያን ትምህርቱን እንደጨረሰ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ገና ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ የማይጨው ጦርነት ተቀሰቀሰ። በዚህ ምክንያት ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ በጦርነት የቆሰሉትን ሰዎች ሲያክም ነበር። ከዚያም ጦርነቱ ሲፈታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ሎንዶን ሄዶ ስለነበረ፣ወደ አሜሪካ ተልኮ ጥቁር አሜሪካኖች ኢትዮጵያን እንዲረዱ ቅስቀሳ ሲያደርግ ሕይወቱ ዐለፈ። ስለዚህ "ታሪክን ለባለ ታሪኩ" ይባላል እና በኢትዮጵያ የሐኪሞች ታሪክ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን የቀደመ የሕክምና ባለሙያ ስለልነበረ፣መላኩ በያን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሐኪም መባሉ ልክ አይደለም እና ይህን የመሰለ ስህተት እንዳይደገም እዚህ ላይ ማሳሰቡ ተገቢ መሆኑን አምንበታለሁ። ይህን ያህል ካልኩ በኋላ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ሎንዶን ውስጥ ተቀምጠው ስለ አገራቸው ጉዳይ የሚያከናውኑትን ተግባራት መግለጤን ልቀጥል።

የጦር ጓድ አስተባባሪ ሆነው ለመሥራት ዶክተር ድራይበርግ (Dr. Driburg) እና ሚስተር ፌርፋክስ (Mr. Fairfax) ወደ ሌጋሲዮኑ መጡ። ከእነሱ በኋላ ደግሞ ሚስ ፓንክረስት እና ሲኞር ኮሪዮ የሚባሉ ጋዜጠኞችም መጡ። ሚስ ሲልቪያ ፓንክረስት፣፣በእንግሊዝ አገር ለሴቶች መብት የሚታገለው የገናናው ድርጅት አባል የሆኑት የሚስስ ኤሜሊን ፓንክረስት (Emmeline Pankhurst) ልጅ ናቸው። ሚስ ኤሜሊን እና ሁለት ጓደኞቻቸው በዚህ ድርጅት ውስጥ ትልቅ ኃላፊነት ነበረባቸው። ድርጅታቸው በእንግሊዝኛ The suffregates በሚባል ስም በዓለም ይታወቃል። ሚስ ሲልቪያ የእናቷን ፈለግ ተከታይ በመሆኗ ፋሽስቶችና ናዚስቶች በአውሮፓ የሚፈጽሙትን ወረራ እየተቃወመች በጋዜጣ ትጽፍ ነበር። ሲኞር ኮሪዮ በበኩሉ የጣሊያን ሶሻሊስት ንቅናቄ አባል ነበር። እነዚህ ሁለቱ ሰዎች በነበራቸው የጋራ የፖለቲካ አቋም የተነሳ አብረው አዲሱ ዘመን (The New Times) የሚል ጋዜጣ አቋቋመዋል። ጋዜጣው በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ትኩሳት ላይ የሚያተኩር ነበርና እየገነነ የመጣውን ፋሽስቶች እና ናዚዝስቶች ሚፈጽሙትን እኩይ ተግባራት በጋዜጣቸው አምዶች በመጻፍ ያጋልጡ ነበር። ፋሽስት ኢጣሊያ ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በወልወል በኩል ጠብ በመጫር አገራችንን ለመውረር መዘጋጀቷን የተረዱት የእነዚህ ጋዜጠኞች ትኩረት ወደ ኢትዮጵያ ጉዳይ ስለዞረ ሁኔታዎችን በቅርብ እየተከታተሉ በጋዜጣቸው አማሃይነት ማጋለጡን ተያያዙት።

ጋዜጣውን በርካታ ሰዎች እንዲያነቡት ጥቂት ቅጂዎች ለሌጋሲዮኑ በነጻ መላክ ጀመሩ። በዚህ ሳቢያ ከምኒስትር ሐኪም ወርቅነህ ጋር ለመተዋወቅ በቁ። የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒስትር ሐኪም ወርቅነህም አገራቸው ላይ የደረሰውን የግፍ ወረራ በየጊዜው ጽፈው ለብዙሃን መገናኛ ጋዜጠኞች ይሰጡ እንደነበረ ቀደም ሲል አንብበናል። ከሲልቪያ ፓንክረስትና ከሲዎ ኮሬ ጋር ሲገናኙ፣ሐኪም ወርቅነህ ለእነሱም ጋዜጣ አንዳንድ ጽሑፎች መስጠት ጀመሩ። የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር በቂ መሣሪያ ቢኖረውም የኢትዮጵያ ሕዝብ "ወኔውን ሰንቆ እና እምቢ ለሀገሬ ብሎ በቆራጥነት በአርበኝነት ተሰማርቶ እያሌ ድሎች መቀዳጀቱ በዚሁ ጋዜጣ እየታተመ ይወጣ ጀመር። በመቀጠልም ጋዜጣው በአብዛኛው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ነበር።

ኢጣሊያኖች ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲገቡ እነሲልቪያ ፓንክረስት ጋዜጣውን "አዲስ ዘመንና የኢትዮጵያ ዜና" (New Times and Ethiopian News) ብለው ሰየሙት። ጽሑፉ የሚያተኩረው በአብዛኛው ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል እንድትችል መሣሪያ የመግዛት እና ወደ አገሯ ለማስገባት የሚቻልበትን መንገድ ለማፈላለጊያ እና የፋሽስትን ወረራ በመቃወም ነበር። በአደባባይ እና በራዲዮ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይናገሩ የነበሩት ሐኪም ወርቅነህ፣ቅሬታቸውን በመጽሔት እና በበራሪ ወረቀት በመጻፍ ጭምር በብዙ አገሮች እንዲሰራጭ ያደርጉ ነበር። "አዲስ ዘመንና የኢትዮጵያ ዜና" በሚባለው የሲልቪያ ፓንክረስት ጋዜጣም ላይ ሐኪም ወርቅነህ የራሳቸው አምድ ነበራቸው። "አዲስ ዘመንና የኢትዮጵያ ዜና" በሚባለው ጋዜጣ ውስጥ፣ሚስ ሲልቪያ ፓንክረስት ሽንጧን ገትራ ያደረገችው ፋሽዝምን የመቃወም ወኔዋ በእጅጉ የሚያስመሰግናት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም ታላቅ ባለውለታ አድርጓታል። በጋዜጣ ከመጻፏም በተጨማሪ ወዳጆቿን በማሰባሰብ ስለ ኢትዮጵያ መበደል አደባባይ እየወጡ ስሞታቸውን እንዲያሰሙ አስተባብራላች።

ፋሽስቶች በቦምብና በናፓል የመርዝ ጭስ በመታገዝ የኢትዮጵያን ሠራዊት ድል አድርገው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የተማሩት ኢትዮጵያውያን እየፈለጉ ያስሩ ሲፈልጋቸውም ይገድሉ ጀመር። የሐኪም ወርቅነህ ልጆች ዮሴፍ እና ብንያም ሲገደሉ ቴዎድሮስ ወርቅነህ ከእንግሊዛዊት እናት የተወለደ በመሆኑ ከመገደል ቢድንም ታስሮ ወደ ጣሊያን አገር ተወስዶ ነበር። ሐኪም ወርቅነህ የልጃቸውን መታሰርና በሕይወት መኖሩን ሲሰሙ፣በጥር ወር ፲፱፻፴ ዓ.ም. ላይ፣ወደ የእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ቢሮ ሄደው፣ከጣሊያን አገር ለማስፈታት የሚቻልበትን መንገድ ሚስተር ቶምሶንን (Mr. Thompson) እንዲያፈላልግላቸው ጠየቁት። ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ቴዎድሮስን ለማስፈታት አለመቻሉን ሚስተር ቶምሶን ነገራቸው። እሳቸው በልጃቸው አለመፈታት ቢያዝኑም የፖለቲካ ትግላቸውን ግን ሊገታ አልቻለም። ለዚህ ነው መጋቢት ፩ ቀን የገቢ ማስገኛ ባዛር ሎንደን ውስጥ ያካሄዱት። በዚያን ዕለት በተደረገው የቁሳቁስ ሽያጭ ጠቀም ያለ ገንዘብ ለማግኘት ተቻለ።



መጋቢት ፳፩ ቀን ምዕራብ ኢትዮጵያ ገብተው የነበሩት ዶክተር ሎሬንዞ ታዕዛዝ መጥተው፣የኢትዮጵያ አርበኞች ከትላልቆቹ ከተማዎች በስተቀር አገሪቷን በሙሉ እየተቆጣጠሩ መሆናቸውን ነገሯቸው። ዶክቶር ሎሬንዞ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያደረጉት ይህ ጉዞ፣ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው።




ሚስ ሲልቪያ ፓንክረስታና የመብት ታጋይ የሆኑት እንግሊዛውያን ሴቶች፣ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረሯን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጉ ነበር። በስተጀርባ መሐል ላይ የሚታት የገብርኤል ቴዎድሮስ እናት ሚስስ ፍሎሬንስ ቴዎድሮስ ናቸው።

ከሁለት ቀን በኋላ ሐኪም ወርቀነህና ከሚስ ፓንክረስት እና ከልጇ አባት ሚስተር ኮሪ ጋር ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ በሰፊው ሲነጋገሩ ዋሉ። የቀድሞው የብሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር ስታንሌየ ቦልድዊን (Stanley Baldwin) እና የውጭ ጉዳይ ምኒስትሩ ሳሙኤል ሆር ኢትዮጵያን ለኢጣሊያ አሳልፎ ለመስጠት የወጠኑትን ክፍጸሜ ለማድረስና ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ተባብሮ የኤውሮፓን ሰላም እንዳያናውጥ ለማባበል አዲሱ ጠቅላይ ምኒስትር ኔቪል ቻምበርሌን አስቦ ስለነበረ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ግዛት መሆኗን አወቁላት። የኢጣሊያ ንጉሥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆኑን ስለተቀበሉ ከሙሶሊኒ ጋር ለመስማማት ቻሉ።



ዮሴፍ፣ብንያም ወርቅነህና እና ሌሎችም የጥቁር አንበሳ አባላት
ጎሬ ላይ እጅ ከሰጡ በኋላ ወደ እስር ቤት በመወሰድ ላይ እያሉ

## የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ግርግር ምክንያት ከተገደሉት ምሁራን ወጣቶች መሐከል የጥቂቶቹ ፎተግራፍ እነሆ::



ዮሴፍ ወርቅነህ እሸቴ



ብንያም ወርቅነህ እሸቴ



መሸሻ ገብሩ ደስታ




ደበበ ገብሩ ደስታ





በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ

ፎተግራፉ ያልተገኘው
ፊቃደ ሥላሴ ኅሩይ



የወጣቶቹ መረሸን መርዶ ለወጣቹ አባቶች ሲነገራቸው

የብሪታኒያ መንግሥት ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ግዛት መሆኗን አምነው በይፋ የደገፉት ኅዳር ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ነው። ከዚህ የተነሳም አዛዥ ወርቅነህ በብሪታኒያ ቤተ መንግሥት ዘንድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ መልክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒስትር መሆናቸው መቅረቱን (መሰረዙን) ፎሬይን ኦፊስ (Foreign Office) በኦፊሲየል ደብዳቤ ለምኒስትር ሐከሚ ወርቅነህ ማስታወቁን፣አቶ አማኑኤል አብርሃም የሕይወቴ ትዝታ በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ሲሉ መዝግበውታል።

> የቀድሞው የብሪታኒያ ጠቅላይ ምኒስትር ስትንሌይ ቦልድዊን እና የውጭ ጉዳይ ምኒስትሩ ሳሙኤል ሆር፣ኢትዮጵያን ለኢጣሊያ አሳልፎ ለመስጠት የወጠኑትን ከፈጻሜ ለማድረስና ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ተባብሮ የኤውሮፓን ሰላም እንዳያናውጥ ለማባበል፣አዲሱ ጠቅላይ ምኒስትር ኔቪል ቻምበርሌን ቆርጦ ስለነበረ፣ኢትዮጵያ የጣሊያን ግዛት መሆንዋን፣የኢጣሊያ ንጉሥም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆኑን በመቀበልና በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ሚያዚያ ፲፱፻፴ ዓ.ም. ከሙሶሊኒ ጋርተስማማ።
>
> ኅዳር ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ግዛት መሆንዋን የብሪታኒያ መንግሥት አምኖ መቀበሉንም በይፋ ገለጸ። ከዚህ የተነሳም፣አዛዥ ወርቅነህ በብሪታኒያ ቤተ መንግሥት ዘንድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ መልክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒስትር መሆናቸው መቅረቱን ፎሬይን ኦፊስ በኦፊሲየል ደብዳቤ ለምኒስትሩ አስታወቀ።

ይህ እንደሚሆን ከ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ጀምሮ ሐኪም ወርቅነህ ይጠረጥሩ ስለነበረ፣ ብዙ ጊዜ ለእንግሊዝ መንግሥት ሮሮ ያሰሙ እንደ ነበረ ቀድም ሲል ተጽፋል። ያም ሆኖ አንድ ቀን እንግሊዞች ሃሳባቸውን ለውጠው የኢትዮጵያን የፍትሕ ጥያቄ ይደግፋሉ ብለው ማሰባቸው አልቀረም ነበር። ያም ሆነ ይህ የእንግሊዝ ድርጊት፣የመንግሥታት ማኅበር የቆመለትን የጋራ ጸጥታ መሠረተ ሃሳብ ሰርዞ፣ጥቃት የደረሰባትን ኢትዮጵያ በመደገፍ ፈንታ፣ላጥቂዋ ኢጣሊያ ማገዙ ጃንሆይን እና አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን በእጅጉ አሳዘናቸው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ኢትዮጵያና የሕይወቴ እርምጃ በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ስለእንግሊዞች ውሳኔ ሲጽፉ "ከልቤ ከማደንቀውና ጥልቅ የሆነ ወሮታ በልቤ ከማሳድርለት መንግሥት አሳብ ጋር ባለመስማማቴ እጅግ አዝናለሁ። በንዘን ጊዜ የቸርነትና የእንግዳ ተቀባይነት አድራጎቱን የሰጠኝ እርሱ ነው" ብለዋል።

ሐኪም ወርቅነህ እንግሊዝ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ መልክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ምኒስትር መሆናቸው መቅረቱን እንዳወቁ፣እንግሊዝ አገር ተቀምጠው ልጆቻቸውን እያስተማሩ ለመኖር በእጅጉ ከባድ እንደሚሆን ተገነዘቡ። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው፣ከ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ድረስ ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት መከበርና ኀልውናዋ እንዳይጠፋ እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ያደረጉት አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ሌጋሲዮኑን መልቀቅ ነበረባቸው። ወዲያውኑ በኬንዚንግተን የከተማ ክፍል ቤት ተከራይተው የሌጋሲዮኑን ቤት ለቅቀው ወጡ።



አራት ልጆች ይዘው ያለ ሥራ መቀመጥ ከኑሮ ውድነት ጋር ተዳምሮ ብሪታኒያ ውስጥ መኖር አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ስለዚህ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ሕንድ አገር ለመሄድ የጃንሆይ ፈቃድ ጠየቁ። ምኒስትር ወርቅነህ የጠየቁትን ፈቃድ ካገኙ በኋላ፣እንደ ልጅ እያስተማሩና እየመከሩ፣እንደ ሠራተኛ እየተቆጣጠሩ እና እየመሩ አብረዋቸው የኖሩትን አቶ አማኑኤልን በዚህ በመከራ ጊዜ ብቻቸውን እንግሊዝ አገር ትተዋቸው ለመሄድ አልፈለጉም። ስለዚህ "አንተም ከልጆቼ አንዱ ነህና ከእኛ ጋር አብረን ወደ ሕንድ አገር እንሂድ" ብለው ሐኪም ወርቅነህ ጠየቋቸው። አቶ አማኑኤል በበኩላቸው እንግሊዝ አገር ቆይተው ትምህርታቸውን ለመቀጠል ስለፈለጉ ከእሳቸው ጋር ወደ ሕንድ አገር ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ።

ከሐኪም ወርቅነህ ጎን በመሆንና አብረዋቸው በመሥራት አቶ አማኑኤል በቅን ልቡና ለሰጧቸው መልካም አገልግሎት አመስግነው፣ወደ ሕንድ አገር ከመሄዳቸው በፊት የመኝታ ቤት ዕቃ፣መጻፊያ ጠረጴዛ እና ወንበሮችን ጭምር ለአቶ አማኑኤል አብርሃም ሰጧቸው። ከላይ እንዳነበብነው፣ሥራ እጥ የነበሩትን አቶ አማኑኤል አብርሃምን ወደ አሰበ ተፈሪ አምጥተው ሥራ ያስተማሩ፣የትምህርት ቤት ዲሬክተር አድርገው የሾሟቸው አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ናቸው። ከሌሎች ሠራተኞቻቸው መሐል መርጠው ወደ እንግሊዝ አገር የወሰዷቸውም እሳቸው ናቸው። ለዚህ ውለታቸው አቶ አማኑኤል አብርሃም «የሕይወቴ ትዝታ» በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ የሚከተለውን ጽፈዋል።

> አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ትውልዱ ከዚህ አውራጃ ነው ከዚያ ነው ሳይሉ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ይሰጡት የነበረው ድጋፍ እና እርዳታ፣ያሳዩ የነበረው የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት አርዓያም፣ እስከ ዘመኔ መጨረሻ በልቤ ውስጥ ይኖራል።

በአንጻሩ ደግሞ ሐኪም ወርቅነህ ያደረጉላቸውን ውለታ ረስተው በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ብለዋል።

> አዛዥ ወርቅነህ ወደ ሕንድ ለመሄድ በቆረጡ ጊዜ፣ተከትያቸው እንድሄድ ጠይቀውኝ ነበር። እኔም እሳቸውን ከማስቸገር በቀር በሕንድ የምሠራው ጠቃሚ ነገር አለመኖሩ ስለተሰማኝ፣ወደዚያ መሄድ አለ መፍቀዴን ገለጽሁላቸው። በብሪታኒያ ትምህርት ቤት ብገባ ዕውቀት ለመጨመርና ሥራ ለማግኘትም ይጠቅመኛል በማለት፣ለሁለት ዓመት ትምህርት የሚሆነኝ <u>መቶ ሃያ ፓውንድ እንዲሰጡኝ ብለምን ፈቃዳቸው ሳይሆን ቀረ።</u>

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህን አወድሰው የጻፉበት ብዕር ታጥፎ "መቶ ሃያ ፓውንድ እንዲሰጡኝ ብለምን ፈቃዳቸው ሳይሆን ቀረ" ብሎ መውቀስን ምን አመጣው? አባቶች "ወርቅ ላበደረ አፈር" እንደሚሉት መሆኑ ነውን? ለነገሩማ ስለ ሐኪም ወርቅነህ ደግነት በዚያው "የሕይወቴ ትዝታ" በሚለው መጽሐፍ አቶ አማኑኤል ቀጥሎ ያለውን ጽፈው አልነበረምን?

መርዶውን የሰሙት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ክቡር ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣ልዑል ራስ ካሣ፣እና አፄ ኃይለ ሥላሴ ኀዘን ላይ ተቀመጡ:: ይህ ለጆሮ የሚከብድ ድርጊት በዕውነት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት የሚፈልግ ሰው፣አዲስ አበባ የሚገኘውን የየካቲት ፲፪ን ሐውልት መመልከት ይችላል:: በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት ውስጥ አዲስ አበባ ብቻ፣ሕይወቱን ያጣው ሰው ቁጥር ከ፴ ሺሕ (30,000) ይበልጣል::

ከዚህ በላይ የሚታየው ፎተግራፍ፣ሐኪም ወርቅነህና ብላቴን ጌታ ኅሩይ የልጆቻቸው መርዶ ሲነገራቸው ነው:: ምንም እንኳን ጣሊያኖች ሕዝቡን ለማስፈራራት ያለ ርኅራኄ ማስቃየት እና መግደላቸውን ቢቀጥሉም አርበኞቹ መሐል ከተማ ድረስ ገብተው እየተታኮሱ፡ብዙ ጣሊያኖች ገድለው እና ከተማዋንም ዘርፈዋ መሄዳቸውን አላቋረጡም:: በአርበኞቹ እንቅስቃሴ እጅግ የተደናገጠው ማርሻል ግራዚያኒ ወደ ሮማ ያስተላለፈውን ጽሑፍ፣የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ እንደሚከተለው መዝግቦታል::

> አሁን ያሉት የኢጣሊያ ወታደሮች ፻፲፩ ሺሕ (111,500) ናቸው:: አሁን የሚያስፈልገው የዋናው ከተማ ፀጥታ የተጠበቀና አስተማማኝ እንዲሆን በወታደርና በሌላም ዘዴ መታጠር አለበት:: በባቡሩ ሐዲድ ላይ ፀጥታውን የሚጠብቅ ተንቀሳቃሽና የተጠናከረ ኃይል ያስፈልጋል:: የሸዋ ሕዝብ ታማኝ መስሎ በሽፍታዎች የተጠናከረ ስለሆነ ደብረ ብርሃን እና ፍቼ ከተማ ጠቅላይ ቢሮው ሆኖ ጠንካራ ተዘዋዋሪ አዳኝ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ዋናው ከተማ የሚገቡትን ሽፍቶች እንዲቆጣጠር ይደረጋል:: እንደዚሁም ተመሳሳይ የሆነ የጦር ክፍል በምዕራብም የመገናኛ መስመሮችን እንዲጠብቅና እንዲቆጣጠር ያስፈልጋል::

ለዚህ መልዕክቱ ግራዚያኒ ምንም መልስ ባለማግኘቱ ተስፋ ቆርጦ፣ከዚህ በታች ያለውን ትዕዛዝ አስተላለፈ::

> ለዚህ አገር ሕዝብ ፖለቲካ አያስፈልገውም፣ማባበልም አይገባም:: ሰው ሲበሳጭ ይሸፍታል የሚለውን አላምንበትም:: የመጨረሻ የምነግራችሁ ትንሽ ትልቅ ሳትሉ . . . . . . . . . .እንድትፈጁት:: ይኸ የእኔ መመሪያ ነውና የአማራን ጎሳ በሙሉ ጨርሱት:: ርኅራኄ ማድረግ አያስፈልግም፣ጨርሷቸው፣ፍጇቸው:: አማሮች ካላለቁ ሰላም እንደማይገኝ አውቃለሁ:: አስቸጋሪ ሕዝቦች ናቸው፣ በአለቁና ከቢሮዬ ቁጭ ባልኩ?

የኢትዮጵያ መጠቃት እንዲህ በቀላሉ ተዳፍኖ ይቀራል ብሎ ያመነ ኢትዮጵያዊ ባለ መኖሩ፣አገር ውስጥ የሚደረገው የሽምቅ ውጊያ በየቀኑ እያየለ የመሄዱ ወሬ ተሰማ:: ይህንንም ምኒስትር ወርቅነህ፣በጋዜጣ ይጽፉ በስብሰባም ላይ ይናገሩ ነበር:: ለኢትዮጵያ የገንዘብ እርዳታ እንዲደረግ ምኒስትር ወርቅነህ በየጊዜው ይጠይቁ ስለነበረ በኀዘን ስሜታቸው የተነካ፣ሀብታም ያልሆኑም እንኳን ሳይቀሩ እርዳታ ይሰጡ ነበር:: እርዳታ ይገኝ የነበረው በአብዛኛው "አቢሲኒያን አሶሲዬሽን" እና "የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ማኅበር" ከሚባሉት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጭምር ነበር:: ከዚህም ጎን ኢትዮጵያን በችግሯ ለመርዳት "ኤምፐረርስ ወይም ኢትዮጵያ ፈንድ" በሚል ስም ለኢትዮጵያውያን እርዳታ የሚሆን ገንዘብ ከብሪታኒያ የሰበሰብ ነበር::




እርዳታውን በተመለከተ፣የሌጋሲዮኑ ፀሐፊ አቶ አማኑኤል አብርሃም እንዲህ ብለዋል::

> የኢትዮጵያ መንግሥት ፈርሶ፣ንጉሠ ነገሥቱ ተሰድደው ሥራ የሚካሄድበት ገንዘብ ከኢትዮጵያ ማግኘት ባልተቻለበት በዚያ ቀውጢ ዘመን፣ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ድረስ ሎንዶን የነበረው ሌጋሲዮን ሲካሄድ የቆየው እንዲሁም ስደተኞን በየጊዜው ለመርዳት የተቻለው፣ምኒስትር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በልመና ካጠራቀሙት ገንዘብ ላይ ነበር::

ከፍ ብለን እንደ ተመለከትነው አመቺ ጊዜ እየጠበቁ በማጭበርበርና በማወናበድ ገንዘብ ለማግኘት የሚጥሩ ብዙዎች እንደሚመጡ፣ምኒስትር ወርቅነህ በሚገባ ዐውቀዋል:: የፐሮግሬስ ማኅበር (African Progress Society) መሪ፣ብራዘር ብሮድኸርስትን (Brother Broadhurst) የመሳሰሉት፣ የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ችግር ምክንያት በማድረግ እናግዛችኋለን በማለት በማጭበርበር ገንዘብ ለማግኘት ይሯሯጡ የነበሩት ሰዎች ወደፊት ትርፍ ለማካበት ከፍተኛ ጉጉት ያላቸው ናቸው:: እነዚህን የመሰሉትን ሰዎች ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ተደረገ:: ይህን ጉዳይ እንዲከታተል መላኩ በያን የሚባለው ወጣቱ ሐኪም ተመረጠ:: መላኩ በየና ማን ነው?

## መላኩ በያን



Dr. Melaku Bayen graduated from Howard University as the first Ethiopian medical doctor in the United States. He co-founded the Ethiopian Research Council and the Ethiopian World Federation while raising money and recruiting African American experts to help develop Ethiopia.

> አሰበ ተፈሪ ከጽሕፈት ቤት ሥራ ጋር በመጠኑ የተላመድሁ ብሆንም፣ ሎንዶን ላይ ያጋጠመኝ የሥራ ዓይነት እንግዳ ሆኖብኝ ለጥቂት ጊዜ ድንግር ሳይለኝ አልቀረም። ዳሩ ግን፣የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ምክር ስላልተለየኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራውም፣ከሰውም ጋር ተለማመድሁ እና በንቃትና በትጋት ተግባሬን ቀጠልሁ።

ከእዚህ ሐተታ በመነሳት አንባብያን የራሳቸውን ፍርድ ይስጡ እላለሁ። ያም ሆነ ይህ አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ሌጋሲዮኑን ለቅቀው ከሄዱ በኋላ፣ሌጋሲዮኑ እንዲዘጋ የእንግሊዝ መንግሥት ቢያዝም፣አፄ ኃይለ ሥላሴ ሎንዶን ውስጥ አንድ ጽሕፈት ቤት በህቡዕ ለማቋቋም ወሰኑ። ከዚያም አቶ አማኑኤልን ጠርተው፣ጽሕፈት ቤቱ ውስጥ በጸሐፊነት እንዲረዷቸው ጠየቋቸው። ምንም እንኳን አፄ ኃይለ ሥላሴ ሊከፍሏቸው ያሰቡት ደሞዝ ከወር ወጪያቸው ያለፈ ባይሆንም፣ንጉሠ ነገሥታቸውን እና አገራቸውን ለማገልገል ስለ ፈለጉ ሥራውን በፈቃደኛነት መቀበላቸውን አቶ አማኑኤል "የሕይወቴ ትዝታ" በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ጽፈውታል።

ከዚያ በኋላ "ንጉሠ ነገሥቱ በቤይስ ዎተር የከተማ ክፍል ሌላ አነስተኛ ቤት ተከራዩ። ቤቱ ሦስት ክፍል ሲኖረው ሰፋ ያለው ክፍል ቢሮ እንዲሆን፣የቀረው ሁለት ክፍል እዚያ ለሚሠሩት ጸሐፊዎች መኝታ ቤት እንዲሆን ተወሰነ። ጽሕፈት ቤቱ የተከፈተው ኢንቨርስ በሚባለው ቤት ስለሆነ፣በሌጋሲዮኑ ውስጥ የነበሩትን መዛግብት ሁሉ ይዘው ከአቶ ወ/ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ (በኋላ ጸሐፌ ትዕዛዝ) ጋር አብረው መሥራት መጀመሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ማንኛውንም ከኢትዮጵያ የሚመጣውን የመንግሥት ጉዳይ የሚሠሩት በማዕከላዊ ቢሮው መጠቀሙንም ጭምር" ነው በማለት አቶ አማኑኤል ጽፈውታል። ጃንሆይ ከሚኖሩበት ባዝ (Bath) አልፎ አልፎ ወደ ሎንዶን ሲመጡ ቢሮውን ለመኖሪያም ጭምር ይጠቀሙበት ነበር። ይህ ቢሮ ከከተማ ራቅ ያለ ስለነበረ፣ ሮዝ ጋርደንስ ቁጥር ፪ መንገድ ላይ ከተከራዩት ቤት ውስጥ ቢሮ ከፈቱ። ቤቱ የአቶ አማኑኤል መኖሪያ እና ቢሮ ሆነ። ከዚህም ጋር ተያይዞ በስደት ላይ የነበሩት ኢትዮጵያውያንም በትግሉ ለመሳተፍ ከጃንሆይና ከአርበኞች ጋር የደብዳቤ መጻጻፍ እና መልዕክተኞችም ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከአርበኞች ጋር መመካከር ጀመሩ። ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ከአርበኞች ጋር ከተመካከሩት አንዱ ዶክተር ሎሬንዞ ታዕዛዝ ስለነበሩ ወደ ኢትዮጵያ ሄደው አስፈላጊውን መረጃ ይዘው ወደ ሎንዶን ተመለሱ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ፋሽስት ኢጣሊያ፣ናዚስት ጀርመን እና ኢምፔሪያሊስቷ ጃፓን ተባብረው ከቀሪው የዓለም ክፍል ጋር ለመዋጋት አክሲስ (Axis) የሚባል ኅብረት መሠረቱ። በዚህ ሁኔታ "የአክሲስ ጦር ጓደኞች የድል ተካፋይ ለመሆን ኢጣሊያ ጓጉታ ሰኔ ፫ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. ወደ ጦርነቱ ጥልቅ ብላ ገባች*"። በሌላ በኩል ደግሞ ሩሲያን ጨምሮ የአውሮፓ አገሮች እና አሜሪካ የተባበሩት መንግሥታት ውህደት (የቃል ኪዳን ኃይሎች) (Allied Nations) በሚል ስም ተደራጁ። ቀጥሎም በእነዚህ ሁለት ኃያላን ጎራዎች መሐከል ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተጧጧፈ። "የእንግሊዝ መንግሥት፣ጣሊያን ኢትዮጵያን መውረሯን በሕግ ያወቀበትን የ፲፱፻፴ ዓ.ም. ውሳኔ ታላቋ በሪታኒያ የሻረችው በዚህ ጊዜ ነበር።



አከታትሎም የእንግሊዝ ፓርለማ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ንጉሠ ነገሥትነት ማወቁንና ኢትዮጵያ ነፃ አገር መሆኗን የሚደግፍ ውሳኔ አሳለፈ"*። ጣሊያን ከእንግሊዞች ጋር መጣላቷ ስለታወቀ የኢትዮጵያ አርበኞች ከብሪታኒያ መንግሥት ጋር ለመተባበር በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. ወሰኑ። በዚህም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስደት ከሚኖሩበት ከእንግሊዝ አገር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ጦርነቱን እንዲመሩት በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችልን በደብዳቤ ጠየቁ። የደብዳቤው መንፈስ፣የኢጣሊያ ፋሽስት መንግሥት፣ የሁለታችንም አገሮች ጠላት በመሆኗ፣የብሪታንያ መንግሥት ረድቷቸው፣ወደ አገራቸው ሄደው ከጦር ጓዶች እንደ አንዱ ሆነው በመዋጋት የኢትዮጵያን ነጻነት ለማስመለስ እንዲጋደሉ፣በጦር መሣሪያና በሌሎችም ለጦርነቱ በሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ እንዲረዷቸው የሚጠይቅ ነበር። ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለዚህ ጥያቄያቸው በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ባለ ሥልጣን ለሚስተር ቶምሰን የጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

> ኢጣሊያ ወደ ጦርነቱ ለመግባት እንደቀረጠች የሚያሳምን መንገድ ባሳየ ጊዜ ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ኃይሎችን ለመርዳትና ተባብሮ ለማጥቃት ለጠቅላይ ምኒስትር ለክቡር ሚስተር ቸርችል የጻፍነውን የደብዳቤ ቃል በእርግጥ የሚያውቁት ነው።

ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው ደብዳቤ ሚስተር ቸርችል እሺም፣እምቢም የሚል መልስ ሳይሰጥ ብዙ ጊዜ አሳልፏል። ቀደም ብዬ እንደገለጥሁት፣ለኢትዮጵያ ነጻነት ደንታ ስላልነበራቸው ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት መያዙን እንግሊዞች በቅድሚያ አምነው ይህንንም በይፋ አውጀው ነበር። ይሁን እንጂ ሙሶሊኒ በእንግሊዝ መንግሥት ላይ ጦርነት ማካሄዱን አፄ ኃይለ ሥላሴ ሲሰሙ፣እነዚህን አደገኛ የዓለም ጠላቶች ለመግታት በውጊያ አውድማው ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በመግለጥ ሁለተኛ ደብዳቤ ጽፈው ለጠቅላይ ምኒስትር ዊንስተን ቸርችል (Winston Churchil) ላኩ። ጣሊያኖች በምሥራቅ አፍሪካ እና ሊቢያ ያላቸውን ጦር ይዘው የእንግሊዝ ግዛቶችን መያዝ ስለጀመሩ፣የጣሊያኖችን ግስገሳ ቸርችል ለመግታት ሲል፣ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ ቢገቡ ሕዝቡ የማይቃወም መሆኑን ለማረጋገጥ ብዙ ምርምርና ክለሳ እንዲካሄድ አደረገ። የንጉሠ ነገሥቱን መመለስ የሚቃወሙ ባይጠፉም፣አብላጫው የእሳቸውን መምጣት የሚደግፉ መሆናቸውን እንግሊዞቹ ስለ ተገነዘቡ ከአርበኞቹ ጎን ለመቆም ወሰኑ። በሁኔታዎች አስገዳጅነት አርበኞቻችን ሁሉ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ወደ ኢትዮጵያ መግባት እንዲደግፉ በማሰብ ዘርፈ ብዙ ዝግጅት አደረጉ። ቀጥለውም አንድ መኮንን ለጃንሆይ መልክት እንዲያደርስ ከወቅቱ ጠቅላይ ምኒስትር ዊንስተን ቸርችል (Winston Churchil) በድብቅ ተላከ። ይህ መኮንን ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ ሄዶ "ነገ ወደ ሱዳን ይሄዳሉና ይዘጋጁ"* ብሎ ነገራቸው። እሱ እንዳለውም ሱዳን አገር ሲደርሱ አስፈላጊው ዝግጅት እዚያ እንዲደረግላቸው ትዕዛዝ ተላልፎ ኖሮ ወደ ሱዳን የሚሄዱበት አንድ አይሮፕላን ተፈቀደላቸው።

---

* ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፡- ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ

በዚህ ሁኔታ፣ንጉሠ ነገሥቱ፣ ልዑል መኮንን፣ሎሬንዞ ታዕዛዝ፣አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ እና የለንደን ታይምስ ጋዜጣ ተላላኪ የነበረውን ሚስተር ጆርጅ ስተርጊን አስከትለው፣ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. በስውር ካርቱም ገቡ:: እዚያ እንደ ደረሱ አንዳንድ እንግሊዛውያን መኮንኖች የእሳቸውን ወደ ሱዳን መምጣት አልፈለጉም ነበርና ለቀድሞው ጥያቄያቸው ምንም መልስ ሳይሰጧቸው፣ከካርቱም ፳፰ ማይልስ ርቆ ዓባይ ወንዝ አጠገብ ከሚገኘው ጀበል አውልያ በሚባል ቦታ እንዲቆዩ ተደረገ:: ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሱዳን ክልል ከገቡ በኋላ፣በሆነ ባልሆነ ምክንያት ጉዟቸው እንዲዘገይ ተደርጎ ከስድስት ወር በላይ አቆይዋቸው:: አንዳንዶቹ የእንግሊዝ መኮንኖች የጃንሆይን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ለምን እንዳልፈለጉ ዊልፍሬድ ቲሲገር እንደሚከተለው ገልጾታል::

> ኃይለ ሥላሴ እ.አ.አ. ሰኔ ፳፯ ቀን ካርቱም ደረሱ:: አንዳንድ የእንግሊዝ ሹማምንት የእሳቸው እዚያ መገኘት አሳፋሪ መሆኑን አምነውበታል:: በዚህም የእሳቸውን ማንነት ለመደበቅ፣አዋራጅ የሆነ «አቶ ስሚዝ» (Mr. Smith) የሚል ድብቅ ስም (የብዕር ስም) ሰጧቸው:: ለዚህም ምክንያታቸው አሁን ከጣሊያን ጋር ጦርነት ገጥመው ካሸነፉ፣ትልቋ ብሪታኒያ በሂደት አቢሲኒያን ከያዘች በኋላ በጥገኝነት የማስተዳደር ተስፋ ሰንቃ ነው::

ምናልባትም ዊልፍሬድ ቲሲገር «የሕይወቴ ምርጫ» በሚለው መጽሐፍ ገጽ ፫፻፲፫ እና ፫፻፲፬ ላይ በእንግሊዝኛ የጻፈውን ማቅረቡ የሚሻል ከሆነ ጽሑፉ እነሆ::

> Haile Selassie arrived in Khartoum on 27 June 1940. His arrival had not been welcomed by certain officials, who regarded his presence as an embarrassment. To conceal his identity, he was given the ridiculous and humiliating pseudonym of "Mr. Smith".
> " . . .Now we were at war with Italy, they hoped that Britain would eventually take over and administer Abyssinia.

ቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ ወደ ካርቱም እንዲሄዱ ፈቃድ የሰጠው ጠቅላይ ሚስትር ቸርችል የአርበኞችን ድጋፍ ለማግኘት አስቦ በአማርኛ የተጻፈ በራሪ ወረቀት ለሳትሞ ጎጃም እና በጌምድር ውስጥ ለሚገኙት አርበኞች እንዲዳረስ በአይሮፕላን አስበተነ:: ካርቱም ታትሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የተበተነው ወረቀት እንዲህ ይላል::

> ሰላም ለእናንተ (ለአርበኞች) ይሁን:: እንግሊዝ እና ኢጣሊያ አሁን በጦርነት ላይ ናቸው:: ይህን የጋራ ጠላታችንን በተቻለ መንገድ ሁሉ ለማጥፋት እንድንችል በምንችለው ሁሉ ልንረዳችሁ ወስነናል:: ስለዚህ ጠመንጃ፣ጥይት፣ምግብም ሆነ ልብስ ቢያስፈልጋችሁ መልክተኛች ከሚነግሯችሁ ቦታ ድረስ ተረካቢ ሰውና መጫኛ እንስሳት ላኩ:: የጠየቃችሁትን ሁሉ እንልክላችኋለን::



ቀደም ሲል ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ካርቱም እንደገቡ ደጃዝማች ከበደ ወደ እዚያ ሄደው አገኝተዋቸው ነበር:: ከዚያም ከኮለኔል ሳንድፍሮድ* ጋር በመሆን አርበኞች ተጠናክረው የጣሊያንን ጦር በያለበት ያለፋታ እንዲዋጉ እያበረታቱ ከጃንሆይም ጋር በደብዳቤ እንዲገናኙ አደረጉ:: አርበኞቹም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ላይ መሆናቸውን ሲሰሙ በበለጠ ወኔ ጣሊያኖችን አጠቁ:: ዘርፈ ብዙ ለሆነው የጦር ግንባር ውጊያ ስልት እንዲረዳ፣በኮለኔል ሳንድፎርድ* ቦታ ጀነራል ዊንጌት ተተካ::

ኮለኔል ሳንድፎርድ ጦርነቱ ከመቀስቀሱ በፊት የእንግሊዝ ቆንሲል ሆነው የሠሩ እና ስለ ኢትዮጵያውያን ብዙ ቁም ነገር የሚያውቁ ሰው ናቸው:: ንጉሠ ነገሥቱን እንዲያጅቡ ከተመደቡት ሰዎች በስተቀር፣አብዛኛዎቹ አርበኞች የጣሊያንን መንጋ ለመውጋት ወደ እየቦታው ተሰማሩ:: ከፊታቸው የነበረው የጠላት ጦር በእነዚህ አርበኞች እየተጠራረገ መጥፋት ጀመረ:: ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ ቀደም ብለው ድምበር ዘልቀው እንዳይገቡ እንግሊዞች ሆን ብለው ለሸረቡት ሴራ ዋናው ምክንያት፣ቢቻል ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት አድርጎ ለመያዝ፣ካልተቻለ ደግሞ እንግሊዝ በጥገኛነት (protectorate) ለማስተዳደር መሆኑን ቀጣይ ድርጊታቸው ይጠቁማል::

ከብዙ መዘግየት በኋላ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ከካርቱም ተነስተው ኢትዮጵያ ግዛት ድምበር ከሚገኘው ያሜድላ ከሚባል ስፍራ ሲደርሱ የኢትዮጵያን አረንጓዴ፣ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ:: ጃንሆይ እዚህ ቦታ ከአርበኞች ጋር ሲገናኙ የእንግሊዝ ሠራዊትና መኮንኖችም አብረው ነበሩ:: በደቡብ እና በሰሜን በኩል ደግሞ የእንግሊዝ ሠራዊት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ በሁሉም አቅጣጫ ጦርነቱ ተፋፋመ:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ከገቡ በኋላ ከአርበኞቻቸው ጋር ተገናኝተው ወደ መሐል አገር ለመግባት እንዲችሉ የጥርጊያ ውጊያው ቀጠለ:: እንግሊዞች ደግሞ በሰሜን እና በደቡብ ምሥራቅ ከሚገኙት አርበኞች ጋር ወደ መሐል ኢትዮጵያ መገስገሱን ተያያዙት:: ጃንሆይ በድል አድራጊነት መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ደብረ ማርቆስ ሲገቡ በሺሕዎች የሚቆጠሩ አርበኞች ደማቅ አቀባበል አደረጉላቸው::
የንጉሠ ነገሥቱን ወደ ኢትዮጵያ የመግባት ሂደት ያውኩት እንግሊዞች ዋና ከተማዋን አዲስ አበባን በቅድሚያ ለመያዝ እንዲመቻቸው፣አቅደው ስለነበረ በደቡብ በኩል የነበሩት አርበኞች እና የእንግሊዝ ሠራዊት በሐረር በኩል አድርገው በዚሁ ቀን፣ማለት መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. አዲስ አበባ ገቡ:: ወዲያውኑ የጣሊያንን ባንዲራ አውርደው የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ:: የእንግሊዝ ጦር መሪዎች ይህን ያደረጉት የአገራቸው መንግሥት ኢትዮጵያን በሞግዚትነት ለመምራት (ለማስተዳደር) ወስነው ስለ ነበረ ነው:: ለዚህም መነሾው ቀደም ሲል ዓባይ መውጫ ላይ እንግሊዞች ግድብ ለመሥራት እና እንዲሁም ከሱዳን ጋር ያለውን የወሰን ማሻሻል ጥያቄ ኢትዮጵያ ሳትቀበል መቅረቷ ነው:: "ይህንን ለረጅም ዘመናት የቆየውን ዓላማ ከዳር ለማድረስ አገሪቱን ከጠላት እንዳስለቀቀች በማስመሰል በቅኝ ግዛት ደንብ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር እንግሊዝ ወሰነች"::

“በተጨማሪም ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ ያስገባቻቸውን አያሌ ንብረቶች፣ የተከለቻቸውን ፋብሪካዎች ወደ ቅኝ ግዛቶች ለማሸሸ፣እንዲሁም የአገሪቱን ሀብት ለመበዝበዝ ዐቀደች። ይህን ሁሉ የእንግሊዝ መንግሥት የጠላት አስተዳር ብሎ ያወጣው የራሱ መመሪያው ያረጋግጣል*። እንግሊዞች አዲስ አበባ እንደገቡ ያካሄዱት ደባ እና እኩይ ተግባር ብዙ ነው። የመብራት ኃይል ማመንጫ ጀኔሬተሮች፣ፈብሪካዎች፣የራዲዮ ጣቢያዎች፣አውቶቡሶች፣ ካሚዎኖችና አውቶሞቢሎች፣ የመንገድ መሥሪያ መሣሪያዎች፣ማተሚያ ቤቶች፣የነዳጅ ማከማቻ ጋኖች ሳይቀሩ ወስደዋል።ከደቡብ አፍሪካ የመጣው ጦርም ቁጥራቸው ያልታወቀ ብዙ የምሕንድስና መሣሪያዎች መውሰዱን የእንግሊዝ የጦር ምኒስነር መዝግቦታል*። ይህን የመሰለ ዘረፋ እንግሊዞች ማካሄዳቸውን ኢትዮጵያውያን በመቃወማቸው አንድ የጠላት ንብረትን ሁኔታ የሚመረምር የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ። የኮሚቴው ሥራ ለሁለተኛው ዓለም ጦርነት የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች የመመርመር ሥልጣን ነበረው። ይሁን እንጂ በኮሚቴ አባልነት የተመደቡት አራት እንግሊዛውያን ሲሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን የተመደቡት ለይስሙላ ስለነበረ፣ዘረፋው ይበልጥ ተጧጥፎ ንብረቶች በገፍ መወሰዳቸው ቀጠለ። ከኢትዮጵያ የተዘረፉትን የጣሊያን ንብረቶች በተመለከተ፣አምባሳደር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፣ ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 256 እስከ ገጽ 257 በዝርዝር ጽፈውታል። ነገሩ እጅግ የሚያስቆጭ ስለ ሆነ፣የእንግሊዞችን እኩይ ተግባር የወደፊቱ ትውልደ እንዲያውቀው በማለት ከመጽሐፉ ውስጥ ቀንጭቤ ከዚህ በታች አቅርቤያቸዋለሁ።

፩. ሲቲ ጋራዥ (C.I.T.I. Workshop)፣ በዓመት ከስድስት መቶ ተሽከርካሪዎች ለመጠገን የሚችል፣ከአንድ ሺ ሁለት መቶ የጣሊያን ባለሙያዎች ጋር ከነሙሉ ወደ ኬንያ ተልኳል።
፪. ፒሬሊ (Pirelli) የጎማ ፋብሪካ ወደ ኬንያ ተወስዷል።
፫. ስባት መቶ ክዩቢክ ሜትር ኦክሲጂን የማምረት ችሎታ የነበረው ፋብሪካ ከነሙሉ ድርጅቱ ወደ ኤርትራ ተልኳል።
፬. አንድ ማተሚያ ቤት ከሐረር ተወስዷል።
፭. የወለል ምንጣፍ ማምረቻ ድርጅት ወደ ታንዛኒያ ተልኳል።
፮. አንድ የእንጨት መሰንጠቂያ ድርጅት ተወስዷል።
፯. ተሽከርካሪዎችና ዕቃዎች ተወስደዋል።
፰. ላንቻ ጋራዥ የተባለ የከባድ ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያና መጠገኛ ዕቃ ተወስዷል።
፱. ዘመናዊ የመድኀኒተ ማከማቻ ተቋም ተወስዷል።
፲. የብረታ ብረት ማቅለጫ ድርጅት ተወስዷል።
፲፩. መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብና ወርቅ ወደ ናይሮቢ ተልኳል።

አምባሳደር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ የዘረፋውን ታሪክ ያጠቃለሉትን አጠር አድርጌ በሚቀጥለው ገጽ ውስጥ ጽፌዋለሁ።



> እነዚህ እላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች፣ፋብሪካዎችና ልዩ ልዩ ተቋማት በሙሉ ለጦርነት ማገልገላቸው የሚያጠያይቅ ነው። ለምሳሌ የወለል ንጣፍ ማምረቻ ፋብሪካ እንዴት አድርጎ ለጦርነቱ የቁሳቁስ ድጋፍ እንደሚሰጥ ለመረዳት ያዳግታል። ተቋማቱ ለጦርነቱ የሚጠቅሙ እንኳን ቢሆን ኖሮ፣በነበሩበት የሚፈለገውን አምርተው ለማቅረብ ምን ያዳግታቸው ነበር? እንዲያውም የኢትዮጵያና የፈረንሳይ ምድር ባቡር ኩባንያ፣ለእንግሊዝ የጦር አስተዳደር፣የሚፈለጉትን የፋብሪካ ምርቶች ወደሚፈልጉበት የጦር ግንባር ለመላክ አመቺ ነበር።

ለታሪክ ሲባል፣ከዚህ ቀጥሎ ስለ ተማረኩት ጣሊያኖች የተፈፀመውን የእንግሊዞች ተጨማሪ ደባ መፈተሹ ተገቢ ነውና እንደሚከተለው ቀርቧል። የብሪታኒያ ጦር አዲስ አበባ እንደገባ የፖለቲካ እና የቴክኒክ አስተዳደሩን በእጁ አስገባ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ አዲስ አበባ ከመጓዛቸው በፊት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚቆዩት ጣሊያኖች ቁጥር መወሰን ያስፈልጋል ብለው የብሪታኒያ ባለ ሥልጣኖች ሐሳብ አቀረቡ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን፣ኢትዮጵያ ውስጥ ለአጭር ጊዜ ለመቆየት የሚፈልግ ማንኛውም ኢጣሊያዊ ይፈቀድለታል አሉ። ራስ አበበ አረጋይ በበኩላቸው፣፲፭ ሺሕ ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆዩ ቢደረግ የሚሻል መሆኑን ገለጹ። ውኒስተን ቸርችል ደግሞ ፭ ሺሕ ጣሊያኖች እንዲቆዩ አሳሰቡ። በኢትዮጵያ ለሚገኙት የብሪታኒያ ምክትል የፖለቲካ ሹም የሆነው ብሪጋዴር ላሽ በበኩሉ፣በስትራቴጃዊ እና ወታደራዊ ምክንያት ቁጥሩ ወደ ፪ ሺሕ ዝቅ እንዲል እና ቀይቶም ከ፩፫ እንዳይበልጥ ሚያዚያ ፫ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ሲወስን የሰጠው ምክንያት የሚከተለው ነው።

> “በሺሕ የሚቆጠሩ የጠላት ወገኖችን አገር ውስጥ ማቆየት አደጋ ሊሆን ይችላል። እዚህ አገር የጣሊያኖች መኖር ኢትዮጵያ ውስጥ ከተበታተነው የጦር ኃይል ጋር በመቀላቀል ብሪታኒያን የሚቃወም ኃይል ይፈጥራሉ የሚል ስጋት አለኝ” አለ።

ብሪጋዴር ላሽ ይህን ሃሳብ ያቀረበው፣የብሪታኒያ መንግሥት ጃንሆይ ወደ አገራቸው እንዲገቡ በማገዙ፣መሣሪያ በመስጠት እና የእንግሊዝ ሠራዊት በውጊያውም በመሳተፋቸው እንዲሁም በቅድሚያ አዲስ አበባ ስለገቡ እና በአጠቃላይም ኢትዮጵያን ስለረዷት በመኩራራት ነው።

ከውሳኔው በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከደብረ ማርቆስ ተነስተው ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ በሚገኘው ታችኛው ቤተ መንግሥት ከዋናው ሕንፃ ፊት ለፊት ከደረጃዎቹ በታች በተዘጋጀው ሰንደቅ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያን ጥገኛ (protectorate) አድርገው ለመያዝ ለማመቻቸት በእንግሊዞች ተሸርቦ ሴራውን ለማሳካት “የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ተገድቦ ነበር” በማለት፣ፕሮፌሰር አልቤርቶ ሳባኪ በጻፈው፣ኢትዮጵያ በፋሽስቶች ወረራ ዓመታት በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ጽፏል።

ኃይለ ሥላሴ ማናቸውንም የኢትዮጵያን መንግሥት በሚመለከት ጉዳዮች፣በታክስና የመንግሥት ወጪ ላይ አስቀድመው የብሪታኒያን መንግሥት ስምምነት ለማግኘት፣የውጭ አገር ዜጎችን ክስ ለእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች ብቻ ለማቅረብ፣የብሪታኒያ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ማንኛውንም የሀገሪቱን ክፍል በጦሩ ኃይል ስር ለመቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ ቢያገኘው ሳለመቃወምና የብሪታኒያ መንግሥት የሚሰጠውን ማናቸውንም ምክር ያለማወላወል ተቀብለው ሥራ ላይ የሚያውሉ ከሆነ፣የኃይለ ሥላሴን ሃሳብ ለመቀበል እንደሚችል አስታውቋል። ይህም ማለት፣ኃይለ ሥላሴ በሚያዚያ ወር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ ቢገቡም ከኢጣሊያ ጋር የሰላም ስምምነት እስኪፈረም ድረስ፣የርእሰ ብሄርነት ወይም የንጉሠ ነገሥትነት ደረጃና ሥልጣን አልነበራቸውም ማለት ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን፣የብሪታኒያን ባለሥልጣናትን ሳያሳውቁ ሰባት ሚኒስትሮችን በሾሙ ጊዜ፣ሥልጣን እንደ ሌላቸው ለመግለፅ ከእንግሊዞች ምክር (ትእዛዝ) ተሰጣቸው። በዚህ ምክንያት ሚኒስትሮቹ «ሕጩ ሹሞች» ብቻ እንደ ሆኑ ተቆጠሩ። "በዚህ ሕግ መሠረት እ.አ.አ. በ፲፱፻፵፯ የተደረገው የሰላም ስምምነት እስኪፈረም ድረስ ሁኔታው ቀጥሎ ነበር" በማለት አልበርቶ ሳቢኒ እላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ ዘግቦታል።

የእንግሊዝ ሠራዊት፣በተለይም ከደቡብ አፍሪካ የመጡት ወታደሮች የሠሩትን ግፍ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፣እንግሊዝ አገር ለሚገኙት ሴት ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡*:

፩. ጠላት ከአገራችን ሊወጣ ድል ከሆነ በኋላ በእንግሊዝ መንግሥትና በእኛ መካከል የተጀመረው ንግር ስለተቋረጠ ችግር ሆኗል። በያእወራጃው ያሉተ ፖለቲካ ኦፊሰሮች የተባሉት በኦሮሞውና በአማራው ልዩነት እንዲገ የሚሰብኩትን በግልጽ እንደዚህ ያለው አሳብ የኢጣትና የሳውዝ አፍሪቆች ይሆናል እንጂ፡የእንግሊዝ መንግሥት እና ሕዝብ ከኢትዮጵያ መሬት ምንም አይፈልገም ብለው ካስታወቁ በኋላ፣ይህን የመሰለ መጥፎ አሳብ አላቸው ማለት አይታመንም። ይህንን ለወዳጆቻችን ለማስረዳት ብትችዪ መልካም ነው። በእኛ በኩል አገራችን እማካሪ እንደሚያስፈልጋት እናውቃለን፣ነገር ግን ነፃነቷ ሳይነካ ካልሆነ፣ከጣሊያን ቀንበር ወጥታ ወደ ሌላ ቀንበር ትዞራለች ማለት፣የማይታብ ከንቱ ነገር ነው።

፪. ባገራችን ውስጥ የገባው የኢጣትና የሳውዝ አፍሪቃ ወታደር ነጭም ቀርም ቢሆን የሚያደርገው ብልግና ብዙ ነው። ገንዘብ እየዘረፈ፣ሰው እየገደለ፣የሰው ሚስት እየቀማ፣የሚሠራው ግፍ ሕዝባችንን አስመርሮት፣አስቸግሮናል። ይህ በጠላቱ እፍ እንኳን ሳይቀር የሚመሰከር ይሆናል።

፫. ወደ ዋናው ከተማችን ስንገባ፣ያስፈጃችኋል ተብሎ የተሰበከውን ሐሰትነቱን ስለተረዱት፣ሕዝባችንም ቃላችንን በማክበር የማረከውን እያመጣ ስለ አስረከበን፣በኢትዮጵያውያን እጅ ጉዳት እንደያገኛቸው ፈጽመው አውቀዋል። ይህን መጻፌ ወሬውን ለውጦ የሚያወራ ሲገኝ፣ከዚህ ጋር እንድታመዛዝኚውና እውነቱን እንደታውቂው ነው።



እንግሊዞቹ ይህን የመሰለ የአምባገነን ተግባር በመፈጸማቸው ሕዝቡ በአመቸው መንገድ ተቃውሞውን ያሰማ ጀመር። በተለይ አርበኞቹ "እንግሊዞች ሊረዱን የመጡ መስሎን እንጂ፣ዓላማቸው በገዛ አገራችን ሊያዙንና ሊገዙን ከሆነ ለዚህ፣ለዚህማ ለምን ከጣሊያኖች ጋር አምስት ዓመት ሙሉ ተዋጋንን?" ብለው አማረሩ። ማማረር ብቻ ሳይሆን መሣሪያ አንግበው ለመዋጋትም ተነሱ። የብሪታኒያ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች የኢትዮጵያውያንን ስሜት ስለ ተረዱት፣ቀድሞ የነበራቸውን አቋም ለውጠው፣ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መሪ መሆናቸውን አምነው ውስጥ ለውስጥ ይዘውት የነበረውን ሥልጣን ቀስ በቀስ አስረከቧቸው። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዙፋናቸው ላይ ተመልሰው በመቀመጣቸው ከልብ ይደግፉ የነበሩት ሐኪም ወርቅነህ የ"እንኳን ወደ አገርዎ በሰላም ገቡ" የሚል የደስታ መግለጫ በስደት ከነበሩበት ሕንድ አገር ላኩላቸው። ቀጥሎም በሰኔ ወር ላይ እሳቸውም (አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ) ወደ አገራቸው ለመግባት መፈለጋቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ጻፉላቸው። ጥያቄያቸው ተቀባይነት ስላገኘ የሕንድ መንግሥት ከአገር የመውጫ ፈቃድ እንዲሰጣቸው በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የተጠየቀላቸው መሆኑን በመግለጽ ንጉሠ ነገሥቱ ጥር ፪ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. የላኩላቸው ቴሌግራም (cable) ደረሳቸው። ሐኪም ወርቅነህ ወደ አገራቸው ለመግባት ላቀረቡት ጥያቄ ከሕንድ መንግሥት በኩል ፈቃድ ባለማግኘታቸው፣ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከላቸውን ቴሌግራም በማሳየት ወደ ኤደን ለመሄድ ፈቃድ ጠየቁ። ሕንድን ለቅቀው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ወስነው ስለነበረ፣የልጆቻቸውን የተማሪ ቤት ሂሳብ ሁሉ ከፍለው እና ደህራ ዱን የነበራቸውን ጉዳይ ፈጽመው የካቲት ፫ ቀን ከነልጆቻቸው ወደ ለክናው (Lucknow) አመሩ። እዚያ ሲደርሱ ወዳጃቸው ራጃ ሰር ማሃራጅ ሲንግ (Raja Sir Maharaj Singh) ወደ አዘጋጁላቸው ሆቴል ገብተው አረፍ አሉ። ከዚያም ሰር ማሃራጅ ሲንግ ምሳ ጋበዛቸው። ለክናው ተቀምጠው ፓስፖርታቸውን አሳድሰው በመንዝ ቦምቤይ የካቲት ፱ ቀን ደረሱ። ቦምቤይ እንደ ደረሱ የውጭ ጉዳይ ኃላፊዎች፣በኤደን እና በርበራ በኩል ወደ ጅቡቲ የሚገቡበትን መንገድ ለማመቻቸት ቃል ገቡላቸው። በዚህ መሠረት ወደ ቦምቤይ የመንግሥት የፖለቲካ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ሄደው ወደ ጅቡቲ የመሄጃ ፓስፖርት ታድሶ የካቲት ፲፱ ቀን ተሰጣቸው። ይሁን እንጂ ከቦምበይ መጋቢት ፲፫ ቀን ተነስቶው ኤደን የደረሱት መጋቢት ፳፩ ቀን ነው። ኤደን እንደ ገቡ ከአገረ ገዥው ከሰር ጀ ኸርሶርን (Sir J. Hurthorn Hall) ጋር ምሳ በልተው፣ከሚስተር ኮዋጂ ዲንሾው (Mr. Cowaji Dinshaw) ጋር ሻይ ጠጡ። መጋቢት ፳፮ ቀን የኤደን አርጉስ (Aden Argus) ጋዜጣ አዘጋጅ ጋር ቃለ ምልልስ አደረጉ። በማግስቱ መጋቢት ፳፯ ቀን ከአ.ቤስ. ኩባንያ Besse Co.) በተከራዩት ጀልባ ተሳፍረው፣በውሽንፍር የታጀበው ባህር አቋርጠው፣እንደምን ብለው ጅቡቲ ደረሱ። ሁኔታዎች ከተመቻቸላቸው በኋላ ጅቡቲ ላይ ባቡር ተሳፍረው ሚያዚያ ፬ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. አዲስ አበባ ደረሱ። ለገሐር ባቡር ጣቢያ ድረስ ሄደው ይጠብቋቸው የነበሩት ልጆቻቸውና ወዳጅ ዘመድ በእልልታና በደስታ ተቀበሏቸው።

ከዚያም ቀደም ሲል ልጆቻቸው ሁኔታዎችን አመቻችተው ስለነበረ፣በቀጥታ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ይዘዋቸው ሄደው ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ተገናኙ። ግርማዊነታቸው እና አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ፣የ"እንኳን ለአገርዎ አበቃዎ" መልካም ምኞት ከተለዋወጡ በኋላ ጃንሆይን ተሰናብተው አራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ ወደሚገኘው የቀድሞ ቤታቸው ሄዱ። እሳቸው ወደ አገራቸው መመለሳቸውን የሰሙ ኢትዮጵያያን እና የውጭ አገር ወዳጆቻቸው ያለማቋረጥ ወደቤታቸው እየመጡ ለብዙ ቀናት "እንኳን ወደ አገርዎ በደህና ገቡ" በማለት የደስታ መዕልክት ሲገልጡ ከረሙ። የእንግዶቹ ቁጥር ጋብ ሲል፣የ፲፫ ልጆቻቸው እናት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ወደሚኖሩበት የካ ሚካኤል አካባቢ ወደሚገኘው ቤት ሄዱ።

ወይዘሮ ቀጸላ ቱሉ ጣሊያን አገር በግዞት በነበሩበት ጊዜ ከተዋወቋቸው ከደጃዝማች ታዬ ጉልላት ጋር ሁለቱም ከእስር ተፈትተው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ትዳር መሥርተው ነበር። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እዚያ ሲደርሱ፣ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ፣ደጃዝማች ታዬ፣በዚያን ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ዶክተር ሎሬንዞ ታእዛዝ፣የትምህርት ሚኒስትሩ አቶ መኮንን ደስታ እና የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አቶ ጌታሁን ተሰማ እንዲሁም ሌሎች መኳንንትና ወይዛዝርት ግቢው ውስጥ ተሰባስበው በናፍቆት ይጠብቋቸው ነበርና ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉላቸው። የእንኳን ደህና መጡ አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ ወደ ተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ ተቀመጡ። ስለ ጤናቸው እና ስለ ጉዟቸው ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ ማዕድ ቀርቦ ምሳ ተበላ። የግብዣው ሥርዓት እንደተጠናቀቀ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ለአገራቸው ያበረከቱት አስተዋፅኦ በሰፊው ተነገረ። በቀጠልም አሁን ወደ ውድ አገራቸው ስለመጡ ቸሩ አምላክ ረጅም ዕድሜና ጤና እንዲሰጣቸው በመመኘት የሻምፓኝ ግብዣ ተደረገ። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህም በበኩላቸው ለተደረገላቸው መስተንግዶ ልባዊ ምስጋናቸውን አቀረቡ። የግብዣው ሥነ ሥርዓት እንዲህ በአማረ ሁኔታ ተፈፅሞ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ አብረዋቸው በሚኖሩት ልጆቻቸው ታጅበው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ተመለሱ። በማግስቱ ቀድሞ የሚያውቋቸው አንድ የአዳል ትልቅ ባላባት ወደ ቤታቸው መጥተው "በአዳሎችና በሶማሌዎች መሐከል ትልቅ ጠብ ተነስቷልና እርስዎ ተደማጭነት ስላለዎ እባክዎን ወደ እዚያ መጥተው ያስታርቁልን" ሲሉ ጠየቋቸው። እሳቸው በጤና ምክንያት ወደ አዳል ለመሄድ ስላልቻሉ፣ብላታ መርስዔ ኀዘን እንዲሄዱ አደረጉ። ብላታ መርስዔ ኀዘንም ሄደው በሁለቱ ወገኖች መሐከል የነበረውን ጠብ አብርደው እና አስታርቀው ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ተመለሱ።

ጣሊያኖች ከአገራችን ከተባረሩ በኋላ፣ወይዘሮ አስቴር የአባታቸውን ንብረቶች ሲያስተዳሩ ስለነበረ በእጃቸው የሚገኘውን ሰነድና ገንዘብ፣ለአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ አስረከቡ። ሰነዶቹን ሲመረምሩ በጣሊያኖች ተወርሶባቸው ከነበሩት ንብረቶቻቸው መሐከል ያልተመለሱላቸው መኖሩን ዐወቁ።



ስለዚህ በዚያን ዘመን "የጠላት ንብረት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት" ተቋቁሞ ስለነበረ ሳይመለሱላቸው የቀሩት ንብረቶች እንዲሰጧቸው ለጽሕፈት ምኒስቴር አመለከቱ። ለጥያቄያቸው ምንም መልስ ሳያገኙ በመቅረታቸው ይህንኑ ለንጉሠ ነገሥቱ አመለከቱ። የሐኪም ወርቅነህ ጥያቄ ትክክል መሆኑን ጃንሆይ ስላመኑበት የጽሕፈት ሚኒስትሩ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ተጠርተው፣ጣሊያኖች የወረሷቸውን የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ንብረት አስረክቧቸው ብለው አዘዟቸው። ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በበኩላቸው በትእዛዙ መሠረት፣በጠላት ተወርሰው የነበሩት የሐኪም ወርቅነህ ንብረቶች እንዲመለስላቸው፣በዚያን ዘመን የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ለነበሩት ለልጅ ይልማ ደሬሳ ትእዛዙን አስተላለፉ። ልጅ ይልማ ትእዛዙን ተቀብለው፣አቃቂ በሰቃ ድልድይ ጎን የሚገኘውን በውሀ የሚሠራ የእህል ወፍጮ እና በአካባቢው የነበራውን ቤቶችና መሬት እንዲመለስ የጠላት ንብረት አስተዳደር ኃላፊ ለነበሩት ለአቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ ነገሩ። በዚህ ዓይነት አብዛኛው ንብረት ሲመለስ፣ወፍጮው አጠገብ ባለው ቤትና ቦታ ላይ ጣሊያኖች አቋቁመውት የነበረው የመኮረኒ ፋብሪካ አልተሰጣቸውም ነበር። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በቤቴ እና በቦታዬ ላይ ያለው ንብረት ይመለስልኝ ብለው ሲጠይቁ፣የመኮረኒ ፋብሪካውን "አዳ ወንድማማቾች ተከራይተውታል እና የውል ጊዜው እስኪያልቅ ይጠብቁ" ተባሉ።

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በበኩላቸው ንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ የሰጡት ንብረቶቻቸው በሙሉ እንዲመለስ ስለሚል "ፋብሪካውን ጭምር መረከብ አለብኝ። ከእንግዲህ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ተከራዮቹ መነጋገርና መዋዋል ያለባቸው ከእኔ ጋር ብቻ ነው። ስለዚህ ፋብሪካውን አሁኑኑ መረከብ እፍልጋለሁ" በማለት ፍርጥም ብለው ለልጅ ይልማ ደሬሳ ተናገሩ። የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ልጅ የወይዘሮ ኤሊሣቤጥ ባለቤት የሆኑት ልጅ ይልማ የንጉሠ ነገሥቱን ትእዛዝ አክብረው ፋብሪካውን ለተከበሩት አማቻቸው ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣በሁለቱ መሐል ትንሽ አለመግባባት ተፈጠረ። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በጣም ተናድደው ስለነበረ በአማቻቸው ላይ ጥቂት የቁጣ ቃል ሰነዘሩ። ከዚያም እንደተለመደው ወደ ቤተ መንግሥት ሄደው እሳቸው በሠሩት ቤት ውስጥ ጣሊያኖች ያቋቋሙት የመኮረኒ ፋብሪካ እና ጣሊያን ከተባረረ ጊዜ ጀምሮ ድርጅቱን የተከራዩት ሰዎች ለመንግሥት የከፈሉት ኪራይ ጭምር እንዲሰጣቸው ጠየቁ። እንደተለመደው፣ግርማዊ ነገሥቱ ነገሩን በጥሞና ከሰሙ በኋላ፣የመንግሥት ግብር ተሰልቶ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ከነፋብሪካው ለሐኪም ወርቅነህ እንዲሰጥ አዘዙ። በትእዛዙ መሠረት አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ንብረቱን እና ገንዘቡን ተረከቡ። እንዲሁም በጣሊያኖች ተወርሰው የነበሩ ሌሎች ንብረቶቻቸውንም አስመለሱ። ከነዚህም መሐከል በኤደን መንገድ የሚገኘውን ፎቅ ቤት ለአንድ ዳቦ ጋጋሪ ግሪክ በወር ፻፶ ብር ተከራይቶ የነበረው አንዱ ነው። ሌላው ከራሳቸው መኖሪያ ቤት አጠገብ ያለውን ግቢ አሼዲስ ቴሬዚያን ተከራይቶት የነበረ መኖሪያ ቤት ነው። እነዚህን ቤቶች ከተረከቡ በኋላ ከተከራዮቹ ጋር ውል ተፈራርመው እሳቸው ራሳቸው አከራይዋቸው።

በሐምሌ ወር ውስጥ፣ከእንግሊዞች ጋር ስለነበረው ስምምነት ጉዳይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ፣እስከ አሁን ያለው አቋም (policy) አገርን የሚጎዳ በመሆኑ፣ጠንከር ያለ አካሄድ መያዝ አለብን ሲሉ መከሩ:: ይህን ሃሳባቸውን በማጠናከር ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. በእንግሎ—ኢትዮጵያ መሐከል የተደረገውን ወታደራዊ ስምምነት በመተቸት (በመንቀፍ) ሲልቪያ ፓንክረስት ባጋዜጣ እንድታወጣው፣አዲስ ተሹመው ወደ ሎንዶን በሚሄዱት በአምባሳደር ብላታ አየለ ገብሬ እጅ ላኩላት:: በዚህ መሐል ንጉሠ ነገሥቱ ጥቂት ሕመም ተሰምቷቸው ስለነበረ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ከመረመሩ በኋላ ተገቢውን መድኃኒት ስለሰጧቸው ጤናቸው በመስተካከሉ፣ጃንሆይ ተደስተው ሐምሌ ፴ ቀን ወደ ቤተ መንግሥት ጠርተው አመሰገኗቸው:: እንዳጋጣሚም ይሁን ታስበበት አይታወቅም፣የዚያን ዕለት የአገር አስተዳደር ምኒስትር ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው ወደ ጎን ጠርተዋቸው፣እንግሊዛዊ ሐኪሙ በአማካሪነት ይሠራ በነበረበት ምድብ ተተክተው የብሄራዊ ጤናና የሕክምና ዲሬክተር ተብለው መሾማቸውን ነገሯቸው:: ሐኪም ወርቅነህ "እስቲ በጉዳዩ ላስብበት" ብለው ከሄዱ በኋላ በማግስቱ ሥራውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ለምኒስትሩ ነገሯቸው::

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ አገራቸው ከመጡበት ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸው እንደነበረ እስካሁን ካነበብነው መገንዘብ ይቻላል:: አሁን በስደት ከነበሩበት አገር በሰላም ለመኖር ከተመለሱ በኋላም ቢሆን ችግሮችና ውዝግቦች በየጊዜው ማጋጠሙ አልቀረም:: ለበርካታ ቤተሰቦቻቸው እና በእሳቸው ስር ለሚተዳደሩት ሰዎች መርጃ የሚሆን ገንዘብ እንደሚያስፈልጋቸው ግልጥ ነው:: ለዚህም ሲባል ንብረቶቻቸውን በማስተዳደር የገቢ ምንጭ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል:: ለዚህ ነው በየቦታው ተበታትነው በሌላ ሰው እጅ የገቡትን ንብረቶች የሚቆጣጠሩት:: ለምሳሌ አሩሲ ከጃንሆይ ርስት ጉልት ተቀንሶ የተሰጣቸው መሬት እንዲመለስላቸው ሲጠይቁ፣ርስት አስተዳዳሪው አልሰጥም ብሎ አስቸግሯቸው ነበር:: እንደ ተለመደው ይህንንም በደል ለንጉሠ ነገሥቱ ነግረው ስለነበረ፣ርስት ጠባቂያቸው መሬቱን ለአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እንዲያስረክብ ተነግሮት ወዲያውኑ መሬቱን አስረከባቸው:: ሌላው ችግር ደግሞ፣የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እና የብላታ ደሬሳ አመንቴ ይዞታ የነበረው ዩብዶ በሚባል ቦታ ወለጋ ውስጥ የሚገኘው የፕላቲነም እና የወርቅ ማዕድን ማምረቻ ላይ፣አሜሪካዊው ሚስተር ጊጊኖ አሌክሳንደር (Mr. Ghighino Alexander) አስተዳዳሪ ተብሎ በገንዘብ ምኒስቴር መሾሙ ነበር:: ይህንንም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በተነጋገሩበት ጊዜ እስከዚያን ቀን ድረስ በመንግሥት ስር ለነበረበት ዘመን ኪራይ እንዲከፈላቸውና ማዕድኑን ለመረከብ ጠየቁ:: ጃንሆይ ጥያቄያቸውን ከሰሙ በኋላ ገንዘብ ምኒስትርን እንዲጠይቁ መከሯቸው:: ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ማዕድኑ እንዲመለስላቸው ስለ ተፈቀደ፣ከሽሪካቸው ከብላታ ደሬሳ ጋር ማዕድን የማምረት ሥራውን ጀመሩ:: በመቀጠልም ከሕንድ አገር የየኤሌክትርክና የሜካኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም ሁለት መምህራን ለማስመጣት ጃንሆይን አስፈቀዱ::



ከዚያም ሕንድ ለሚገኘው ወዳጃቸው ለሰር ሳርዳህ አሊ ካን (Sir Sardah Ali KJahn) ደብዳቤ ጽፈው፣ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች መልምሎ እንዲልክላቸው እና ከተቻለም ለማዕድኑ ሽሪክ የሚሆን "ሀብታም ሕንዳዊ" ሰው እንዲፈልግላቸው ጠየቁት:: እሱም በጥያቄው መሠረት የተፈለጉትን ባለሙያዎች ቀጥሮ ላከላቸው:: ባለሙያዎቹ አዲስ አበባ ሲደርሱ ሁለቱ የቴክኒክ ሰዎች ዩብዶ በሚገኘው የማዕድን ማምረቻ ውስጥ እንዲሠሩ ላኳቸው:: መምህራኑን ደግሞ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተመደቡ:: ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ወደ ቤተ መንግሥት ሄደው ስለነበረ፣ጃንሆይ አቃቂ ያለውን ንብረትዎን መጠበቂያ ይሁንዎት ብለው ሁለት አልቢን ጠመንጃዎች ሰጧቸው::

መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ.ም. የእንቁጣጣሽ ዕለት ወደ ቤተ መንግሥት ሄደው ግርማዊ ጃንሆይን እና ግርማዊት እቴጌ መነንን ለአዲሱ ዓመት በሰላም በመድረሳቸው፣መጪውም ዓመት የጤና እና የሰላም እንዲሆን በመመኘት እጅ ነስተውና ምሳ ተጋብዘው ወደቤታቸው ተመለሱ:: ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ ይሸነፉ እንጂ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ፣እስያ እና አፍሪካ ውስጥ ሲካሄድ ብዙ ጊዜ ፈጅቷል:: ይሁን እንጂ እንደ ተጠበቀው ሁሉ የተባበሩት መንግሥታት ውህደት በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. (E.C. 1945) የጦርነቱ አሸናፊ ሆነ:: በዚህ ጦርነት ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት እንግሊዝ፣አሜሪካ፣ፈረንሳይ እና ሩስያ ነበሩ:: የአክሲስ ኃይሎች በጦርነቱ ስለተሸነፉ እንኳንስ የቀድሞ የቅኝ ግዛታቸውን ማስከበር ይቅር እና የገዛ አገራቸውም ቢሆን በአሸናፊዎቹ ቁጥጥር ስር ዋለ:: አብዛኛውን "የጠላት ይዞታ" የተቀራመቱት እንግሊዝ፣ፈረንሳይ እና ሩሲያ ናቸው:: በዚህ ሁኔታ፣ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት የጣሊያን ቅኝ ግዛት የነበረችው ኤርትራ ዕጣ ፈንታዋ በእንግሊዞች ሞግዚትነት ስር መውደቅ ሆነ::

የጠላት ንብረት ነው በማለት እንግሊዞቹ ከኢትዮጵያ የወሰዱት ሀብት አልበቃ ብሏቸው፣ከኤርትራም በእጃቸው የገባውን ንብረት ሁሉ ወደ ቅኝ ግዛታቸው ኬንያ ያጉዙ ነበር:: ቀደም ሲል በጣሊያኖች ከዚያ በኋላ ደግሞ በእንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀሙትን እኩይ ተግባራት ሚስ ፓንክረስት እየጻፈች ግፋን ከማጋለጥ አልቦዘነችም ነበር:: ጣሊያኖች በጋዝ ያነፈሩትን፣ጥይት የደበደቡትን፣በስቅላት የቀጡትን፣በእሳት ያጋዩትን እና አንገቱን ቆርጠው፣አፉ ውስጥ ሲጋራ ወሽቀው የተሳለቁበትን እና በፊሽስት ኢጣሊያ የተፈፀመውን ግፍ "አዲስ ዘመንና የኢትዮጵያ ዜና" በሚባለው መጽሔቷ ውስጥ እያሳተመች ታወጣ ነበር:: እንደዚሁም እንግሊዞች ነፋስ ስልክ (?) ዐፀዋን የሲሚንቶ ፋብሪካ ነቃቅለው ሲወስዱ፣ሕንፃዎችን አፈራርሰው ስብርባሪውን ለመሸጥ ወደ ዐረብ አገሮች በመርከብ ሲያጓጉዙ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች እና ኤርትራ ከእናት አገሯ ኢትዮጵያ ተነጥላ በእንግሊዝ መንግሥት አስተዳደር ስር እንድትሆን የሚሸርቡትን ተንኮል ሁሉ በዚሁ መጽሔት ውስጥ ሲልቪያ ፓንክረስት አጋልጣለች:: እሷ ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ የጻፈችው ይህ ብቻ አይደለም:: አገር ከተረጋጋ በኃላ የኢትዮጵያ የባህል ታሪክ (Cultural History of Ethiopia) የሚባል መጽሐፍ ጻፋለች::

ኢትዮጵያን ኦብዘርቨር (Ethiopian Observer) የሚባለውን መጽሔትም ታዘጋጅ ነበር። ሚስ ሲልቪያ ፓንክረስት የኢትዮጵያ ታላቅ ወዳጅ በመሆኗ ወደ አዲስ አበባ መጥታ ስትኖር ቆይታ እዚሁ ስለ ዐረፈች አስክሬኗ ተቀብረው ለኢትዮጵያ አርበኞች በተዘጋጀው የመቃብር ቦታ በቅድስት ሥላሴ ግቢ ውስጥ ነው። እግረ መንገዳችንን፣ሚስ ሲልቪያ እና ሲኞር ኮሪዮ ልጅ ሲወልዱ ሪቻርድ የሚል ስም አወጡለት። እንደ ፈረንጆቹ ልማድ በአባቱ በኮሪዮ ስም ሳይሆን ሪቻርድ የሚጠራው በሴት አያቱ በኩል ያለውን ስም ወርሶ ሪቻርድ ፓንክረስት በሚል ስም ነው።

ሐኪም ወርቅነህ፣ናዝሬት አካባቢ ወንጂ በሚገኘው መሬታቸው ላይ ጣሊያኖች የስኳር ፋብሪካ አቋቁመው እንደነበረ ተነገራቸው። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ሥራውን ለማስፋፋት ማሰባቸውን ለጃንሆይ ገልጸው መሬቱ እና ፋብሪካው እንዲመለስላቸው ጠየቁ። ንጉሠ ነገሥቱም ይህን በተመለከተ ማመልከቻ ጽፈው ለገንዘብ ምኒስቴር እንዲሰጡ ነገሯቸው። በዚሁ ጊዜ ውስጥ ከግርማዊነታቸው ጋር ለመወያየት የሚፈልጉት ጉዳይ መኖሩን ገለጡላቸው። ታኅሣሥ ፪ ቀን ባደረጉት ውይይት መሐል በታይም ጋዜጣ ስለ ሐረር የሚያትተውን እትም ለጃንሆይ አሳይዋቸው። በጋዜጣው ውስጥ ከተጻፈው መሐከል "አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የጨርጨር አስተዳዳሪ ሆነው ይመደቡልን" የሚል የአዳል የጎሳ መሪዎች እና ባላባቶች ጥያቄ ያከተተ ነበር። ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ እያለ፣ታኅሣሥ ፲፯ ቀን የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ልጆች፣ዮሐንስ እና ሳሙኤል (ቻርሊ) ወደ ግብፅ ሄደው ቪክቶሪያ ኮሌጅ እንዲማሩ ፈቅደው ወጪውንም ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ እንደሚከፍሉላቸው ነገሯቸው። አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለሥራ ጉብኝት በሚሄዱበት አንዳንድ ቦታ አይለይዋቸውም ነበር። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ተከፍቶ ሲመረቅ፣አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ የበዓሉን ተሳታፊ ነበሩ። ቀደም ብሎ እንደ ተገለጠው፣ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወርራ በነበረችበት ወቅት የተማሩ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እያደነች ደምስሳለች። በዚህ ምክንያት ነጻነት ከተመለሰ በኋላ የተማረ ሰው እጥረት ስለነበረ፣የመንግሥት አማካሪዎች፣ከፍተኛ ዳኞች፣የፖሊስ ኮሚሽነሮችና የወታደርና አየር ኃይል አሠልጣኞች የውጭ አገር ሰዎች ነበሩ። እነዚህን ሰዎች ለመተካት ይቻል ዘንድ፣የተማረ ሰው ማፍራቱ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አልነበረም። አዲስ አበባ ውስጥ በመጀመሪያ የተከፈቱት ባለባት (በኋላ መድኃኒ ዓለም)፣ተፈሪ መኮንን፣ዳግማዊ ምኒልክ እና አርበኞች ትምህርት ቤት የሚባሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ቀጥሎም የመምህራን ማሠልጠኛ፣ተግባረ እድና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረቀ ዕለት፣እንደ እንግሊዞቹ አባባል "እጩ" የትምህርት ምኒስትር ሆነው የተሾሙት አቶ መኮንን ደስታ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ የትምህርት ቤቱን ስም አበሰሩ። በመቀጠልም ግርማዊነታቸው የትምህርትን ጠቃሚነት እና አስፈላጊነት ገለፁ።



ቀጥለውም፣በጠላት ዘመን በንፁሃን ኢትዮጵያውያን ላይ ከደረሰው ግፍና ሰቆቃ አምልጠው፣ይህን ቀን ለማየት ለበቁት ምክር ሲሰጡ "መከራን የቻለ ያሸንፋል" ብለው ለትምህርት ቤቱ አርማ እንዲሆን ፈቀዱ። ያ ትምህርት ቤት ዛሬ ኮተቤ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ በመባል ይታወቃል።ከጠላት ወረራ በኋላ ስለ ትምህርት ቤቶች መከፈት ከዚህ በላይ የሰፈረውን እና አሁንም በተጨማሪ ከዚህ በታች የምጽፍበትን ምክንያት በቅድሚያ መግለጡ ተገቢ ይሆናል። ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

አንደኛ:- ኢጣሊያ ከአገራችን ከተባረረች በኋላ፣ትምህርት ቤቶች እንዴት እንደተከፈቱ እና የነበረውን ችግር ለመግለጥ

ሁለተኛ:- የመጀመሪያው ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲከፈት የነበረውን ሂደት ለማሳወቅ

ሦስተኛ:- ትምህርት ቤቱ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንደ ነበረ ለማሳየት

አራተኛ:- ጥሩ እንክብካቤ የተደረገላቸው ወጣቶች፣ተምረውና አድገው፣ አገራቸውን በቅንነት ለማገልገል፣ ለራሳቸውም መልካም (ጥሩ) ስም ለማትረፍ እንደሚችሉ፣ለተተኪው ትውልድ ለማሳወቅና አርዓያነታቸውን እንዲከተሉ ለማሳሰብ

አምስተኛ:- በቀ.ኃ.ሥ. ፪ኛ ደረጃ ት ምህርት ቤት ምክንያት ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እሸቱ ጋር ለመተዋወቅና ከቤተሰቡም ቅርብ ግንኙነት እንዲኖረኝ ዕድል ማግኘቴ ለዚህ መጽሐፍ መታተም ያነሣሣኝ በመሆኑ ነው

በወቅቱ የአገሪቷ ኢኮኖሚ የሚያወላዳ ባይሆንም፣ለትምህርት ልዩ ትኩረት በመስጠቱ፣ለመንግሥት ቢሮዎች እና ተቋማት የተማረ ሰው በቶሎ ሊያዘጋጅ ይችላል ተብሎ ተስፋ የተጣለው በዚያን ዘመን ብቸኛ በነበረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነበር። በዚህ ትምህርት ቤት፣ጥሩ ምግብ፣ምርጥ ልብስ፣ንፁህ መኝታ እና የገላ መታጠቢያ ክፍል፣ሙሉ የስፖርት ትጥቅ፣የጠረጴዛ ቴኒስ፣የሜዳ ቴኒስ፣የእግር ኳስ ሜዳ፣መዋኛ ገንዳና የሚጋለቡ ፈረሶች ከአሠልጣኝ ጭምር ተዘጋጅቶ ነበር፡ በትምህርት በኩል በቂ የትምህርት መሣሪያ እና የተሟላ መጻሕፍት ቤት ነበረ። ትምህርት ይሰጥ የነበረው ቀኑን ሙሉ ሲሆን፣ማታ ከአንድ ሰዓት እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ የጥናት ጊዜ ግዴታ ነበር። በእነዚያ ሁለት ሰዓታት ውስጥ ተማሪዎቹ ወይ የቤት ሥራቸውን (home work) ይሠራሉ አለበለዚያም ያጠናሉ። ይህ ለመፈፀሙ ማታ ማታ የሚቆጣጠር ተረኛ አስተማሪ አለ። ልክ ሦስት ሰዓት ላይ፣ተማሪዎቹ ሁሉ ወደ መኝታ ቤታቸው ሄደው፣ገላቸውን ታጥበው አለያም ተፀዳድተው አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው ይወያያሉ። እስከ አራት ሰዓት ድረስ ተረኛ አስተማሪው በየክፍሉኙ እየዞረ፣ተማሪዎቹ በየአልጋቸው ላይ መሆናቸውን ያያል። አራት ሰዓት ላይ መብራት ማጥፋታቸውንና ሁሉም በየአልጋቸው ላይ መተኛታቸውን አረጋግጦ ወደ ቤቱ ይሄዳል። መብራት ከጠፋ በኋላ ማውራት ቀርቶ መንሾካሾክ እንኳን አይፈቀድም ነበር።

ይህን የሚቆጣጠሩ የተማሪ አለቃዎች በየመኝታ ቤቱ አሉ:: የአለቆቹ ኃላፊነት ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ ተማሪ ሁሉ ጸጥ ብሎ መተኛቱን፣ጧት ጧት ደግሞ አልጋቸውን ማንጠፋቸውን እና የመኝታ ክፍሎች በደንብ ማጽዳታቸውን፣ቀን ቀን ደግሞ ምግብ በሰዓቱ መመገባቸውን መቆጣጠር እና በትምህርት ግቢው ውስጥ በስነ ሥረዓት ተግባራቸውን መፈጸማቸውን መከታተል ነው:: ይህ ሁሉ ተዳምሮ ተማሪዎቹ ዕውቀት በማካበት እንዲጎለምቱ ብቻ ሳይሆን፣በማንኛውም ጊዜና ቦታ የጨዋነት ተግባር እንዲፈጽሙ በማድረግና በመቆጣጠር፣ከእነዚህ መመሪያዎች ዝንፍ የሚለውን ይመክሩ ነበር:: ደንቡን ያወጣው፣በእንግሊዝ አገር የታወቀው የኢተን የወንድ ልጆች ትምህርት ቤት (Eton School for Boys) ዲሬክተር የነበረው፣ሚስተር ብለንደን ኤሊስ ትክክለኛ የሆነ ጨዋ እንግሊዛዊ* ነበር:: የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልክ እንደ ኢተን ምርጥ የወንዶች ልጆች ትምህርት ቤት እንዲሆን ይጥር ነበር:: ተማሪዎቹም ቢሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ እንዲኖራቸው የሚጥር ሰው ነበር:: በአስተዳደር በኩልም፣ጥብቅ የሆነ አመራር ይሰጥ ነበር:: ከዚህ ትምህርት ቤት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች፣ወደፊት የአገር መሪ እና አስተዳዳሪ ይሆናሉ የሚል ሙሉ እምነት ነበረው:: ለዚህ ዓላማ ግብ መምታት እንዲዘጋጁ ለማስቻል፣ልክ እንደ ኢተን ትምህርት ቤት፣ተማሪዎቹ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ፣የተማሪ መሪዎችና ሹሞች (Student Governors and Prefects) ከተማሪዎቹ መሐከል ይመረጡ ነበር:: የቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሆኑ ግርማዊነታቸው ልዩ ትኩረት ይሰጡት ነበር:: በዚህም ምክንያት እሁድ፣እሁድ ለተማሪዎቹ ፍራፍሬና ብስኩት፣በጾም ጊዜ ደግሞ ዓሣ አስይዘው ወደ ትምህርት ቤታችን ይመጡ ነበር:: ተማሪ ቤቱን ሲጎበኙ ልጆችን ስለ ትምህርታቸው ይጠይቃሉ:: ተማሪዎቹ የጠረጴዛ ቴኒስ (ፒንግ ፖንግ) ሲጫወቱ ከደረሱ እሳቸው ኳስ መምቻውን (ራኬት) ከአንዱ ልጅ ተቀብለው አንድ ሁለት ጊዜ ኳሷን ያጠነጉት ነበር:: ተማሪ ቤቱ ለሦስት ወር ዕረፍት ተዘግቶ ከቆየ በኋላ መስከረም ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. እንደገና የተከፈተ ዕለት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ተምህርት ቤቱ የመጡት ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጋር ነበር::

በዚያን ቀን የመጨረሻ ልጃቸው ዳዊት ወርቅነህም አባቱን ተከትሎ መጥቷል:: ጃንሆይ የትምህርት ቤቱን ሁኔታ አይተው እና ልዩ ልዩ ክፍሎችን ጎብኝተው ከግቢው ወጥተው ከመሄዳቸው በፊት፣ዳዊት ወርቅነህ በአዳሪ ተማሪነት እዚህ እንዲማር መፍቀዳቸውን ለዲሬክተሩ ነገሩት:: ሚስተር ብለንደን ኤሊስ ትዕዛዙን ተቀብለው ዳዊት ከተማሪዎቹ አንዱ ሁኖ ተመዘገበ::



ከትምህርት ቤቱ ሥነ ሥርዓት አንዱ፣በዕድሜ ትንሽ የሆነ ልጅ ወደዚህ ትምህርት ቤት ለመማር ሲገባ፣የትምህርት ቤቱን ደንብ እና ሥርዓት እንዲያውቅ የሚረዳውና ትምህርት የሚያስጠናው ከእሱ ታላቁ የሆነ ልጅ መመደብ ነበር:: አዲስ የገባው ዳዊት ወርቅነህ ከትናንሽ ልጆች አንዱ ስለ ነበረ "ታላቅ ወንድም" እንድሆነው የተመደብኩት እኔ ታደሰ ብጡል ክብረት ነበርኩ:: ስለዚህ እኔ የተማሪዎች አለቃ (Prefect) በሆንኩበት የማደሪያ መኝታ ክፍል አልጋ ተሰጠው:: በትምህርት ቤታችን ውስጥ በተሰጠኝ ኃላፊነት እና ለዳዊት ወርቅነህ "ታላቅ ወንድም" ሁኜ በመመደቤ ለመቀራረብ በቃን:: በእረፍት ቀናት ዳዊት እየጋበዘኝ ወደ አባቱ ቤት እሄድ ስለነበረ፣ ከአዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ጋር ለመገናኘት እና በሂደትም ስለ እሳቸው እና ቤተሰባቸው ብዙ ነገር የማወቅ ዕድል አጋጠመኝ:: እኔ የዳዊት ጓደኛ እና "ታላቅ ወንድም" በመሆኔ ከ፲፱፻፴፯ እስከ ፲፱፻፵፬ ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ፣ከገበታቸው በመቋደስ "ቤተኛ" የመሆን ዕድል አገኘሁ::

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ቤት፣ለሁሉ ነገር ሥርዓት ነበረው:: በየቀኑ ምግብ የሚዘጋጀው በ፲፪ ዕለታዊ የምግብ ቤት ወንበሮች ልክ ነው:: ምሳም ይሁን እራት ለመብላት አስቀድሞ የተናገረ ሰው ከተዘጋጁት ወንበሮች ላይ ተቀምጦ የመብላት ዕድል (መብት ልበለው?) አለው:: እሳቸው ቤት ለመመገብ የፈለገ ሰው የሚጠበቅበት በቅድሚያ ስሙን ማስመዝገብ ብቻ ነበር:: ምሳ ወይም እራት ሲደርስ ቃጭል ይደወላል:: ምግቡን የሚቋደሱት ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ሲይዙ በአንዲት ክብ የነሐስ ጎድጓዳ ሣህን ውስጥ፣ለብ ያለ ውሀ እና ከሣህኗ ጋር ግማሽ ሎሚ ከእያንዳንዱ ሰው ፊት ይቀመጣል:: በሙቅ ውሀው ውስጥ ጣቶችን እየነከሩ በሎሚው አሽቶ ከታጠቡ በኋላ ምግብ ይቀርብና መብላት ይጀመራል:: ምግብ ተበልቶ ከአለቀ በኋላም እጅ የመታጠቡ* ሥርዓት በዚሁ ዓይነት ይፈጸማል:: የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በማዘጋጀት ላይ እያለሁ ስለዚህ ሁታ ከወይዘሮ ሱዚ ጋር መወያየት ጀመርን:: እንደ ዕድል ሆኖ ምሳ ሲቀርብ በዚያን ዘመን ሐኪም ወርቅነህ ቤት እጃችንን እንታጠብበት ከነበሩት ጎርጓዳ ሣህኖች ሁለቱ ቀርበውልን እኔና አባዬ ሱዚ እንደወትሮው እጃችንን ስንታጠብ ለትዝታ የተነሳነው ፎተግራፍ ተነሳን:: ፎተግራፉን በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ:: ሐኪም ወርቅነህ ከእሳት ማሞቂያው አጠገብ ማታ ማታ ቁጭ ብለው ልጆች ሲደንሱ ማየት ያስደስታቸው ነበር:: ስለዚህ፣በዚያን ዘመን በነበረው በእጅ መዘውር የሚሞላው የሸክላ ማጫወቻ (gramophone) የዳንኪራ ሙዚቃ ይከፈታል:: ወንዶችና ሴቶች ልጆች እየደነስን እሳቸውን እና ራሳችንን እናስደስት ነበር:: በዚያን ዘመን ወለሉን በዳንኪራ ከምናሟሙቀው መሐከል፣ከወንዶቹ ማርቆስ ደስታ፣ዳዊት* ወርቅነህ እና እኔ ታደሰ ብጡል ክብረት ነበርን:: አብረውን የሚደንሱት ሴቶቹ ልጆች ደግሞ፣የሐኪም ወርቅነህ የዘመድ ልጆች የሆኑት አጸደ፣ዐመለ ወርቅ እና ጓደኞቻቸው ነበሩ:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የመጨረሻ ሴት ልጃቸው ሊያም አልፎ አልፎ አብራን ትደንስ ነበር:: ትዳር የያዙት ሴቶች ልጆቻቸው፣ብቻቸውን ወይም ከባለቤቶቻቸው ጋር ሐኪም ወርቅነህን ለማየት ምሽት ላይ ከመጡ፣ዳንሱን አቋርጠን እና እጅ ነስተን እንቆማለን::

ወይም እኛ ወደ ሌላ ክፍል ሂደን እነሱ እስኪሄዱ እንጠብቃለን፣አለበለዚያም በሐኪም ወርቅነህ ፈቃድ ዳንኪራችንን እንቀጥላለን። በአጋጣሚ በጣም ሕፃን የሆኑት የልጅ ልጆቻቸው ከወላጆቻቸው ጋር ከመጡ፣ዳንስ ለማስለመድ የእነሱን እግር፣እግራችን ላይ አቁመን እናስጨፍራቸው ነበር። በሆነ ምክንያት አደናነሳችን ቀዝቀዝ ካለ፣ሐኪም ወርቅነህ የወንበራቸውን የእጅ መደገፊያ በሙዚቃው ንዝረት ልክ መታ፣መታ እያደረጉ "ልጆች ደንሱ፣ደንሱ" ይሉን ነበር።



እኔ እስከማውቀው ድረስ ሐኪም ወርቅነህ ቤት የሚመጣ ማንኛውም ሰው፣ በሃይማኖት፣በጎሳ እና በሀብት ሳይለይ፣ትንሽ ትልቅ ሳይባል ተስተናግዶ የሚሄድበት ቤት ነበር። እሳቸው ቤት የሚኖሩትም ይሁኑ ከውጭ በእንግድነት የምንመጣው ሰዎች ሁሉ በመፈቃቀር እና በመከባበር እንደ ታላቅና ታናሽ እንቀራረብ እና እንተያይ እንደ ነበረ አስታውሳሁ። የቤተሰቡን ታላላቆቻችንን ሰዎች ስም ስንጠራ፣ሴቶቹን "አባዬ"፣ወንዶቹን ደግሞ "አብዬ" በማለት በአክብሮት እንጠራቸው ነበር። :ከእነሱ አነስ ያሉትን ደግሞ፣"ጋሼ" እና «እትዬ» እያልን ነው። ለምሳሌ ወይዘሮ አስቴርን "አባዬ" ባለቤታቸው አቶ በፈቃዱ ወልደ ሚካኤልን "ጋሼ በፈቃዱ"፣እንዲሁም ወይዘሮ ሱዚን "አባዬ" ባለቤታቸው አቶ መኩሪያ ወልደ ሥላሴን "አብዬ መኩሪያ" ብለን እንጠራቸው ነበር። ወይዘሮ ኤሊሣቤጥን "አባዬ" ባለቤታቸውን ልጅ ይልማ ደሬሳን ደግሞ፣በሕዝብ ዘንድ በሚታወቁበት አጠራር "ልጅ ይልማ" በማለት እንጠራቸው ነበር።






ሐኪም ወርቀነህ ከእሳት መሞቂያው አጠገብ ተቀምጠው የእኛን ዳንኪራ ሲመለከቱ

ዳዊት ቀደም ሲል እንግሊዝኛ ማንበብና መናገር ይችል ስለነበረ፣ዕድሜው ከእኛ በእጅጉ ያነሰ ቢሆንም የተመደበው የእሱ ታላላቆች ከሆንነው ተማሪዎች ክፍል ነበር። በዚያን ዘመን መምህራኖቻችን ከሚሰጡን ቀጥተኛ ትምህርት በተጨማሪ፣የንባብ ልምድ እንዲኖረን እና የቋንቋ ችሎታችን እንዲዳብር በክፍል ውስጥ ቆመን መጽሐፍ ጮክ ብለን በማንበብ የመጽሐፉን ይዘት የክፍሉ ተማሪ እንዲያውቀው ይደረግ ነበር። በሚቀጥለው ገጽ ውስጥ ዳዊት ቆሞ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ሲያነብ ይታያል። በዚህ ፎተግራፍ ከፊት ያሉት ከተማ ይፍሩ፣ኃይሉ ደስታና ዳዊት ሲሆኑ፣ከኃይሉ ጀርባ ግንባሬ የሚታየው እኔ ታደለ ብጡል ክብረት ነኝ። በመጨረሻው ረድፍ ፊቱን አግድም አዙሮ የሚታየው መንግሥቱ ለማ ነው።

ከዚህ በታች ከሚታየው ፎተግራፍ ልብ ልንለው የሚገባው፣ቀደም ሲል እንደገለጽሁት፣የትምህርት ቤታችንን የደንብ ልብስ አጅግ ያማረ መሆኑን እና እኛ ተማሪዎቹ መንግሥት የሰጠንን ልብስ በንጽህናና በጥንቃቄ ጠብቀን ወደ ትምህርት ክፍል ስንገባም ይሁን በሌላ ቦታ የደንብ ልብሳችንን በኩራት የምንለብስ መሆኑን ነው።

በሐኪም ወርቅነህ ፈቃድ ዳንኪራችንን [illegible]
የሆኑት የልጅ ልጆቻቸው ከወላጆቻቸው ጋር ከመጡ፣ዳንስ ለማስለመድ የእነሱን እግር፣እግራችን ላይ አቁመን እናስጨፍራቸው ነበር። በሆነ ምክንያት አደናነሳችን ቀዝቀዝ ካለ፣ሐኪም ወርቅነህ የወንበራቸውን የእጅ መደገፊያ በሙዚቃው ንዝረት ልክ መታ፣መታ እያደረጉ "ልጆች ደንሱ፣ደንሱ" ይሉን ነበር።





ሐኪም ወርቅነህ ከእሳት መሞቂያው አጠገብ ተቀምጠው የእኛን ዳንኪራ ሲመለከቱ


ዳዊት ቀደም ሲል እንግሊዝኛ ማንበብና መናገር ይችል ስለነበረ፣ዕድሜው ከእኛ በእጅጉ ያነሰ ቢሆንም የተመደበው የእሱ ታላላቆች ከሆንነው

Plate CXII.



እንዲሁም በሳይንስ ትምህርተ ጊዜ፣ በመምህራኖቻችን መሪነት በተግባር የተደገፈ የምርምር ሥራ በላቦራቶሪ ውስጥ እናካሂድ ነበር። በቀጣዩ ገጽ የሚታየው ፎተግራፍ በሳይንስ ክፍል ሆነን መምህራችን ዶክተር ቶምሶን እና እኛ ተማሪዎች ረቂቅ ህዋሳትን በማይክሮስኮፕ ስንመለከት ነው። የዚያን ጊዜው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርተ ቤት የተማሩት ወጣቶች አብዛኞዎቹ ለአገራቸው ከፍተኛ አገልግሎት የሰጡና በመስጠት ላይ የሚገኙ ናቸው። ስመ ጥር ሐኪሞች፣ተመራማሪዎች፣የሕግ ባለሙያዎች፣ መሐንዲሶች፣የፖለቲካ መሪና የአስተዳደር ባለ ሥልጣን ለመሆን በቅተዋል። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተማሩት መሐከል፣በሥዕል ጥበብና በሥነ ጽሑፍ ክህሎት አንቱ ለመባል የበቁ ሆነዋል። በአጭሩ ለመናገር፣በዚያ ጊዜ በቀዳማዊ ኃይል ሥለሴ ሁለተኛ ደረጃ ትህርት ቤት ይሰጥ የነበረው ትምህርትና የተማሪዎች አስተዳደር ወጣቱን ለአገር ጠቃሚ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት የታቀደውን ግብ አሟልቷል ለማለት ይቻላል።





ከፊት ረድፍ ከቀኝ ወደ ግራ፣የሳይንስ ክፍል ተማሪዎች አሰፋ ወልደ ጊዮርጊስ፣ኃይሉ ነገም፣ታደለ ብጡል ክብረት፣ሀብቱ እሸቴ፣ዘውዴ ገብረ መድኅን፣ሙሉጌታ ሥነ ጊዮርጊስ ሲሆኑ በማይክሮስኮፕ የሚመለከተው መንግሥቱ ለማ ነው።


አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ ምንም ቢሸመግሉ፣ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ብዙ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በቅርብ ይገናኙ እንደ ነበረ በሕይወት ታሪካቸው ማስታወሻ መድበል ( Memoirs) ውስጥ ጽፈውታል። ለምሳሌ ያህል አንዳንዱን እጠቅሳለሁ። ለዕልት ፀሐይ ለኮለኔል ዓቢይ አበበ ለሠርግ ተጋብዘው ነበር። በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የቤተሰብ ቅልቅል ግብዣ ሲደረግ፣ከሚስተር አትሂል (Mister Athil) እና ከሚስተር ኮሊየር (Mister Collier) ጋር በክብር እንግድነት ተጋብዘዋል።

ሚያዚያ ፳፩ ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ለእህታቸው ለልዕልት ፀሐይ ምሳ በመጋበዝ መልስ ጠርተው ስለ ነበረ ክቡር አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ እሸቱ ከተጋባዦቹ አንዱ ነበሩ። ምሽት ላይ ደግሞ፣እቴጌ መነን የእናታቸው የወይዘሮ ስሂን ቤት በነበረበው ግቢ ባዘጋጁት የእራት ግብዣ ላይ ከተጋባዦቹ አንዱ ሆነው ተገኝተዋል።

PLATE CXII.








ከፊት ረድፍ ከቀኝ ወደ ግራ፣የሳይንስ ክፍል ተማሪዎች አሰፋ ወልደ ጊዮርጊስ፣ኃይሉ ነገዎ፣ታደለ ብጡል ክብረት፣ሀብቱ እሸቴ፣ዘውዴ ገብረ መድኅን፣ሙሉጌታ ሥነ ጊዮርጊስ ሲሆኑ በማይክሮስኮፕ የሚመለከተው መንግሥቱ ለማ ነው።

[illegible] ሐኪም ወርቅነህ ምንም ቢሸመግሉ፣ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ብዙ



ሙሽሮቹ ከነሚዜዎቻቸው:: ከግራ ወደ ቀኝ ወ/ሮ ሐና ማርቆስ፣አቶ ኀይለገበና፣ ወይዘሮ ኤልሣቤት ወርቅነህ፣ልዕልት ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ ኮሎኔል ዓቢይ አበበ (በኋላ ጀነራል)፣ ወ/ሮ ሣራ ወርቅነህ እና ሻለቃ (በኋላ ልዑል) አሥራት ካሣ (በኋላ ልዑል)

ልዕልት ፀሐይ ጋብቻ ከፈፀሙ በኋላ ባለቤታቸው ኮለኔል ዓቢይ አስተዳር ወደሆነው ወሎ ሄዱ:: በጣም የሚያሳዝነው እኝህ ለጋ ወጣት እና ለሕዝብ አገልግሎት ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጡ የነበሩት ነርስ ልዕልት ፀሐይ በወሊድ ምክንያት ነሐሴ ፲፩ ቀት ነቀምት ዐረፉ የሚል መርዶ መምጣቱ ነበር:: ከሁለት ቀን በኋላ አስከሬናቸው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በታላቅ ኀዘንና ዋይታ ተቀበረ:: ሐኪም ወርቅነህ ልዕልት ፀሐይን ቀደም ሲል በቤታቸው፣በኋላም ከራሳቸው ልጆች ጋር ወደ ውጭ አገር ወስደው እንዲማሩ ያደረጉ፣በስደትም ጊዜ እንግሊዝ እና ስዊስ አገር የነርስነት ትምህርት እንዲማሩ የመከሩ እና የረዱ የመንፈስ አባታቸውም ነበሩ:: ከዚህም በላይ ሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው የልዕልቲቷ ሚዜዎች ናቸው:: ይህ ሁሉ ተዳምሮ ሐኪም ወርቅነህ፣በወጣቷ ልዕልት መሞት እጅጉን አዝነው ከረሙ:: የሐኪም ወርቅነህ ልጅ ርብቃ፣ቀደም ሲል ከአቶ ጌታሁን ተሰማ ጋር ለመጋባት ተጫጭተው ስለበረ፣የልዕልት ፀሐይ ኀዘን ላይ መቀመጡ ጋብ ሲል፣ሁለቱ እጮኛሞች ጋብቻቸውን ፈፀሙ:: ግንቦት ፲፮ ቀን ከሰዓት በኋላ ጃንሆይ ጠርተዋቸው ስለ አገር ጉዳይ በሰፊው አነጋገሯቸው::



በውይይቱ መሐል፣በጥር ወር ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ከእንግሊዞች ጋር የተፈራረሙትን የእንግሎ—ኢትዮጵያን ውል ግልባጭ ሰጧቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይ በሰፊው ሲወያዩ ሐኪም ወርቅነህ ውሉ የጨቋኞች ውል ሆኖ አገኙት::* ቀደም ብዬ እንደ ገለጥሁት የእንግሊዞች ሐሳብ ኢትዮጵያን በጥገኝነት ይዞ ለመቆየት ነበር:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዙፋናቸው ላይ እንዲቀመጡ ከጎኛም ጀምሮ እየመራ እና እንግሊዞች እሳቸውንና ሕዝባቸውን የበደሏቸውን ለማስተካከል የሞከረ ሰው ቢኖር ጀነራል ዊንጌት ነው:: እንግሊዞች የኢትዮጵያን ነፃነት ለመንጠቅ ማሰባቸውን በመገንዘቡ "በጠላት የተያዙ ግዛቶች አስተዳደር" Enemy Occupied Territories Admisnistration የሚባለውን በኢትዮጵያ የተቋቋመውን አሠራር ጀነራል ዊንጌት አበክሮ ይቃወም ነበር::

የእሱን አባባል ዊልፍሬድ ቴሲገር ሲጽፍ "After receiving the Anglo-Ethiopian Agreement he considered it to be very imperialistic" ብሏል:: በዚህ እና በሌሎችም ምክንያቶች በአጋጣመው ብስጭት፣ዊንጌት ፈርቶና ተስፋ ቆርጦ በመጨነቁ፣አንገቱን በካራ ገዝግዞ ለመሞት በመሞከሩ በሆቴሉ ወለል ላይ ነፍሱን ስቶ ወድቆ ተገኘ:: ዊንጌት ራሱ ጽፎ የተወው ማስታወሻ ደግሞ "እኛ ኢትዮጵያን የያዝናት በበራድና በአምባገነናዊነት ነው:: ነፃ ለማውጣት ነው ብለን የምንናገረውም የማይረባና ተልካሻ አባባል ነው:: እኔ ራሴን ብገድል ሰዎች ረጋ ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸው ይሆናል" ይላል::

(I thought our treatment of Ethiopia is cold and tyrannical, and our talk of liberation miserable cant. I thought my death at my own hand would make people pause and think).

ከዚህ ጽሑፍ የምንረዳው የእንግሊዞች ሐሳብ ከመጀመሪያውኑ ኢትዮጵያን የእነሱ ጥገኛ ለማድረግ ስለነበረ፣ሐኪም ወርቅነህ እንዳሉትም የጨቋኝ ዓላማቸውን Anglo—Ethiopian Agreement በሚል ውል ሸርበው መጡ:: ሐኪም ወርቅነህ ከጃንሆይ ጋር ተገናኝተው ለረጅም ጊዜ ከተነጋገሩ በኋላ፣ኢትዮጵያ ከእንግሊዞች ጋር በሚኖራት ግንኙነት ጠንካራ አቋም እንዲይዙ መከሯቸው:: ሐኪም ወርቅነህ ነሐሴ ፩ ቀን ለሚስ ሲልቪያ ፓንክረስት የላኩት ረጅም ጽሑፍ የእንግሊዝና የኢትዮጵያን ወታደራዊ ስምምነት አጥብቀው የነቀፉበት ድርሰት ነበር:: ይህን ጽሑፍ ለሚስ ፓንክረስት ያደረሱት አዲስ የተሾሙት በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ምኒስቴር ናቸው:: ይህ ውል ለረጅም ጊዜ እንግሊዝና ኢትዮጵያን ሲያወዛግብ ቆይቶ ነበር:: በመጨረሻ ከሎርድ ዴላዋር ጋር የከረረ ክርክር ከተደረገ በኋላ ነበር ሁኔታዎች የተስተካከሉት::


ሆኖም፣ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ የሚሆነው፣የተማሩ ሰዎችን በአስቸኳይ ማፍራት ነበር:: ሐኪም ወርቅነህ ጃንሜዳ ሠርተውት ከነበረው ዘመናዊ ቤት አጠገብ የተከፈተውን የፖሊስ ማሠልጠኛ በጃንሆይ ተጋብዘው ሄደው አዩ::



ሙሽሮቹ ከነሚዜዎቻቸው። ከግራ ወደ ቀኝ ወ/ሮ ሐና ማርቆስ፣ አቶ ኀይለጎበና፣ ወይዘሮ ኤልሣቤት ወርቅነህ፣ ልዕልት ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ ኮሎኔል ዓቢይ አበበ (በኋላ ጀነራል)፣ ወ/ሮ ሣራ ወርቅነህ እና ሻለቃ (በኋላ ልዑል) አሥራት ካሣ (በኋላ ልዑል)




በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. Anglo–Ethiopian Agreement ያሻሻለው ኮሚቴ አባላት




በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. Anglo—Ethiopian Agreement ያሻሻለው ኮሚቴ አባላት

እግረመንገዳችንን፣በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. የተከፈቱት የማሠልጠኛ ከተቋቋመው የተግባረ እድ ትምህርት ቤት በስተቀር ሁሉም በችኮላ በመሆኑ ሥራቸውን የጀመሩት በጊዜያዊ ቤትና ቦታዎች ላይ ነበር። ለምሳሌ፣የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት የተጀመረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ግቢ ሲሆን የመምህራን ማሠልጠኛው ደግሞ፣በኋላ ለፖሊስ ኮሌጅነት በተሰጠው ሕንፃ ውስጥ ነበር። በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ታግባረ እድ ሙያ ማሠልጠኛ፣በ፲፱፴፭ ዓ.ም. ቀ.ኃ.ሥ. ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር የተከፈቱት ለታሰበው ዕቅድ በተገነቡ ሕንፃዎች ውስጥ ባይሆኑም ጠንካራ እና ጥሩ ቤቶች ናቸው።

መስከረም ፩ ዓ.ም. ፲፱፻፴፮ ቀን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እና ግርማዊት እቴጌ መነንን እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሰልን ለማለት ወደ ቤተ መንግሥት ሄደው፡ ለንጉሣውያን ቤተሰቡ ያላቸውን መልካም ምኞት ገለጹ።



እዚያው ግብር (ምሳ) በልተው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ወደቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት፣ሳሙኤል (ቻርሊ) ወርቅነህ እና ቦጋለ ወደ ፖሊስ ማሠልጠኛ እንዲገቡ አስፈቀዱላቸው።

ወንጂ በነበራቸው መሬት ላይ ጣሊያኖች የስኳር ፋብሪካ አቋቁመውበት እንደነበረ ሰሙ። ንብረታቸው እንዲመለስላቸውና ተጨማሪ መሬት ለማስፈቀድ ጃንሆይን ሲጠይቁ ማመልከቻ ይጻፉ ተባሉ። ሁኔታው ሲጣራ፣ቀደም ሲል እሳቸው ተክለውት የነበረው መሣሪያ ተነቅሎ፣ሌላ በጣም ከፍ ያለ መሣሪያ ተተክሎ ስለነበረ ሁኔታው ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ፣ጨርጨር የሚገኘውን ንብረታቸውን ለማየት ሐኪም ወርቅነህ በባቡር ተሳፍረው መዔሶ ወርደው ጉዟቸውን ቀጠሉ። አሰበ ተፈሪ ደርሰው ንብረታቸውንና እሳቸው ለከተማዋ ዕድገት ብለው የሠሯቸውን ተቋማት ሁሉ እየዞሩ ሲያዩ፣አብዛኛው ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ተለውጦና ተበላሽቶ አዩ። ከአሰበ ተፈሪ ጉብኝት በኋላ በጨርጨር ዳር አገር የሚገኙትን አንዳንድ ቦታዎችን አይተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በዚህን ጊዜ የወንጅ ስኳር ፋብሪካ ስለሚመለስላቸው የስኳር ማምረት ፈቃድ እንዲያድሱ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መከሯቸው። ፈቃዱ ታድሶ ሥራ ለመጀመር ሲሉ አብዛኛው መሣሪያ ተበላሽቶ እና ተነቃቅሎ ስለነበረ ፋብሪካውን ለማንቀሳቀስ ሳይቻል ቀረ። የአዛዥ ሐኪም ወርቅነህን ንብረት ያስተዳድሩ የነበሩት ልጃቸው ወይዘሮ አስቴር ይቀበሉት የነበረውን የቤት ኪራይ አሁን እራሳቸው ይቀበሉ ጀመር። ለምሳሌ፣ከራሳቸው መኖሪያ ቤት አጠገብ ያለውን፣ዛሬ ቸርቸል ጎዳና በሚባለው መንገድ ዳር የነበረውን ባለ ሁለት ፎቅ ቤት፣እንዲሁም ዛሬ ኤደን መንገድ በሚባለው ዳር ያለውን የዳቦ መጋገሪያ ቤት ኪራይ ተቀበሉ ነበር። ተከራዮቹ አቬዲስ ቴሬዚያን፣ገብረያና፣ኤቫል እና ሃርዲ ናቸው። እግረ መንገዳችንን ዛሬ ቤርሻኮ የሚባለው የሽቶ ፋብሪካ በመጀመሪያ የተቋቋመው ሐኪም ወርቅነህ ሕንፃ ውስጥ ሲሆን፣ማዳም ሃርዲ ለብዙ ዘመናት ሥራውን ሲመሩ ቆይተው ልጃቸው ተረክቦ ሲሠራ ነበር።

ወጣቱ ሐርዲ፣ለሽቶ መቀመሚያ የሚሆኑ ጭማቂ የሚያወጣው ወንዶ ገነት ከሚገኘው ሰፊ የእርሻ መሬት ከሚበቅሉት ዕፀዋት ነበር። መጭመቂያውም እዚያው ወንዶ ገነት የተተከለ በመሆኑ (ደን ኮሌጅ አጠገብ)፣ምርቱን ወደ ፈረንሳይ አገርም እየላከ ብዙ የውጭ ምንዛሬ ያገኝ እንደነበረ ነግሮኛል። ቦታውን ለእኔ እና በዚያን ዘመን የንግድ ምኒስትር ለነበሩት አቶ ኃይሉ ይመኑ አስጎብኝቶናል። እኛ ድርጅቱን የጎበኘነው፣የሽቶ እፀዋት ማብቀያ የነበረው መሬት በደርግ ዘመን ገበሬዎች ሰብቀሎና ማሽላ ማሳ አውለውት፣ መጭመቂያውንም ከጥቅም ውጭ አድርገውት በነበረበት ጊዜ ነው። ሐርዲ በዚህ ተበሳጭቶ ለአሁኑ የቤርሻኮ ባለንብረቶች ሸጦ ከአገር ወጥቷል። ያ ከዛሬ አርባና ሃምሳ ዓመት በፊት ከውጭ አገር በሚገቡ የሽቶ ተክሎች ጭምር ለምቶ የነበረው ቦታ እንደዚያ ተበላሽቶ ማየት፣እጅግ በጣም ያሳዝናል።

አዛዥ ሐኪም ወርቅነህ በኢትዮጵያ ውስጥ የፈጸሟቸውን ተግባራት እስካሁን አንብበናል። እስኪ ስለ ሰብዕናቸውንና ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ጥቂት ልበል።